ሥርዓተ ሚሞተ ክህነት

ለሚመተ ኤጲስ ቆጶሳት
የተዘጋጀ ልዩ እትም

ዋና አዘጋጅ

መልአከ መዊዕ ቀሲስ ሳሙኤል እሸቱ

ም/አዘጋጅ

ቃለ መጋቤ ሀብታት ቃለ ወንጌል ...
መ/ር አካለወልድ ተሰማ (ዶ/ር)

ኮምፒዩተር ጽሑፍና አርትኦት

ላእከ ሰላም ነቢዩ ኤልያስ

ገጽ ቅንብር

ውብዓለም ዘውዱ

ፎቶግራፍ

መልአከ ሰላም አባ ኪሮስ ወልደአብ

ኅትመት

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

ማውጫ

ገጽ

ርዕሰ አንቀጽ 3
ቅዱስ ሲኖዶስ መግለጫ ፓትርያርክ 5
መልእክት ቅዱስ ፓትርያርክ 8
የብፁዕ ጠቅላይ ዋና ሥራ አስኪያጅ መልእክት 10
ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ መልእክ 14
አባ ሣህለ ማርያም ቶላ ግምቢ 18
አባ ወ/ገብኤል አበበ ጨመዳ 19
ሊቀ ጉባኤ ቆሞስ አባ ጥላሁን ወርቁ ደሳለኝ 20
ቆሞስ አባ ዓምደ ሚካኤል ኃይሌ ደገፋ 21
ቆሞስ አባ ኃይለ ማርያም ጌታቸው ዘሊቦ 22
አባ ተክለሃይማኖት ገብሬ ደርሶ 24
ቆሞስ አባ እስጢፋኖስ ገብሬ ዘውዴ 25
መልአከ ምሕረት ቆሞስ አባ ክንፉ ገብርኤል ተክለ ማርያም ደሌቦ
አባ ስብሐት ለአብ ኃይለ ማርያም አንጆጆ 28
ሥርዓተ ሚመተ ክህነት 30
ሕገ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አበው 33
እኮተ ሐዋርያትና ፈተናዎቹ 38
መርዐገ ኤጲስ ቆጶስ በጥንታውያን 45
ኤጲስ ቆጶስ (ጳጳስ) አባታዊ ተግባርና ኃላፊነት 55

ርዕሰ አንቀጽ

የምድር ጨው

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድራዊ አገልግሎቱ አንቀጸ ብፁዓንን ባስተማረበት ጉባኤው ደቀ መዛሙርቱን አስተምሮና አሰልጥኖ ፤ ሾሞና ባርኮ በሥልጣን ወደዓለም ከማሰማራቱ በፊት ዋጋቸው ምንያህል የከበረ እንደሆነ ያወቁ ዘንድ እናንተ የምድር ጨው ናችሁ ብሎ ነግሯቸዋል ማቴ 5-13

በጥንት ዘመን ከፀሐይ በታች ከጨው የበለጠ ዋጋ ያለው ነገር እንደሌ ለሮማውያን ያምኑ ነበር። ሮማውያኑ መገበያያቸው ጨው ስለነበር ለአንድ ነገር ዋጋ ሲሰጡ በጨው ልኬት ነበር። አንድ ነገር ዋጋ የማያወጣ ሆኖ ሲያገኙት “የጨው ዋጋ የለውም” ሲሉ ርካሽና አላስፈላጊነቱን ይገልጣሉ ። ከዚህም በተጨማሪ በጥንታውያን ዘንድ ጨው የመተማመንና የቃል ኪዳን ምልክት ተደርጎም ይወሰዳል ። ለምሳሌ ሁለት ሰዎች በመካከላቸው ጥል ያስከተለ ፀብ ቢኖር ጨው ከተካፈሉ ቀደም ሲል የነበረውን ፀብና ክርክር የሚሸረው ስለሆነ አንዳቸው የሌላውን ደህንነት የመጠበቅ ውል እንዳደረጉ ይቆጠር ስለነበር በሁለቱ ወገኖች መካከል ቃል ኪዳንን ለማሰር ጨው ያገለግል ነበር ።እንዲሁም በጥነት ዘመን ጨው ምግብ እንዳይበሰብስ ለማቆያነትና ምግብ ጣዕም እንዲኖረው ያገለግልነበር። ስለዚህ ጨው የሚለው ቃል የተቀጠለለት አንድ ሰው «የተከበረ፤ ውድና አስፈላጊም» የሚለውን ትርጉም ይሰጠዋል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን እናንተ የምድር ጨው ናችሁ። ብሎ ሲጠራቸው ከላይ የጠቀስነው ከጸሐይ በታች በጊዜው ያለ ውድ ዕቃ አድርገው እራሳቸውን እንዲቆጥሩ የሚያስጠነቅቅና የሚያሳስብ ቃል ነው። እነሱም ይህን የጌታን የቃልኪዳን ይዘው የወንጌል ምስክሮች ሆነው በኢየሩሳሌም ፤ በሰማርያና በይሁዳ እንዲሁም በምድር ዳርቻ ሁሉ ፤ በመስበክና በማሳመን ያለመታከት ተግባራቸውን ተወጥተዋል። ዛሬ ባለንበት የመጨረሻው ዘመን ላይ ለምንገኝ ውሉደ ክህነት የምድር ጨው ሆነን ዓለምን በክርስቶስ ወንጌል ጣዕም ለማጣፈጥና ለመንግስቱም ወራሽ ዜጎች ለማፍራት የተጠራን ሁነን ሳለ በየደረጃው አልጫውን ዓለም ለማጣፈጥ ያለን አቅም ጠፍቶ እራሳችን በአፍአ (በውጪ) እንደ ደንቢያ የምንወረወርበት የማስጠንቀቂያ ዘመን ላይ ደርሰናል።

በሚመተ ኤጲስ ቆጶስነት በዛሬው ዕለት የተሰየማችሁና ለዚህ ታላቅ ክብርና ተልዕኮ የተመረጣችሁ ብፁዓን አበው አባቶቻችን ያለንበት ዘመን በሀገራችን በቸልታ ሊታለፉ የማይችሉ በርካታና ውስብስብ የሆኑ ችግሮች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩበት ወቅት በመሆኑ በቤተ ክርስቲያን የምሰጡት አገልግሎት የጊዜው ምልክቶች በጥልቀት የምትገመግሙበት፤ የምትተረጉሙበት በሐዋርያዊ አገልግሎታችሁ ዙሪያ ያሉትን ተቃርኖዎች በጥልቀት በመረዳት በሱታፌአችው ሁሉ የጨውነት ጣዕማችሁን እንዳታጡ የኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ እምነታችሁን አቋም ማጽናት ይጠበቅባችኋል።

ብፁዓን አበው ኤጲስ ቆጶሳት ርትዕትና ጽንዕት ከሆነችው ቤተ ክርስቲያን ዓለሙን እንደጨው እንድታጣፍጡ ታላቅ ተልዕኮ በተሰጣችሁ በዚህ ወቅት በሀገራችን ውስጥ ያልተፈታ የፖለቲካ ቀውስ፤ ሥር የሰደደ የብሔር አመለካከት፤ ጽንፍ የወጣ የሃይማኖት አክራሪነት ፤ ሊቋጩ ያልቻሉ ግጭቶችና ጦርነቶች የበዙበት ወቅት በመሆኑ ሐዋርያዊ ተልዕኮውን ለመወጣት በጠቀስናቸው ችግሮች የተተበተበውን ማህበረሰብና ሀገር ለመቀየር የምድር ጨው የመሆን ሚናችሁ ጎልቶ ሊታይና በሥራ ሊተረጎም ይገባል።

ዛሬ የተቀበላችሁት የአባትነት አደራ ዘረኛነት ጣራ ነክቶ የእኔ ብሔርና ጎሳ አባት ሆኖ ካልተሾመ የሚል ሙግትና ንትርክ እስካሁን

በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ውስጥ ባልተለመደ ሁኔታ ሀገርና ቤተ ክርስቲያንን ታላቅ ችግር ውስጥ በከተተበት ወቅት መሆኑ ችግሩ ምን ያህል ጥልቅና በአንዲት እናት ቤተ ክርስቲያን ጉያ ውስጥ ያለነውን የአንድ ሰማያዊ አባት የእግዚአብሔር ልጆችን እየከፋፈለ የሚገኝና በስከተለውም ችግር ምክንያት በሕዝበ ክርስቲያኑና በአገልጋዩ መካከል፤ እንዲሁም እርስ በእርስም ታላቅ ልዩነት እየፈጠረ መሆኑን በመረዳት ለሁሉ አባትና እረኛ በመሆን የተፈጠረውን ክፍተት በመሙላት በሁሉ ኢቃፊነት መንፈስ የአባትነታችሁን አደራ ለመወጣት የምድር ጨው መሆን ያስፈልጋችኋል።

ከዚህ ሐገ ወንጌል ትአዛዝና አደራ አንጻር የዛሬው ሥዩማን ብፁዓን አበው ኤጲስ ቆጶሳት የድሆች መብዛት፤ የስደተኞችና የተፈናቃዮች ቁጥር መጨመር፤ የፍትህ መታጣት ባስከተለው ችግር የበረታ ጩኸት የበዛበትና የአቅመ ደካሞች ምሬት ምድሪቱን የሸፈነበት፤ እንዲሁም የተስፋ ጭላንጭልና ብሩህ ጊዜ ለማየት የሚጓጉ ወጣቶች የበረከቱበት ወቅት ላይ ሐዋርያዊ ተልእኮአችሁን ለመፈፀም ይህን ታላቅ የክርስቶስን አደራ የተቀበላችሁ መሆኑን በመገንዘብ በተሰየማችሁበት አህጉረ ስብከት ያለውን የእምነታችንን ተከታይና የሌሎችን ማኅበረሰብ ችግር ለመፍታት ከፍ ያለ ትጋት እንዲኖራችሁ እንጂ እራሳችሁም ችግር እንዳትሆኑና ለችግርም እንዳትጋለጡ የምድርጨው መሆን በጽኑ ይጠበቅባችኋል።

ሀገረ መንግስትን በመመስረት ቀደምት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እናት እንደ መሆኗ መጠን በሀገራችን ኢትዮጵያ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለው የባሕልና የቋንቋ የአኗኗር ልዩነት እንደ ጽጋ በመቁጥር የጋራ ቤታችን የሆነችውን ሀገራችንን ኢትዮጵያን በመንፈሳዊውም ሆነ በማኅበራዊው አኗኗር ለማገልገል በአንድነትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ ተልዕኮ ይዛችሁ ወደ ሕዝባችን መቅረብ ይገባል። በሀገራችን የሚስተዋሉት ጊዜና ወቅት የወለዳቸው የመከራ ቀኖች እንዲያበቁ ዘወትር በጸሎትና በምህላ እግዚአብሔርን በመጠየቅ የምድር ጨውነታችሁን ልታስመሰክሩ ይገባል።

በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ሐዋርያዊ ተልዕኮ ላይ ጊዜና ወቅት አምጥቷቸው ብቅ ብቅ ያሉትን የአንድነት እጦት፤ የሙስና አደጋ ፣ ግላዊ ምኞትና ጥቅምን በሚወዱ አንዳንድ አገልጋይ መሳይ ካህናትና መነኮሳት መከሰት ምክንያት በማኅበረሰቡ ላይ ሰለደረሰውና ስለሚደርሰው ማታለል፤ በሥጋም በነፍስም የተሰቃዩ ወንድሞችና እህቶችን ሕመም የመሸከምና የማከም ጥንካሬን በማምጣት የምድር ጨው መሆናችሁን በአባታዊ አርአያነት ልታሳዩ ይገባል።

ብፁዓን አበው ኤጲስ ቆጶሳት በብፁ ወቅዱስ ፓትርያርክ በሐዋርያዊ አባትነት በተሰየማችሁባቸው አህጉረ ስብከት የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ሁሉ የምድር ጨው ይሆኑ ዘንድ ከተፈለገ ዋነኛው ምስጢር የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ተግባር በግብር መከተል ነው። በአገልግሎት መድረካችንም ላይ የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርትና ተልዕኮ በአርአያነት ስፍራ ካልሰጠነው የእኛ ክብር የእርሱን ቦታ ከወሰደ፣ የቤተክርስቲያን ተልእኮ ስኬት ዋጋ ያጣል። በአሁኑ ወቅት የክብረ ክህነት መቀነስ፣ በነቀፋ መታጅብና ተቀባይነቱ በየጊዜው እየወረደ የፖለቲከኞችና በሚድያ ለሚነግዲ ሽቃጮች ቤተ ክርስቲያኒቱ መጫወቻ የሆነችው ከዚህ የተነሳ ነው።

አደራችሁ ጥብቅና ሰፊ ከሰማይ እስከ ምድር የሚደርስ በመሆኑ ታላቋን ቤተ ክርስቲያንን በሚመጥን መልኩ ተልእኳችሁን በመወጣት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከገባችበት የዘርና የጎሳ አዘቅት እወነተኛ መሰላል ሆናችሁ ለማውጣት የቅዱስ ሲኖዶስ ተጨማሪ ጉልበትና ኃይል እንድትሆኑና እያሳሰብን ለዚህ ክብር በመብቃታችሁ ዝግጅት ክፍሉ ይደልዎ ይደልዎ ይደልዎ በማለት መልካም ምኞቱን ይገልጻል።

መላከ መዊዕ
ቀሲስ ሳሙኤል እሸቱ
የትምህርትና ሥልጠና መምሪያ ኃላፊ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ



ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በክርስቶስ ደም ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ከቅዱሳን ሐዋርያት የወረሰችውን ምዕመናንን የመጠበቅና ወንጌለ መንግሥቱን ለዓለም የማዳረስ እንዲሁም ዶግማዋ እና ቀኖናዋ ሳይፋለስ ጠብቃ በማስ`ጠበቅ የተቀደሰውን ሥርዓተ አምልኮ ከትውልድ ወደ ትውልድ በማሻገር የማይተካ ሚና በመጫወት እስካሁን የደረሰች በቀጣይም ይህንን ሐዋርያዊ ተልዕኮዋንና የክህነት አገልግሎትዋን ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻል ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ኤጲስ ቆጶሳትን እየሾመች መንፈሳዊ አገልግሎቷን ስታከናውን ኖራለች፤ ወደፊትም ትኖራለች።

ይህም በመሆኑ ጥር 14 ቀን 2015 ዓ.ም. በኦሮምያ ክልል በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ በተፈጸመው ሢመት በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የደረሰውን መከራና ፈተና ለማሳለፍ ሲባል ዶግማዋን፣ ቀኖናዋንና ትውፊቷን ባስጠበቀ ሁኔታ ችግሩ በውይይት እንዲፈታ ባደረገችው ያላሰለሰ የሰላም ጥሪ መነሻነት የካቲት 8 ቀን 2015 ዓ.ም. ክቡር የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ በተገኙበት በተደረሰው ስምምነት መሠረት የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ግንቦት 14 ቀን 2015 ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ቀኖናዋን ከስምምነቱ፣ ስምምነቱን ከቀኖናዋ ጋር በማዛመድ በኦሮምያና በደቡብ ክልል ባሉ ክፍት

አህጉረ ስብከት ተመድበው የሚያገለግሉ 9ኝ ኤጲስ ቆጶሳት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንዲሾሙ በወሰነው መሠረት ተሿሚ እጩ ኤጲስ ቆጶሳትን መልምለው የሚያቀርቡ ሰባት ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳትን መሰየሙ ይታወሳል።

ጥሪ መሠረት ከሰኔ 27 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ባደረገው የ2 ቀን ስብሰባ በሁለት ዓበይት አጀንዳዎች ማለትም በእጩ ኤጲስ ቆጶሳት ምርጫና በትግራይ ክልል አህጉረ ስብከት ወቅታዊ ችግር ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ



በዚሁም መሠረት የተሰየሙት አስመራጭ ብፁዓን አበው ሊቃነጳጳሳት ቋሚ ሲኖዶስ አስቀድሞ ባወጣው የእጩ ኤጲስ ቆጶሳት መመልመያ መስፈርት መሠረት ከብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት በጥቆማ ከቀረቡላቸው 75 ቆሞሳት መካከል በትምህርት ዝግጅታቸው፣ በአሠረ ምንኩስናቸው፣ በቋንቋ ችሎታቸውና መንፈሳዊ አገልግሎታቸው መስፈርቱን አሟልተው የተገኙትን 18 እጩ ቆሞሳትን ከነሕይወት ታሪካቸው የተሟላ ሪፖርት ሰኔ 16 ቀን 2015 ዓ.ም. ለቋሚ ሲኖዶስ አቅርበዋል።

ቋሚ ሲኖዶስም የቀረበውን ሪፖርት መነሻ በማድረግ በጉዳዩ ላይ ከተወያየ በኋላ በቀረቡት እጩ ቆሞሳት ላይ ምርጫ እንዲደረግ ለቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ባስተላለፈው የስብሰባ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፏል።

በዚሁም መሠረት፦- ፩ኛ. የእጩ ኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ በተመለከተ፦-

1. ቆሞስ አባ ሣህለማርያም ቶላ

ለምዕራብ አርሲ ሀገረ ስብከት

2. ቆሞስ አባ ወ/ገብርኤል አበ

ለምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት

3. ቆሞስ አባ ጥላሁን ወርቁ

ለምሥራቅ ሐረርጌሀገረ ስብከት

4. ቆሞስ አባ አምደሚካኤል ኃይሌ

ለሆሮ ጉድሩ ሀገረ ስብከት

5. ቆሞስ አባ ኃይለ ማርያም ጌታቸው

ለድሬዳዋ ሀገረ ስብከት

6. ቆሞስ አባ ዘተ/ሃይማኖት ገብሬ

ለምዕራብ ወለጋ ሀገረ ስብከት

7. ቆሞስ አባ አስጢፋኖስ ገብሬ

ለቡኖ በደሌ ሀገረ ስብከት

8. ቆሞስ አባ ክንፈገብርኤል ተ/ማርያም

ለጌዴኦ አማሮና ቡርጂ ሀገረ ስብከት

9. ቆሞስ አባ ስብሐት ለአብ ኃይለማርያም

ለዳውሮ ኮንታ ሀገረ ስብከት

ክርስቲያንንና መላው ሕዝበ ትግራይን በአካል በቦታው ተገኝታ ባለመጠየቋና ባለማጽናናቷ፣ ጦርነቱ ቁሞ በአገር አቀፍ ደረጃ እርቀ ሰላም ከወረደበት ጊዜ ጀምሮ ለደረሰው ጉዳት በቅዱስ ሲኖዶስ የተወሰነውን ሰብአዊ ድጋፍ በውሳኔው መሠረት በወቅቱ ማድረስ ባለመቻሏ፣ በዚሁም የተነሣ በቤተ ክርስቲያኗና በመላው ሕዝበ ትግራይ መካከል ለተፈጠረው ቅሬታና አለመግባባት ቅዱስ ሲኖዶስ ይቅርታ ጠይቋል።



በኤጲስ ቆጶስነት እንዲሾሙ የተመረጡ ሲሆን በዓለ ሢመቱንም በተመለከተ ሐምሌ 9 ቀን 2015 ዓ.ም. እንዲፈጸም ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ አስተላልፏል።

በክልል ትግራይ በተካሄደው ጦርነት ወቅት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊትና ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን እንደመሆኗ መጠን ጦርነቱ እንዲቆም በወቅቱ መግለጫ ባለመስጠቷ፣ በጦርነቱ መካከል ወደ ትግራይ ክልል መግባትና መውጣት በሚቻልበት ወቅትም በክልሉ የሚገኙ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳትን፣ ሊቃውንተ ቤተ

እግዚአብሔር አምላክ ኢትዮጵያንና ሕዝቦችዋን ይባርክ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን!

አባ ማትያስ ቀዳማዊ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

ሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

መልእክተ ቅዱስ ፓትርያርክ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ
አሜን

“ኢይክል ሰብእ ነሢአ ጸጋ ለሊሁ እመ ኢተውህበ ሎቱ እምሰማይ
ከሰማይ ካልተሰጠው በቀር ሰው ራሱ በራሱ ጸጋን ሊቀበል አይችልም” (ዮሐ. 3፥27)



ይህንን ዐረፍተ ነገር የተናገረው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነው ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ነው፤ የዮሐንስ ደቀመዛሙርት ለእሱ የተቈረቈሩ መስሎአቸው ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት በጠየቁት ጊዜ ይህንን መልስ መልሶላቸዋል፤ ቅዱስ ዮሐንስ በዚህ አባባሉ ሰው ያለውን ወይም የሆነውን ከመሆን ባለፈ የሌለውንና ያልሆነውን መሆን እንደማይችል አመልክቶአል፣ ለዮሐንስ የተሰጠው ጸጋ “መንገድ ጠራጊ መሆን” ነው፤ ከዚህ ውጭ ያልተሰጠውን ገንዘብ ሊያደርግ አልሞከረም፤ ምክንያቱም ከወደሰማይ አልተሰጠውምና ነው፣ በመሠረቱ ሰው በሁሉም ነገር ተቀባይ እንጂ ሰጪ አይደለም፣ “ያልተቀበልከው ምን አለህ” የሚለው የቅዱስ መጽሐፍ አስተምህሮም ይህንን ያረጋግጣል፤ የሰዎች ችግር የተሰጣቸውን ጸጋ በውል አለማወቅና ቢያውቁም በተሰጣቸው ጸጋ ለመስራት ፈቃደኞች አለመሆናቸው ነው፤ በዚህም ምክንያት ዕድሜ ልካቸው የሌላውን ጸጋ በመመኘት ሲታክቱ ውጤት አልባ ሆነው ይቀራሉ፤ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚያስተምረን ጸጋን የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ አንድ ሲሆን የሚሰጠው ጸጋ ግን ዓይነቱ ብዙ ነው፤ ለአንዱ የማስተማር፣ ለሌላው የመምከር፣ ለሌላው

ደግሞ ተአምራት የማድረግ ጸጋ ወዘተ ይሰጣል፤ ጸጋዎቹ ለሰው ልጆች እኩል አስፈላጊ እንደሆኑ አውቆ መንፈስ ቅዱስ ለሰው ይሰጣል፤ ሰዎች ግን አንዱ ትንሽ ሌላው ትልቅ ጸጋ እንደሆነ አድርገው በመውሰድ ራሳቸው ግራ ተጋብተው ሌላውን ግራ ያጋባሉ፤ ይህ ዓይነቱ አመለካከት በቤተ ክርስቲያን ቦታ እንዳያገኝ በጽናት መቆም ይገባል። ዛሬ በሐዋርያዊ ቀኖና እና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተመረጡትን ኤጲስ ቆጶሳት ስንሾም ይህንን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ መሠረት አድርገን ነው፤ ኤጲስ ቆጶስ ማለት የምእመናን ላዕላዊ ጠባቂ ወይም አውራ ጠባቂ ማለት ነው፤ ይህ ማለት በተመደበበት ሀገረ ስብከት የመጨረሻው የምእመናን ጠባቂ እረኛ ማለት ነው፣ ኤጲስ ቆጶስ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ምእመናን ላይ በመንፈሳዊ የጥበቃ አገልግሎት የተሾመ ነው፣ ይህም በመሆኑ የሚሊዮኖች ዓይኖች እሱን ይመለከታሉ፣ ትምህርቱን፣ ንጽህናውን፣ ቅድስናውን፣ ትጋቱን፣ ሃይማኖቱን፣ ጸሎቱን፣ ፍቅሩን፣ አመራሩን፣ አኗኗሩን፣ አነጋገሩን፣ በአጠቃላይ ሁለንተናዊ ሕይወቱ ለምእመናን ዓይንና አእምሮ የተጋለጠ ነው፤ ታዲያ ኤጲስ ቆጶሱ አኗኗሩ ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ብቻ የሚመራ ከሆነ ለብዙዎች መዳን መሪና ፈታውራሪ ነው፣ ያ ካልሆነ ደግሞ ለብዙዎች መሰናክል ይሆናል፤ ይህ እንዳይሆን ኤጲስ ቆጶሳት እጅግ መጠንቀቅ አለባቸው። በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ባልተጠበቀና ባልተለመደ ሁኔታ ብቅ ብቅ ሲሉ የሚታዩት ራስን በራስ የመሾም አባዜ መገታት አለባቸው፤ ማንኛውም ችግር በውይይትና በምክክር የተበደለውንም በትክክል በመካስ መፈታት ይገባዋል፤ ከዚህ ውጭ በጥፋት ላይ ጥፋት እየተከሠተ የቤተ ክርስቲያንን ህልውና የሚፈታተን ድርጊት ማቆም አለብን፣ እኛም ሊቃነ ጳጳሳት የምንናገረውንና የምናስተምረውን የምንመራውንም ሕዝብ በውል አውቀን በትክክል መምራትና ማገልገል ይገባናል፣ ችግሩ እየመጣ ያለው ከውጭ ሳይሆን ከኛው ከራሳችን ነው፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ከሁለተኛ ፓትርያርክ አንሥቶ እስካሁን የመጣንበት ጉዞ ሲገመገም አመርቂ አይደለም፤ አካሄዳችን ሁሉ ለፈተና የሚዳርግ ነበረ፤ አሁን ወደ ልባች እንመለስና ቤተ ክርስቲያንንና ቤተ ክርስቲያንን ብቻ ማእከል አድርገን መስራት አለብን፣ ኤጲስ ቆጶሳትን መሾም የጐደለውን ለመሙላት እንጂ የጐደላቸውን ለመሙላት አለመሆኑ ሊሠመርበት ይገባል፣ ስለዚህ በዛሬው ዕለት ለላዕላዊው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የበቃችሁ ኤጲስ ቆጶሳት ከዛሬ ጀምሮ ዘመድ አዝማድን፣ ብሔርና ዘውግን፣ ቤተሰብና ሀብትን ብቻ ሳይሆን ራሳችሁንም እንድትክዱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን፤ አደራም እንላችኋለን፤ ይህንን ብታደርጉ ራሳችሁንም የሚሰማችሁንም ታድናላችሁ፣ እኛም ሐዋርያዊ ጉዞአችሁ የተቃና ይሆን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን፣ እግዚአብሔር እኛንም እንደ ፈቃዱ እንድንመላለስ በከሃሊነቱ ይርዳን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አሜን

አባ ማትያስ ቀዳማዊ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

ሐምሌ ፱ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

“ማእረሩሰ ብዙኅ ወገባሩ ኀዳጥ። ሰአልዎ እንከ ለበዓለ ማእረር ከመ ይወስክ ገባረ ለማእረሩ” ማቴ. ፱፥፴፯

“መከሩስ ብዙ ነው፤ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው። እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደመከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት” ማቴ. 9፥37



አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አልጫ ዓለም ለማጣፈጥ በማስተማር፤ ሕሙማንን በመፈወስ፤ ሙታንን በማንሣት፤ ርኁባንን በመመገብ ለሰው ልጆች ያላደረገው ነገር የለም። ከዚህም በላይና ይህን ሁሉ እያደረገ ማስተዋል ለጐደላቸው እንዲያስተውሉ፤ ርኅራኄ ለሌላቸው ርኅራኄ እንዲኖራቸው ከላይ በተጠቀሰው አምላካዊ ቃሉ መክሯል፤ መመሪያም ሰጥቶአል።

ኀዘኑንም ሲገልጽ “ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው።” ማቴ. 9፥36

ዛሬም በዘመናችን የተጣሉ ተመልካች ያጡ የተበተኑ ሰብሳቢ የሌላቸው ፍቅረ እግዚአብሔርን፤ ፍቅረ ቢፅን የተራቡ መጋቢ የሌላቸው የጠፉ ፈላጊ የሌላቸው የብዙ ብዙ ናቸው። ዋይታቸው ጩኸታቸው በስም ብቻ ጠባቂዎች እረኞች ሰብሳቢዎች የተባልነውን

በዘመኑ ያለነውን ይከሳል፤ ይወቅሳል። ይህም ሁሉ ሆኖ “ጆሮ ዳባ ልበስ” እንዲሉ እኛም ለመስማት ጎላፊነታችንን ለመወጣት በርኀራኄ በፍቅር ለመጠበቅ አልታደልንም። ምክንያቱም ከዓላማችንና ከተልእኮአችን ወጥተን የዓለሙ ጠባይና ማዕበል ቀዛፊና መልሕቅ እንደሌለው መርከብ የጎሊና ዕረፍት ነሥቶ ስለሚያገላታን ነው ለማለት አያጠራጥርም። ነገር ግን ዛሬም አለን ለማለት ብንጥርም ጥቂቶች ነን መከሩ ብዙ ነውና ሠራተኛ ያስፈልጋሉ በሚል ቅዱስ ሲኖዶስ እረኞችን መርጧል፤ ሠይሟል።

የአሁኑን የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫና ሢመት ልዩ የሚያደርገው በ2015 ዓ.ም በወርኃ ጥር መከሩን (ምእመናንን) ምክንያት በማደረግ በቋንቋ በፖለቲካ በዘር ተጠልፈን ለተፈጠረው ችግር በቤተ ክርስቲያን ሕግና ቀኖና ብቻ ሳንወሰን ክቡር ምንስትሩ ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት የተደረገውን ስምምነት ማዕከል አድርጎ የተካሄደ ምርጫና ሢመት መሆኑ ነው። ከዚህም የተነሣ በሕገ ቤተ ክርስቲያንና በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ያልተለመደና እንግዳ ነገር (ደራሽ) በመሆኑ ሊቃውንቱ፤ ካህናቱ በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ለምን? እንዴት? ብሎ ከመጠየቅም አልፎ ጽፈዋል፤ ተችተዋል፤ አባቶችንም ተማፅነዋል።

ይሁን እንጂ ቅዱስ ሲኖዶስ የሊቃውንቱን ጩኸት የሁሉንም ወገኖች ጥሪ በማቃለል ሳይሆን ችግሩ በተፈጠረ ጊዜ የሞት ሰለባ የሆኑ ካህናት፤ ምእመናን ወጣት አዛውንት መከራና ሐዘን ከህሊናችን ሳይወጣ የታሰሩት የተፈናቀሉት የድረሱልኝን ጥሪ በጆሮአችን እየቃጨለ ከሥራ የተፈናቀሉት ተራብን ተጠማን አቤቱታ ሳይቋረጥ ስምምነት ጥሰን በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ብቻ ይሁን ብለን ብንወሰን ወደኋላ ተመልሰን ካህናቱን ምእመናንን ለመከራ አሳልፈን ላለመስጠት ጳጳሳት ሆናችኋል ከተባሉ በኋላ በስምምነቱ መሠረት ያወለቁትን ልብስ ጳጳሳት እንደገና ለብሰው እንዳይሰማሩ ቀኖናን በቀኖና በማስተካከል ሢመተ ኤጲስ ቆጶሳት አጽድቆ ችግሩን መፍታት አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው ብሎ ተቀብሎታል። ይኸም ሆኖ ውጤታማ መሆን ከተቻለ ተመስገን የሚያሰኝ ነው። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያኒቱ ፈተና ተጀመረ እንጂ አልተጠናቀቀም።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆን ሁላችንም መለያየቱን ትተን በአንድነት፤ መተቻቸቱን ትተን በስምምነት በመመካከር አባቶቻችን እና እናቶቻችን አንዲት ቤተ ክርስቲያን እንዳስረከቡን ሁሉ እኛም ለነገው ትውልድ አንዲት ቤተ ክርስቲያን እንድናስረክብ እረኞች ለመንጋው መንጋው ለእረኞ (አባቶች ለምእመናን ምእመናን ለአባቶች) ርኀራኄና ፍቅር ይኑረን።

በሃይማኖታችን ምንጊዜም ከማንም ከምንም ጋር አንደራደር። ይልቁንም አባቶች፤ ሊቃውንት፤ ካህናት፤ እረኛ እንደሌላቸው በጐች ተጨንቀው የሚገኙትን ወገኖቻችን ለማገልገል እንትጋ! በተለየ ሐሳብ ሳይሆን በአንድ ሐሳብ በየቋንቋቸው ለአንዲት እናት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናስተምራቸው፤ ለመንግሥተ ሰማያትም በቅተን እናብቃቸው። “የመከሩን ጌታ ወደመከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት” በተባለው መሠረት እንለምነው።

ምንም እንኳ ከላይ እንደገለጽኩት የአሁኑ ምርጫና ሢመት በምክንያት ቢፈጸምም ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አልሆነምና ሁላችንም እንቀበለው። በዚሁ አጋጣሚ ለመንጋው ጠባቂዎች ትሆኑ ዘንድ የተጠራችሁና የተመረጣችሁ ብፁዓን ኤጲስ ቆጶሳትም የአርቶዶክሳውያን ሁሉ አባቶች ናችሁና መለያየትንና ጥላቻን በማውገዝ አንድነትንና ፍቅርን በማስተማር ጥንታዊት ሐዋርያዊት የሆነችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ጠብቃችሁ እንድታስጠብቋት፤ የጠራችሁና የመረጣችሁ መንፈስ ቅዱስ መክሊቱን ሰጥቶአችኋል። ማትረፍ ማብዛት ከእኛና ከእናንተ ይጠበቃል። የጠራችሁን የመረጣችሁን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፡ : ለዚህ ታላቅ ሐዋርያዊ አገልግሎት በመመረጣችሁ ደስ ብሎናል። እንኳን ደስ አላችሁ በማለት በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ስም መልካም የሥራና የአገልግሎት ዘመን ይሁንላችሁ።

አባ አብርሃም

በኢ/አ/ተ/ቤ/ክ/ የመ/ፓ/ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና

የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

“ዕዳ አለብኝ”

ሮሜ 1፥14



የመንፈሳዊ አገልግሎት ሹመት እንደምድራዊው ሹመት ክብር፣ ጥቅምና ማዕረግ ተስፋ የሚደረግበት ሹመት ሳይሆን ከሰማያዊው አምላክ በአገልጋይ አባቶች ጫነቃ ላይ የተቀመጠ ዕዳ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ለአገልግሎት የተጠራው በእግዚአብሔር ነው። የሐዋ.ሥ.9፥5 የጠራው አምላክም የመንግሥቱን ወንጌል አሸክሞ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በታናሽ እስያና በአውሮፓ እንዲያስተምር ሲልከው የክብር፣ የማዕረግና የጥቅምን ጉዳይ እንዲያስብ አድርጎ ሳይሆን የተጣለበት መንፈሳዊ አደራ ዕዳ እንደሆነ እንዲሰማው በማድረግ ነው። ለዚሁም

ነው ለሮሜ ሰዎች “ላልተማሩም፣ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም ዕዳ አለብኝ” በማለት የተናገረው፡፡ ሮሜ ፩፣14

በዛሬው ዕለት ሚመተ ኤጲስ ቆጶስነት ለተፈጸመላችሁ የቤተክርስቲያን አባቶች ብፁዓን ኤጲስ ቆጶሳት ማስተላለፍ የምፈልገው አባታዊ መልእክት ቢኖር ይኸ እናንተ ሚመቱን የተቀበላችሁበት ወቅት የአገልጋዮች ሸክም የከበደበት ዕዳችንም ከፍተኛ የሆነበት መሆኑን ተረድታችሁ ቤተክርስቲያናችንን የገጠማትን ተደራራቢ ፈተና እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ለማስወገድ ራሳችሁን እንድታዘጋጁ ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያን ላለፉት ጥቂት አሥርት ዓመታት ሲፈትናት የቆየው ከዘርና ከጎሣ ጋር የተያያዘ ፈተና ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ቤተክርስቲያናችንን ሰላም እየነሳት መሆኑ ይታወቃል፡፡ የዛሬ ተሿሚ ኤጲስ ቆጶሳት ይህንን ፈተና ታሳቢ በማድረግ በምትሰማሩበት አህጉረ ስብከት ሁሉ የሚገኙ ምእመናንና የቤተክርስቲያናችን ወዳጆች ሁሉ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚያዘው ከሁሉ ጋር በሰላም መኖር እንዲችሉ ትግታችሁ በማስተማር አባታዊ ኃላፊነታችሁን እንደምትወጡ እምነቴ ጽኑዕ ነው፡፡

ቤተክርስቲያናችን የምትመራው በቅዱሳት መጻሕፍት፤ በቀኖናተ ሐዋርያትና ከእንዚህ በተውጣጣው በሕገ ቤተክርስቲያን መሆኑ ይታወቃል፡፡ የቤተክርስቲያናችን አስተዳደራዊ መዋቅርም ከእነዚህ ሕግጋት የተቀዳ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ መንፈሳዊ አገልግሎታችንን ለማሳለጥ የተሠራውን አስተዳደራዊ መዋቅር ለማፍረስና ቤተክርስቲያናችንን ከፍተኛ ፈተና ላይ ለመጣል በተለያዩ አካላትና መንገዶች ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተገንዝባችሁ የቤተክርስቲያናችንን አስተዳደራዊ መዋቅር አስጠብቃችሁ አገልግሎታችሁን ትፈጽሙ ዘንድ አደራዬን እያስተላለፍኹ በየምትሠማሩበት አህጉረ ስብከት መልካም የአገልግሎት ዘመን እንዲገጥማችሁ የዘወትር ጸሎቴ መሆኑን እገልጻለኹ፡፡

አባ ጴጥሮስ (ዶ/ር)
የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ፀሐፊ
የኔዎርክና አካባቢው ሀገረ ስብከት
ሊቀ ጳጳስ

“ከመ ዘናአምር ንነግር ወበዘርኢነ ሰማዕተ ንከውን”

“የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን!” ዮሐ 3፡11



ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም ተመሥርታ በሐዋርያት ስብከት ታንጻ ለዛሬ ደርሳለች። በዚህ ሂደቷ ውስጥ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ አገልግሎቷን እስከ ዓለም ዳርቻ ለማድረስ ብዙ ፈተናና መከራ ሰማዕትነትን ስትቀበል ቆይታለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዓመታት በእስክንድርያ በቅዱስ ማርቆስ መንበር ሥር ከቆየች በኃላ በብዙ ጥረትና ውጣ ውረድ ከሷ ሥር በመውጣት የራስዋን ቅዱስ ሲኖዶስ በመመሥረት የሀገሩን ቋንቋ፣ ባህልና እሴትን የምያውቁ ተላላቅ አባቶችን መሾም ችላለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የራሷን መንበር ከሰየመች ጊዜ ጀምሮ ብዙ አባቶች በኤጵስ ቆጶስነት ተሹመው የቤተ ክርስቲያኒትዋን ትምህርት እና ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ ብዙ ጥረዋል። በዚህም ለቤተ ክርስቲያናችንም ሆነ ለሀገርቱ ተላላቅ አስተዋጽኦ አበርክቶዋል።

ይሁን እንጂ በቋንቋ የመገልገል ጥያቄ ብዙም ትኩረት ሳያገኝ በመቆየቱ የክርስቶስ በጎች ምዕመናን በስፋት ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለቀው ወጥተዋል። ቅዱስ ሲኖዶስ ይህንን

በመረዳት በዚህ ዓመት በተለየ መልኩ ትልቅ ትኩርት ሰጥቶ ለዓመታት የሰፊውን ሕዝብ ጥያቄ ሆኖ የቆየውን የቋንቋ አገልግሎት ጥያቄ ለመመለስ የሕዝቡን ቋንቋና ባሕል እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤን የሚያውቁና ከአብራኩ የተገኙ ልጆችን ሹመዋል። ለዚህም ደግሞ ካህናትና ምዕመናን በሙሉ ለቅዱስ ሲኖዶስ ትልቅ ምስጋናና ክብር ይኖራቸዋል ብዬ አምናለሁ። እንዲህ ዓይነት ሹመት ከዚህ በፊት የተፈፀመ ቢሆንም ዘንድሮ በተለየ መልኩ የተሰጠው ትኩረትና ውሳኔ በጣም የሚደነቅ በመሆኑና ይህ ውሳኔ ዘመኑን የዋጀና ቤተ ክርስቲያንቱን እያጋጠማት ካሉት ፈተናዎች የሚታደጋት በመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ የሕዝቡን ጥያቄ ለመመለስ የሄደበት ርቀት ቤተ ክርስቲያኒቱ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን መሆኗን ማረጋገጫ ነው።

በመቀጠልም የዛሬ ተሿሚ ኤጲስ ቆጶሳት ዳግሞ ለብዙ ዓመታት በብዙ ውጣውረድ በመራብ በመጠማት ገጠርና ከተማ ሳትሉ የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርትና ዓላማ በሁሉም መስክ ለምዕመናን አቅማችሁ በፈቀደ መጠን አገልግሎት ስትሰጡ ቆይታችኃል።

በአሁኑ ጥሪ ደግሞ ከዚህ በፊት ስታገለግሉ ከነበረው አገልግሎት የበለጠ ማገልገል የሚጠበቅባችሁ መሆኑን የሚሰመርበት ጉዳይ ነው። ያለንበት ዘመን ከቀደሞ ይልቅ ትጋትን የሚጠይቅ፣ ብርቱ ተወዳዳሪዎቻችን የበዙበት፣ የውስጥና የውጭ ፈተና ያየለበት፣ ትውልዱ ከቴክኖሎጂ ጋር የሚፋጠንበት ዘመን በመሆኑ በጣም ትኩረትና ጥንቃቄ የሚፈልግ ዘመኑን ዋጅተን መሥራት ያለብንና የትውልዱን ጥያቄ ለመመለስ ጥረት ማድረግ የሚገባን ወሳኝ ጊዜ በመሆኑ፤ ይህ ጊዜ ትኩረትን የሚሻ፣ ጥበብንና ዕውቀትን የአመራር ብቃትን የሚጠይቅ እንዲሁም የተማረውን የሰው ኃይል በመጠቀም ቤተ ክርስቲያኒቱን ማሻገር ዋና ተልዕኮዎችን ነው።

የዛሬ ተሿሚ አባቶች ወንጌል “እናንተ የዓለም ጨው ናችሁ” ማቴ 5፡13 እንደሚለው፣ ዓለማችን በብዙ መንገድ ፈተና የበዛባትና አልጫ የሆነችውን ዓለም በእግዚአብሔር ቃል በማጣፈጥ፣ አገልግሎት በማጣት ከቤተ ክርስቲያን የወጡትን ምዕመናን ወደ እናት ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲመለሱ ዋና አጀንዳችሁ ልሆን ይገባል፣ ያላመነውን ማሳመን፣ ያመነው በንስሐ ተመልሶ ለክርስቶስ ሥጋና ደም ብቁ እንድሆን በማድረግ፣ የደከመውን በማጽናት፣ የተበተኑትን በመሰብሰብ የአዳም ልጆች የክርስቶስ ሙሽራ ሆነው የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲወርሱ እነርሱን ማዘጋጀት ከእናንተ ይጠበቃል።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች በዐርባና በሰማኒያ ቀናት የሥላሴን ልጅነት ያገኛችሁ ሁላችሁ ዘንድሮ ቅዱስ ሲኖዶስ ለእነኝህ አባቶች የሰጠው የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ታርካዊ ውሳኔና ዘመን ተሻጋሪ የሆነውን የቋንቋ አገልግሎት ጥያቄ የሚመልስ መሆኑን ተረድታችሁ በፍቅርና በአንድነት በመሆን አባቶች የሰጧችሁን መመርያና ምክር በመከተል ከአባቶች ጎን ቆማችሁ የሚያስፈልጋችውን ነገር እንድያደርጉላችሁ ተቀራርቦ መነጋገርና መወያየት ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ ጉዞዋችን ሁሉ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ከሆነ የሚያስፈልገንን ነገር እግዚአብሔር ይሰጠናል፣ በይቅርታና በምህረት እንዲሁም በንፁሕ ልቡና የምንጓዝ ከሆነ የምህረት አምላክ ሁሉንም ነገር እንድናገኝ የምህረት እጁን ይዘረጋልናል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

ሊቀ አእላፍ ቀሲስ በላይ መኮንን

የጠቅላይ ቤተ ክህነት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ

“ከመ ዘናአምር ንነግር ወበዘርኢነ ሰማዕተ ንክውን”

“Kan beeknu ni dubbanna isa argines ragaa baana!.” Mat 3:11

Manni kiristaanaa Dhiiga Kiristoosin hundooftee bu’uura baruumsa duuka bu’ootaan durfamtee, guyyaa har’aa geessee jirti. Adeemsi ishee kana keessatti Iyyarusaalem irraa eegaltee Andaara addunyaa kana guutuu yeroo geessutti qoruumsaafi wareegamummaan heddu ishee qunnamaa tureera.

Manni Kiristaana Ortodoksi Tawaahidoo Itiyoophiyaa bara hedduuf Iskndiriyaa Teessoo Qulqulluu Maariqoos jala erga bara hedduuf turtee booddee adda ba’uun Sinodoosii mataa ishee hundeeffattee abbootii biyya ishee keessatti qooqaafi duudhaa akkasuma aadaa hawaasichaa beekan muuddachuu dandeesserti.

Manni kiristaanaa keenya kun erga teessoo mataa ishee godhattee booddee, Abboonni heddu keessatti muudamani kaayyoofi baruumsa mana kiristaanitti galmaa’an ga’uuf heddu dhama’aa turaniiru. Kanaanis mana kiristaanaa keenyafis ta’ee biyyattiif bu’aa heddu galmeessanii jiru.

Haa ta’u malee qooqa irratti erga dhiyeenyaa xiyyeeffannoo jabaan waan hin turreef hoolonni kiristoos mana kiristaanitti irraa gadi dhiisanii heddumminaan ba’anii jiru. Kana hubachuudhan Qulqulluun Sinodoosii garuu bara kana bifa adda ta’een xiyyeeffannoo guddaa irratti kennee gaafii saba baldhaa waggaa hedduuf ture deebisuuf abbootii qooqa danda’an aadaafi jireenya sabichaa keessatti guddatan muudeera. Kanaaf ammoo Luboonnifi amantoonni galata Guddaa Qulqulluu sinodoosidhaaf qabu jedheen amana. Hojiin akkanaa kana dura turu illee, murtee fi xiyyeeffannoon bara kana itti kennamee baay’ee waayitawaa fi rakkinichaaf hanga ta’e, deebii ta’uu kan danda’u waan ta’eef, irra deebidhaan maqaa koofi maqaa amantootatin Qulqulluu Sinodoosii galateeffachuun barbaada.

Itti aansudhaan abbootin Eephis Qoophoosonni muudamaaf filataman ammoo abbootii saba isaaniif waggaa heddu bu’aa ba’ii heddu keessa baadiyyaafi magaalaa osoo hin jedhin baruumsaa fi kaayyoo mana kiristaanaatti amantoota biraan ga’uuf dhama’aa turtaniidha.

Waamicha Kanaan ammo tajaajila kana dura kennaa turtan caalaa kennuun ka nisin irraa eegamu ta’uun isaa beekamaadha, barri nuti amma keessa jiru isa durii caala jabina kan gaafatu, amantootni biroo

kan itti babaldhatan, teeknolojiin dhaloota kan itti to'achaa jiru waan ta'eef isa duraa caala hojjachuufi gaafii dhalootaa deebisuuf carraaqun yeroo murteessaa ta'ee waan jiruuf, yeroon kun yeroo xiyyeeffannoo guddaadhaan, ogummaafi beekumsan durfamanii dhaloota barate hirmaachisuudhan mana kiristaanitti dhalootaf dabarsuun ergama keenya isa jalqabaati.

Egaa abboonni muudamtoonni akkuma wangeelli "Isin soogidda biyya lafaati" Mat 5:13 jedhu, addunyaa ishee yeroo kana karaa hedduun hadhooftuu taatee jirtu kana jecha waaqayyootin mi'eessudhaan, isa mufatee jiru, ofitti dhjiyeessitanii goorsuudhan, isa hin amanne, amansiisudhaan; isa amane, gaabbidhaan deebi'ee fooniifi dhiiga kiristoos akka qaqqabu taasisuudhan; isa laafee, jabeessudhaan; warra adda adda bittiman, walitti qabuudhaan dhalli namaa hundi misirroo kiristoos ta'ee mootummaa Waaqayyoo akka dhaaluf isaan qopheessun keessumatto uummata oromoo fi ummata kibba itiyoophiyaa jiran mufatanii mana kiristaanatii ba'an kana akka isaan mann kiristaanitti kan kooti jedhanii gammachuun keessaa deddeebi'an taasisuun isin irraa eegama.

Dhuma irratti hordoftootni amantaa Ortodoksi Tawaahidoo Itiyoophiyaa guyyaa afurtaamaafi saddeettamatti cuuphamtanii mucummaa sillaasee kan fudhattan hundi keessan muudama Qulqulluun Siinodoosii abbootii kanaaf kenne kun murtee seena qabeessafi gaafii bara hedduuf tureef deebii ta'uu isaa hubattanii jaalalaafi tokkummaadhan gorsaafi qajeelfama abbootii keessanii fudhachuudhan abbootii kana cinaa dhaabbattanii waan isin barbaachisu hunda akka isinii godhaniif walitti dhiyaattanii hojjachuufi mari'achuun ni barbaachisa.

Walumaagalatti adeemsi keenya guutuun adeemsa foonii osoo hin taane afuuran yoo ta'e waan nu barbaachisu hunda waaqayyo nuuf kenna. Dhiifamaafi araaran akkasuma laphee qulqulluudhan yoo deemne waaqni dhiifamaa waa hunda akka argannuuf harka isaa dhiifamaa nuuf diriirsa.


Galanni Waaqayyoof haa ta'u.

H/K/L/Balaay Mokonnin

I/A/Hoogganaa Mana Lubummaa waliigalaa

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት አንብሮተ እድ፥ በብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ተራዳኢነት ሐምሌ ፱ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም. የተሾሙ ኤጲስቆጶሳት አጭር ግለ ታሪክ።

፲ኛ) አባ ሣህለ ማርያም ቶላ ግምቢ



አባ ደጀኔ ቶላ ግምቢ ከአባታቸው ከአቶ ቶላ ግምቢ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ጅፋሬ ጉደታ በሰሜን ሸዋ ሰላሌ አውራጃ ውጫሌ ወረዳ በአንጐዬ ጎርዳሜ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ አጥቢያ በ1968 ዓ.ም. ተወለዱ።

የትምህርት ዝግጅት፦

- **የቃል ትምህርትና መዝሙረ ዳዊት፦** ከየኔታ ተከስተ፥

- **መዝገብ ቅዳሴ፦** ከየኔታ ጎሐጽባሕ፥ በደብረ ቅዱስ ደብረ ጽጌ ገዳም፤ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመመለስ ከየኔታ ነቅዓ ጥበብ መዝገብ ቅዳሴን በመከለስ በሚገባ ቀጽለዋል፥

- **ቅኔ፦** ከየኔታ ጎይለ ሚካኤል በደብረ ሊባኖስ ገዳም፥ በድጋሚ ከታላቁና ዕውቁ ሊቅ ከየኔታ ምሕረት ዘንድ ተቀኝተዋል፥

- **ብሉይ ኪዳን፦** ከታላቁ መምህር ከየኔታ ጥበቡ ዘንድ በመምህርነት ደረጃ ተመርቀዋል።

መንፈሳዊ አገልግሎት፦

- በሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ተንቀሳቃሽ ሰባኬ ወንጌል በመሆን በኦሮምኛ ቋንቋ ሲያስተምሩ ቆይተዋል፥

- በለገጣፎ ምስካበ ቅዱሳና አቡነ ኪሮስ ገዳም፥ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በቦሌ ለሚ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፥ በየካ አባዶ ቅዱስ ሚካኤልና በቦሌ ቡልቡላ አቡነ ሳሙኤል አብያተ ክርስቲያናት በአስተዳዳሪነት አገልግለዋል፥

- የሰላሌ ሀገረ ስብከት የስብከተ ወንጌል ክፍል ኃላፊ እና የመካነ ሰማዕት አቡነ ጴጥሮስ ገዳም አስተዳዳሪ በመሆን ተልእኮ ፈጽመዋል፥

- ወደ ሰሜን አሜሪካ በማቅናት በብፁዕ አቡነ ገብርኤል በተመሠረተችው የማኅበረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን በስብከተ ወንጌልና በአስተዳዳሪነት አገልግለዋል።

መዓርገ ክህነት፦

- **ዲቁና፦** ከአቡነ ባስልዮስ፥

- **ምንኩስና፦** በደብረ ሊባኖስ ገዳም፥

- **ቅስና እና ቁምስና፦** ከብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ የሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ተቀብለዋል።

የቋንቋ ችሎታ፦

አሮምኛና፥ አማርኛ፥ እንግሊዝኛ

2ኛ) አባ ወ/ገብርኤል አበበ ጨመዳ



አባ ወልደ ገብርኤል አበበ ከአባታቸው ከአቶ አበበ ጨመዳ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ በቀሉ ዳባ በ1971 ዓ.ም. በሆረ ጉድሩ ወለጋ ዞን ዐባይ ጮመን ወረዳ ፊንጫአ ስኳር ፋብሪካ (7ኛ ክምፕ) ተወለዱ።

የትምህርት ዝግጅት፤

- **የቃል ትምህርት፥ ንባብ፥ ውዳሴ ማርያምና ዜማ፦** ከየኔታ ደቂቅ፤ ምሥራቅ ጎጃም ባሶ ሊበን ወረዳ ድንጓም ማርያም፥

- **ቅኔ፦** ከየኔታ መንክር፥ ደብረ ማርቆስ፤ ከየኔታ ክነፈርግብ፥ አንበር ከተማ፥

- **ቅዳሴና ሰዓታት፦** ከመምህር አንዱዓለም፤ ምሥራቅ ጎጃም ባሶ ሊበን ወረዳ አንጅም ኪዳነ ምሕረት፥

- **ዲፕሎማ፦** በነገረ መልኮት ትምህርት፤ ከሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ በእጅግ ከፍተኛ መዓርግ፥

- የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን የኮርስ ትምህርቶች፥

- በዘመናዊ ትምህርት በኩልም እስከ 12ኛ ክፍል ተምረዋል።

መንፈሳዊ አገልግሎት፤

- በዲቁና፥ በቅስና፥ በግብዝና እና በስብከተ ወንጌል አገልግሎት በፊንጭኣ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፤ ከ1992-1998 ዓ.ም.

- በደብር አስተዳዳሪነት፦ የአርጆ ጉደቱ ደብረ ስብሐት በኣታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን፥ የኮምቦልቻ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፥ የሥሬ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፥

- የነቀምቴ ርእሰ አድባራት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን እና በተለያዩ አድባራት በደብር አስተዳዳሪነት አገልግለዋል።

- በሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅነት፦ የምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ፤ ከኅዳር 2010 ዓ.ም. ጀምሮ

መዓርገ ክህነት፤

- ዲቁና፡- ከብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፥ ደብረ ማርቆስ፥ 1989 ዓ.ም.

- ምንኩስና፡- በፊንጫኣ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፤ 1992 ዓ.ም.

- ቅስና፡-. ከብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፤ 1993 ዓ.ም.

- ቁምስና፡- ከብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፤ ደብረ ማርቆስ፤ 1996 ዓ.ም.

የቋንቋ ችሎታ፤

አሮምኛና አማርኛ

3ኛ) ሊቀ ጉባኤ ቆሞስ አባ ጥላሁን ወርቁ ደሳለኝ



ሊቀ ጉባኤ ቆሞስ አባ ጥላሁን ወርቁ ከአባታቸው ከአቶ ወርቁ ደሳለኝ (ኋላ አባ ወርቁ) እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ጀማነሽ በሼ (ኋላ እማሆይ ጀማነሽ) በ1972 ዓ.ም. በሰላሌ አውራጃ በደብረ ሊባኖስ ወረዳ በባቡ ቀበሌ ልዩ ስሙ ሠምሮ ጊዮርጊስ በሚባል ቦታ ተወለዱ።

የትምህርት ዝግጅት፤

- የቃል ትምህርትና ንባብ፡- ከየኔታ ተከስተ ካሣ፥

- ከግብረ ዲቁና እስከ መዝገብ ቅዳሴ፡- ከየኔታ ነቅዐ ጥበብ ደምሴ፥

- ቅኔ፡- ከየኔታ ምሕረተ ሥላሴ ደሳለኝ፥

- ሐዲሳት ትርጓሜ፡- ከየኔታ ዘተክለ ሃይማኖት ወልደ ጊዮርጊስ (መጋቤ ሐዲሳት) በመምህርነት ተመርቀዋል።

- በዘመናዊ ትምህርት በኩልም እስከ 8ኛ ክፍል ተምረዋል።

መንፈሳዊ አገልግሎት፤

- በአርድእትነት፥ በሰዓታት አገልግሎት፥ በሰባኬ ወንጌልነት፥ በሰሞነኛነት በሊቀ ዲቁና፥ ከ1997 እስከ 2007 ዓ.ም.

- በተደራቢነት የአብነት ት/ቤቶች ዋና ጸሐፊ፥ ከ2003 እስከ 2006 ዓ.ም.

- በገዳም ሊቀ ጉባኤነት ከ2006-2014 ዓ.ም.

- በገዳም ትምህርት ክፍል የክፍሉ ኃላፊዎችና መምህራን ሰብሳቢ፥ ከ2010 እስከ 2014 ዓ.ም.

መዓርገ ክህነት፤

- ዲቁና፡- ከብፁዕ አቡነ ቶማስ በወቅቱ የሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ 1987 ዓ.ም።

- ምንኩስና፡- ደብረ ሊባኖስ አንድነት ገዳም፤ 2012 ዓ.ም.

- **ቅስና፡-** ከብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ የሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ 2012 ዓ.ም.

- **ቁምስና፡-** ከብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የቦረና፣ ጉጂና ሊበን አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ 2014 ዓ.ም.

የቋንቋ ችሎታ፤

አሮምኛና አማርኛ

4ኛ) ቆሞስ አባ ዓምደ ሚካኤል ጎይሌ ደገፋ



ቆሞስ አባ ዓምደ ሚካኤል ጎይሌ ከአባታቸው ከቀሲስ ጎይሌ ደገፋ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ በቀሉ ገብሬ በ1975 ዓ.ም. በአርሲ ዞን ሂጦሳ ወረዳ ቦሩ ሌንጫ ቀበሌ ልዩ ቦታው ጉለሌ ሂዱቢሮ ተወለዱ።

የትምህርት ዝግጅት፤

- **የቃል ትምህርት፡-** ከመምህር ሳሙኤል ታደሰ፥ በትውልድ አካባቢ ሌንጫ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፥ በተጨማሪ ከመምህር ተከስተ ብርሃን በደብረ ሊባኖስ ገዳም፥

- **ዜማ፡-** ከመምህር ልሳነ ወርቅ፥ በአዲስ አበባ ላፍቶ ደብረ ትጉሃን ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፥ ከመምህር መርዓዊ ሳሕለ ሚካኤል፥ በደብረ ሊባኖስ አንድድነት ገዳም፥

- **ሰዓታት ዘሌሊትና መዝገብ ቅዳሴ ዘደብረ ዐባይ፡-** በቅድሚያ ከመምህር ነቅዓ ጥበብ፥ በደብረ ሊባኖስ አንድነት ገዳም፥ ቀጥሎ ከነ አንቀጹ በማስመስከር ከመምህር ታደሰ፥ በፍቼ ደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፥

- **ቅኔ፡-** ከመጋቤ ምሥጢር ክንፈ ሚካኤል በደብረ ሊባኖስ አንድነት ገዳም፥ በተጨማሪ ከመጋቤ ምሥጢር ኢያሱ ገብረ አልፋ በአዲስ አበባ ምስካየ ኅዙናን መድኀኔ ዓለም ገዳም፥

- **መጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ፡-** ለአንድ ዓመት በታእካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም፥ በማስመስከር ከመጋቤ ሐዲስ ወልደ ጊዮርጊስ ጸጋው በአዲስ አበባ ምስካየ ኅዙናን መድኀኔ ዓለም ገዳም፥

- መጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ፡- በማስመስከር ከመጋቤ ብሉይ ቀለመ ወርቅ አቡኔ በአዲስ አበባ ምስካየ ኅዙናን መድኀኔ ዓለም ገዳም ትምህርታቸውን ተከታትለው አጠናቀዋል።

- በዘመናዊ ትምህርት ረገድም የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ምስካየ ኅዙናን መድኀኔ ዓለም ገዳም ተከታትለዋል።

የሙያ ደረጃ፤

የመዝገበ ቅዳሴ፥ የመጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ፥ የመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ መምህር እንዲሁም የምልክት ቋንቋ መምህር።

መዓርገ ክህነት፤

- **ዲቁና፡-** በ1990 ዓ.ም. ከብፁዕ አቡነ ናትናኤል የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፥ በአሶሳ ደብረ ጽላልሽ ቅድስት ማርያም ገዳም።

- **ምንኩስና፡-** በ2003 ዓ.ም. በደብረ ሊባኖስ ገዳም፥

- **ቅስና፡-** በ2003 ዓ.ም. ከብፁዕ አቡነ ሰላማ የአክሱም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በአዲስ አባባ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ግቢ፥

- ቁምስና፡- በ2007 ዓ.ም. ከብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፥ በወለቴ ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀብለዋል።

መንፈሳዊ አገልግሎት፤

- **በዲቁና ቀዳሽነት፡-** ከ1990-1993 ዓ.ም. በአርሲ ሀገረ ስብከት ሊንጫ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፥

- **በአንጣፊነት፥** በቁልፍ ያዥነት ከ2002-2006 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ምስካየ ኀዙናን መድኀኔ ዓለም ገዳም፥

- በሰዓታት ቋሚነት፥ በቅስና ቀዳሽነት፥ በሰባኬ ወንጌልነት ከ2007-2015 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ምስካየ ኀዙናን መድኀኔ ዓለም ገዳም፥ በተደራቢነት በአርሲ ሀገረ ስብከት የሄጦሳ ወረዳ ሌንጫ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል፥ የጉለሌ ሐዲ ቢሮ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስና የጉለሌ ቦሩ ወዴቻ ምሥራቀ ፀሓይ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ወበኣታ ለማርያም አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪ በመሆን አገልግለዋል።

- በአርሲ ሀገረ ስብከት የሄጦሳ ወረዳ ሌንጫ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል፥ የጉለሌ ሐዲ ቢሮ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስንስ የጉለሌ ቦሩ ወዴቻ ምሥራቀ ፀሓይ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ወበኣታ ለማርያም አብያተ ክርስቲያናት ምሥረታና ግንባታ እንዲሁም በሌንጫ እና በጉለሌ ቦሩ ወዴቻ መካከል ያለውን ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት የሚያገናኘው መንገድ ግንባታ ሰፊ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

የቋንቋ ችሎታ፡-

- አሮምኛ፥ አማርኛ፥ ግእዝ፥ የምልክት ቋንቋ።

5ኛ) ቆሞስ አባ ኀይለ ማርያም ጌታቸው ዘሊቦ



ቆሞስ አባ ኀይለ ማርያም ጌታቸው ከአባታቸው ከአቶ ጌታቸው ዘሊቦ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ

አርፋሳ ነሞ ምሥራቅ ሸዋ ሊበን ጨቃላ አዱላላ ወረዳ ወንበር ዳኒሳ ቀበሌ ልዩ ስሙ ዜሮ አንድ በ1977 ዓ.ም. ተወለዱ።

የትምህርት ዝግጅት፦

- **የቃል ትምህርት፦** ከመምህር (የኔታ) አባ ገብረ ማርያም ወልደ ሥላሴ፥ በወንበር ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፥

- **ዜማ፦** ከመምህር ይበልጣል፥ በደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አንድነት ገዳም፥

- **ሰዓታት ዘሌሊትና መዝገብ ቅዳሴ ዘደብረ ዐባይ ከነአንቀጹ፦** ከመምህር አባ ዲበ ኩሉ ወልደ ጊዮርጊስ፥ በደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አንድነት ገዳም፤ በድጋሚ በማስመስከር ከመምህር መልአከ ስብሐት አባ ኅይለ ሥላሴ በደብር ዐባይ ገዳም።

- **ቅኔ፦** ከመምህር መዝገቡ፥ በደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አንድነት ገዳም፥

- **የመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ፦** ከመምህር አባ ወልደ ጊዮርጊስ ጸጋው፥ በምስካየ ኅዙናን መድኀኔ ዓለም ገዳም።

- **የነኛ ደረጃ ትምህርት፦** በወንበር ዲንሳ ዜሮ አንድ፥ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ አንድነት አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች፥ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት፦ አዲስ አበባ ልቤ ፋና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተከታትለዋል።

ከፍተኛ ትምህርት፦

- በነገረ መለኮት ትምህርት ዲፕሎማ፤ ቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርስቲ፥

- በሥራ አመራር ትምህርት ዲግሪ፤ አድማስ ዩኒቨርስቲ፥

ሙያዊ ዕውቀት፦

- የሐዲሳት ትርጓሜ እና የመዝገብ ቅዳሴ መምህር።

መንፈሳዊ አገልግሎት፤

- **በዲቁና ቀዳሽነት፥** ምሥራቅ ሸዋ ሊበን ጨቃላ አዱላላ ወረዳ ወንበር ዳኒሳ ቀበሌ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፤ ከ1993-1997 ዓ.ም.፤ በደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አንድነት ገዳም 1997-2000 ዓ.ም.

- **በቅስና ቀዳሽነት፥** ምሥራቅ ሸዋ ሊበን ጨቃላ አዱላላ ወረዳ ወንበር ዳኒሳ ቀበሌ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፤ ከ2000-2004 ዓ.ም.፥

- **በቅስና ቀዳሽነትና በግብዝና፥** ሐዋሳ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ከ2004-2007 ዓ.ም.

- **በቅስና ቀዳሽነት፥** ሐዋሳ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም፤ 2007-2010፥

- **በአስተዳዳሪነት፥** በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ቤተ መንግሥት ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን፥ ከ2010 ጀምሮ።

መዓርገ ክህነት፦

- **ዲቁና፦** ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ ደብረ ዘይት ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን፥

- **ምንኩስና፦** በደብረ ሊባኖስ አንድነት ገዳም፤ 1999ዓ.ም.፥

- **ቅስና፦** ከብፁዕ አቡነ ገብርኤል የሲዳማ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ ሐዋሳ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም፥ 2000 ዓ.ም.፥

- **ቁምስና፦** ከብፁዕ አቡነ ገብርኤል

የሲዳማ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ ሐዋሳ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም፥ 2009 ዓ.ም. ተቀብለዋል።

የቋንቋ ችሎታ፡-

አሮምኛ፥ አማርኛ፥ ግእዝ፥ እንግሊዝኛ።

6) አባ ዘተክለ ሃይማኖት ገብሬ ደረሶ



አባ ዘተክለ ሃይማኖት ገብሬ ከአባታቸው ከአቶ ገብሬ ደረሶ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ አበባዬ በ1970 ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ ሰላሌ በድሬ ጅቦ ጉረኔ ተወለዱ።

የትምህርት ዝግጅት፤

የአብነት ትምህርት፡-

- **ቃል ትምህርትና ንባብ፡-** ከመምህር ኢያሱ ገብረአልፋ፤ ደብረ ሊባኖስ ገዳም፥

- **ዜማ፡-** ከውዳሴ ማርያም እስከ ምዕራፍ ከመምህር መኮንን፤ ደብረ ሊባኖስ ገዳም፥

- **መዝገብ ቅዳሴ፡-** ከመምህር ነቅዐ ጥበብ፤ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመምህርነት

- **ቅኔ ከነአገባቡ፡-** ከመምህር አበበ፤ ስሬ መድኀኔ ዓለም ጉባኤ ቤት፤ በመቀጠልም ከመምህር ንቡር፤ ከመምህር ክንፈ ሚካኤል፤ ከመምህር ምሕረት፤ ደብረ ሊባኖስ ገዳም፥

- **ብሉያትና ሐዲሳት ትርጓሜ፡-** ከየኔታ ጥበቡ፤ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ተምረው በመምህነት አስመስክረዋል።

ዘመናዊ ትምህርት

- አንደኛና የሁለተኛ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል፥

- **ዲፕሎማ፡-** በሰው ኀይል አስተዳደር፥ ጌጅ ኮሌጅ፥ አዲስ አበባ

- **ዲፕሎማ፡-** በቲኦሎጂ፥ ስቴፋን ፕላትስ ቲኦሎጂካል ኮሌ፤ አስትሪያ፥ ቬ

- **ዲፕሎማ፡-** በዶች ቋንቋ፤ ኤቢሲ የቋንቋ ት/ቤት፤ አስትሪያ፥ ቬና ተምረዋል።

መንፈሳዊ አገልግሎት፤

- **በዲቁና፡-** ፈንታሌ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፥ ኮራ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን።

- **በሰዓታት ቋሚነት፡-** ደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ገዳም፥

- **በሰባኪነት፡-** በአፋን ኦሮምና በአማርኛ ቋንቋ፤ ሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት፥

- **በመጽሐፍ መምህርነት፥** ድሬዳዋ ደ/ም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፥

- **በስብከተ ወንጌልና ትርጓሜያትን በማሄድ፡-** ደ/ም ጻድቃኔ ማርያም ገዳም፥

- **በመምህርነት፡-** መቐሌ ቅዱስ ፍሬምናጦስ ኮሌጅ፥

- **በስብከተ ወንጌል ኃላፊነት፥** ወይብላ ቅድስት ማርያም ካቴድራል፥ አየር ጤና አንቀጸ ብርሃን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል፥ ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን፥ ደብረ ገሊላ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን፥ አዲስ አበባ፥

- **በደብር አስተዳዳሪነት፡-** ደብረ ሲና ቅድስት ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን፤አስትሪያ፥ ቬና አገልግለዋል።

መዓርገ ክህነት፤

- **ዲቁና፡-** ከብፁዕ አቡነ ኤፍሬም፥

- **ምንኩስና፡-** በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም፥ 1997 ዓ.ም.

- **ቅስና፡-**. ከብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ፥ 1998 ዓ.ም.

- **ቁምስና፡-** ከብፁዕ አቡነ ማቴዎስ፥ 2003 ዓ.ም. ተቀብለዋል።

የቋንቋ ችሎታ፤

- አሮምኛና አማርኛ አፍ መፍቻ
- እንግሊዝኛ፥ ዶች

7ኛ) ቆሞስ አባ እስጢፋኖስ ገብሬ ዘውዴ



ቆሞስ አባ እስጢፋኖስ ገብሬ ዘውዴ ከአባታቸው ከአቶ ገብሬ ዘውዴና ከእናታቸው ከወ/ሮ ሀጠዴ ገመዳ ሰሜን ሸዋ ሰላሌ አቢቹና ኛአ ወረዳ አደሬ ጮሌ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኩሊዮ ከተሰኘው ቦታ በ1974 ዓ.ም. ተወለዱ።

የትምህርት ዝግጅት፡-

- **ፊደል ቆጠራና ንባብ፡-** ከመምህር ዓለሙ ወተሬ፥ ወልቂጤ ደብረ ሳሕል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፥

- **የቃል ትምህርትና ግብረ ዲቁና፡-** ከመምህር ክብረ፥ አቢቹና ኛአ ወረዳ አደሬ ጮሌ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኩሊዮ በዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን፥

- **ዜማ፡-** ከመምህር አምዴ፥ እቲዛ ደብረ

ጽላልሽ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም፥

- **አቋቋም፡-** ከመምህር ሊቀ መዘምራን ደምሴ፤ እቲሣ ደብረ ጽላላሽ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም፥

- **ሰዓታት ዘሌሊትና መዝገብ ቅዳሴ ዘደብረ ዐባይ ከነአንቀጹ፡-** ከመምህር አእመረ ብዙነህ፤ እቲሣ ደብረ ጽላልሽ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም፥ በድጋሚ በማስመስከር ከመምህር መጋቤ ስብሐት አባ ጎይለ ሥላሴ፤ ደብረ ዐባይ አቡነ ሳሙኤል ገዳም፥

- **ቅኔ ከነአገባቡ፡-** ከመምህር ፍቅረ ዮሐንስ፤ እቲሳ ደብረ ጽላልሽ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም፥ በድጋሚ ከመምህር ሳሙኤል፤ ምድረ ከብድ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አንድነት ገዳም፥

- **የባሕረ ሐሳብ ትምህርት፡-** ከመምህር ልሳኑ፤ ደብረ ጽጌ ቅድስት ማርያም አንድነት ገዳም፥

- **የመጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ፡-** ሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ስድስተኛ ዓመት ድረስ ተምረዋል።

- ዘመናዊ ትምህርት እስከ 7ኛ ክፍል ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አበቦች ፍሬ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ተከታትለዋል።

ሙያዊ ዕውቀት፡-

የቅዳሴ መምህር።

መንፈሳዊ አገልግሎት፡-

- **በዲቁና ቀዳሽነት፡-** በእቲሣ ደብረ ጽላልሽ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም፤ 1989-1996 ዓ.ም.፥

- **በቅስና ቀዳሽነት፡-** በእቲሣ ደብረ ጽላልሽ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም፤ 1997-2001 ዓ.ም.፥

- **በግብዝና፡-** በምድረ ከብድ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አንድነት ገዳም፤ 2002-2004 ዓ.ም.

- **በአብነት መምህርነት፡-** በሰሜን ሰዋ ሀገረ ስብከት በለገጣፎ ዳሌ ደንበል ደብረ ሲና ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን፤ 2004-2005 ዓ.ም.፤ በባሌ ጎባ ሀገረ ስብከ መካነ ሕይወት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም፤ 2006፥

በባሌ ጎባ ሀገረ ስብከት በሀገረ ስብከቱ አዳሪ ት/ቤት፤ 2006-2010 ዓ.ም. አገልግለዋል።

መዓርገ ክህነት፡-

- **ዲቁና፡-** ከብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ፤ 1988 ዓ.ም.፥

- **ምንኩስና፡-** በእቲሣ ደብረ ጽላልሽ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም፤1996 ዓ.ም.፥

- **ቅስና፡-** ከብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ግቢ ውስጥ፥ 1996 ዓ.ም.፥

- **ቁምስና፡-** ከብፁዕ አቡነ ገሪማ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤትና የውጭ ጉዳይ የበላይ ኃላፊ፤ 1999 ዓ.ም. ተቀብለዋል።

የቋንቋ ችሎታ፡-

አሮምኛ አማርኛ፥ ግእዝ።

8ኛ) መልአከ ምሕረት ቆሞስ አባ ክንፈ ገብርኤል ተ/ማርያም ዴሌቦ



መልአከ ምሕረት ቆሞስ አባ ክንፈ ገብርኤል ተ/ማርያም ከአባታቸው ከአቶ ተክለ ማርያም ዴሌቦና ከእናታቸው ከወ/ሮ ጽጌ ጸጋ በሲዳማ ክልል በአርቤጎና ወረዳ በ1965 ዓ.ም. ተወለዱ።

የትምህርት ዝግጅት፤

የአብነት ትምህርት

- **ንባብ፦** ከመምህር የኔታ አስረስ፣ ይርጋዓለም ደብረ መድኀኒ ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን፣

- **ግብረ ዲቁና፦** ከየኔታ መዘምር መንግሥቱ፣ ምዕራብ ሸዋ አድአ በርጋ ደብረ ጽሙና አቡነ ተክለ ሐዋርያት አንድነት ገዳም።

- **ቅዳሴ ምስክር፦** ከመጋቤ ስብሐት የኔታ ጎሃጽባሕ ላእከ፣ ደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም፣

- **ቅኔ፦** ከመምህር የኔታ ገብረ ሕይወት ፈንታሁን፣ ደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም፣

- **ባሕረ ሐሳብ፦** ከሊቀ ሊቃውንት የኔታ ገ/ሕይወት

የሥነ መለኮት ትምህርት

- **የመጀመሪያ ዲግሪ፦** ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ በነገረ መለኮት ትምህርት፣ 1999 ዓ.ም.፤ አዲስ አበባ

- **ዲፕሎማ፦** ከቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ በነገረ መለኮት ትምህርት፤ 1997 ዓ.ም.፤ መቐሌ

ከፍተኛ ትምህርት

- **የማስተርስ ዲግሪ፦** ከኒውዚላንድ አታጎ ዩኒቨርስቲ (Master of Faith (based) Leadership and Management)

- **የመጀመሪያ ዲግሪ፦** በሕዝብ አስተዳደርና ልማት አመራር፤ አ/አ ዩኒቨርስቲ፤ 2005 ዓ.ም.

- **የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት፦** በኒውዚላንድ መሥፈርት መመዘኛ የከፍተኛ ክህሎት ሽልማት፤ 2011 ዓ.ም.

መንፈሳዊ አገልግሎት፤

- **በሊቀ ካህናትነት፦** በምሥራቅ አውስትራሊያና ኒውዚላንድ አህጉረ ስብከት በኒውዚላንድ ሀገር ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ሊቀ ካህናት በመሆን ከታኅሣሥ 2011 ዓ.ም. ጀምሮ፣

- **በአስተዳዳሪነት፦** በምሥራቅ አውስትራልያና ኒውዚላንድ አህጉረ ስብከት የደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ከመጋቢት 2006 ዓ.ም. ጀምሮ፣

- **በሬጅስትራር ኃላፊነት፦** ለአንድ ዓመት ያህል የሰዋስወ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ፥

- **በማስተማር ሥራ፦** በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዴ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በማስተማር፥ በጥናትና ምርመር ሥራ ከማገልገል ባሻገር ለኮሌጁ የማስተማሪያ መጻሕፍትን በማዘጋጀት፥ ከግንቦት 2003 እስከ መጋቢት 2006፥

- **በስብከተ ወንጌል፦** የሱሉልታ ወረዳ ቤተ ክህነት ስብከተ ወንጌል አገልግሎት በመሆን ከ1997-1999 ዓ.ም.፤ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ስብከተ ወንጌል አገልግሎት በመሆን ከታኅሣሥ 1996 እስከ መጋቢት 2006 ዓ.ም.፥

- **በዋና ጸሐፊነት፦** በደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም ከ1992 እስከ 1995 ዓ.ም.፥

- **ከአርድእትነተ እስከ መጋቢነት፦** በደብረ ጽሙና አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንድነት ገዳም 1985-1991 ዓ.ም. አገልግለዋል።

መዓርገ ክህነት፦

- **ዲቁና፦** ከብፁዕ አቡነ ገብርኤል፥ በወቅቱ የምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ 1979 ዓ.ም.

- **ምንኩስና፦** ከአበምኔት ቆሞስ አባ ወልደ ዮሐንስ፥ በምዕራብ ሸዋ ደብረ ጽሙና አቡነ ተክለ ሐዋያት አንድነት ገዳም አድአ በርጋ ወረዳ አሎንኮሜ፤ 1986 ዓ.ም.

- **ቅስና፦** ከብፁዕ አቡነ ገብርኤል፥ በወቅቱ የምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ 1989 ዓ.ም.

- **ቁምስና፦** ከብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የደቡብ ምዕራብ ሸዋና የኬንያና ኡጋንዳ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ 2006 ዓ.ም. ተቀብለዋል።

የቋንቋ ችሎታ፦

ሲዳምኛና ጌዲኦኛ (አፍመፍቻ)፥

አማርኛ፥ አፋን ኦሮሞ፥ እንግሊዝኛ፥ ትግርኛ።

9ኛ) አባ ስብሐት ለአብ ጎይለ ማርያም አንጆጆ



አባ ስብሐት ለአብ ጎይለ ማርያም ከአባታቸው ከአቶ ጎይለ ማርያም እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ዓመተ ማርያም ደጀኔ በ1968 ዓ.ም. በከምባታ ጠምባሮ ዞን ዋለና ቅዱስ ሚካኤል ቀበሌ ተወለዱ።

የትምህርት ዝግጅት፤

- **የቃል ትምህርትና ንባብ፦** ከመርጌታ ተክሌ ዳዊት እና ከአባ ገብረ መድኅን፥

- **ግብረ ዲቁና፦** ከአባ ኤልያስ

- **መዝገብ ቅዳሴ፦** ከአባ ወልደ ገብርኤል፥ ከመምህር አብርሃምና ከመምህር ትጉህ (አሁን አባ ዘካርያስ)፥ በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም፥

- **ጸዋትወ ዜማ፦** ከመምህር ነቅዓ ጥበብ፥ በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም፥

- **ቅኔ፦** ከመጋቤ ሐዲስ እሸቱ አለማየሁ፥ ከመምህር አውላቸው እና ሊቀ ጉባኤ አባ ተክለ ሃይማኖት፥

- **ሐዲሳት ትርጓሜ፦** ከየኔት አባ ስብሐትና ከመጋቤ ሐዲስ ስቡሕ፤ ሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መለስተኛ ኮሌጅ፤ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን፤ በዘመናዊ ትምህርት ረገድም የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቅቀዋል።

- **የመጀመሪያ ዲግሪ በፓትሮሎጂ፦** አቴንስ ቲኦሎጊቻለ ዩኒቨርስቲ፤ 1998 ዓ.ም.፤ እንዲሁም ወደ ጀርመን በመሄድ ተምረዋል።

መንፈሳዊ አገልግሎት፤

- በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም በዲቁና፥ በቅስና ቀዳሽነት፥ ከእጓለ መጋቢነት እስከ ዋና መጋቢነት ፥-

- በምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት አድአ በርጋ ወረዳ የእንጭኒ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳደሪ፤ 1997 ዓ.ም፥.ር በተለያዩ አድባራት በአስተዳዳሪነት፥

- በጀርመን ፍራንክፈርት ከተማ የሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪና ሰባኬ ወንጌል በመሆን አገልግለዋል።

- በውጪው ዓለም ወጣቶችን በማስተማር በሰንበት ት/ቤት እንዲያገለግሉ አድርገዋል።

- በጀርመንና አካባቢው ሀገረ ስብከት በአንበት ት/ቤት ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ በመሆን አራት ዓመታት አገልግለዋል።

- በውጭ ሀገር የሚገኙ የንስሐ ልጆቻቸው በማስተባር በሀገር ቤ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታደሱ፥ ንዋያተ ቅድሳት እንዲሟሉ፥ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ አድርገዋል።

- የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ብቁ ዲያቆናት፥ ካህናትና ሰባክያነ ወንጌል እንዲኖሯት በማሰብ የአብነት ት/ቤት በመክፈት ሙሉ ወጪያቸውን በመሸፈን እስከ 32 የሚደርሱ ተማሪዎችን በማስተማር ላይ ይገኛሉ። ተማሪዎችም ከአንድ ወር በፊት በከንባታ ሐዲያ ስልጤና ደቡብ አፍሪካ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ አንብሮተ እድ መዓርገ ዲቁና ተቀብለዋል።

መዓርገ ክህነት፤

- **ዲቁና፦** ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የምስራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፥ 1972 ዓ.ም.

- **ምንኩስናና ቅስና፦** ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የምስራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ ዝዋይ ገዳም፤ 1989 ዓ.ም.

የቋንቋ ችሎታ፤

- አማርኛ እና ከንባትኛ አፍ መፍቻ፤ ሐዲይኛ፥ ወላይትኛ፥ ጉራግኛ፥ ዳውርኛ፥ ኦሮምኛ ግእዝ፥

- እንግሊዝኛ፥ ግሪክኛ፥ ጀርመንኛ

- ሰርቢያኛና ሩሲኪ ለመግባቢያ ይህል

ሥርዐተ ሢመተ ክህነት

«ወይእዜኒ ዕቀቡ ርእስክሙ ወኵሉ መራዕየ ዘሎቱ ሢመክሙ መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳተ ከመ ትርዐዩ ቤተ ክርስቲያኑ ለእግዚአብሔር እንተ አጥረያ በደሙ»

(የሐዋ.ሥራ 20፥28)

በርእሱ ‘ሢመትና ክህነት’ የተባሉ ሁለት ቃላት የግእዝ ቃላት ሲሆኑ፤ የሚሰጠውም እንደ ዓለማዊ ሥልጣን በምድር ብቻ የሚሠራ ሳይሆን፥ እንደ ሰጪው በምድርም በሰማይም ማሠርና መፍታት የሚችል ልዩና ክቡር ሥልጣን ነው። ለዚህም ነው አበው ሊቃነ ጳጳሳት፡- ምድራውያን፥ መላእክት፡- ሰማያውያን ሰዎች የሚባሉት። (ማቴ. 16፥19፡20)።

ስለዚህም ሥልጣነክህነትሰባትደረጃዎች አሉት፤ ሦስቱ ከፍተኛ ደረጃ የሚባሉ፡- ጵጵስና፥ ቅስና፥ ዲቁና፤ አራቱ ታሕታይ ደረጃ የሚባሉት ደግሞ፡- ንፍቀ ዲያቆን፥ አንባቢ፥ መዘምር፥ በረኛ (አፃዌ ኖኅት) ናቸው። እኒህም በሰባቱ ሀብታት ምሳሌ ሆነው ለመጀመሪያው ሰው ለአባታችን አዳም የተሰጡ ናቸው። እነርሱም፡- አሚን፥ ኩነኔ፥ ንጽሕና፥ ጎይል መንፈሳዊ፥ መንግሥት፥ ክህነት፥ ትንቢት ናቸው። (ገድለ አዳም እና ቀሌምንጦስ ተመልከት)

በዚህም መሠረት አባታችን አዳም በካህንነቱ መሥዋዕት ሰውቷል፤ ዕጣንም አሳርጓል (ኩፋ. 5፥1፡2)። በመቀጠልም የሥርዐተ ክህነት ምሳሌ የሚሆነውን አማናዊውን ለማሳየት አስቀድሞ በተግባር ለአባታችን አብርሃም ያሳየ፥ ተባህትዎና በድንግልና መኖርን የጀመረ ካህነ አምላክ መልከጼዴቅ ነው፤ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር ተብሏል (ዘፍ. 14፥18-20)። ታላቁ አባት አብርሃምም የሌዋውያን ካህናት አባት ሲሆን፤ ሥርዐትን ለማሳየት ለመልከጼዴቅ አሥራቱን በኩራቱን ሰጥቷል (ዕብ. 7፥9)። መልከጼዴቅ የወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌም ነው። ነቢዩ ዳዊት እንደገለጠው «መሐለ እግዚአብሔር ወኢይኔስሕ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከጼዴቅ» (መዝ. 109፥4። ዕብ. 7፥21)

ከዚህም በመነሣት ሠያሜ ካህናት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአበው ሐዋርያት እንዴት መሾም እንደለባቸው በቃል አስተምሮ፥ በተግባርም በአንብሮተ እድ ሹሟቸው ዐረገ ይለናል ቅዱስ መጽሐፍ (ሉቃ. 24፥50)፤ እንዲሁም ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ክህነትን በንፍሐት ሰጥቶአቸዋል (ዮሐ. 20፥22)።

እነርሱም እርሱ ባሳያቸው መንገድ እንደ አሁኑ ለተከታዮቻቸው እንዲያስተላልፉ አዝዞ፥ ‘እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ’ ብሎ በማይታበል ይሁንታ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል (ማቴ. 28፥20)። በዚህም መሠረትነት ነው ሢመተ ጵጵስና የሚሰጠው ያለ። ዛሬም ይህ ረቂቅ ሥልጣን የሚፈጸመው በፈጣሬ ዓለማት ፈቃድ ነው። ያለጥርጥር የታመነ ለመሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራሉ።

ይህንን ረቂቅ ሥልጣንም እንደ ምድራውያን ነገሥታት እጅ እግርን በስለት፥ ዐይንንም በፍላት እያስወጣ የሚቀጣ ወይም እንደ ብሉይ ኪዳን ካህናት አፍአዊ ኃጢአትን

ብቻ የሚያስወግድ አይደለም፤ ይልቁንም ምድራዊም ሰማያዊም ሥልጣን ያለው ነው እንጂ። ይህም በምድር አውግዞ ከማኅበረ ምእመናን ወምእመናት የሚለይ ነው። ሰይፍ ዘክልኤ አፉሁ ይለዋል። ይህ በሁለት ወገን የሚሠራ ተጸፅዖ ንስሐ ገብቶ እስካልተመለሰ ድረስ ግን ማኅበረ በዅር (ጻድቃን) ከሚገቡባት ከመንግሥተ ሰማያት ያስወጣል። ይህም ማለት አክብረው ሥልጣኑን የያያዙት ካህናት (ሊቃነ ጳጳሳት) ሁሉንም ይመረምራሉ፤ በሁሉም ላይ ይፈርዳሉ ማለት ነው።

ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚለው «መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው ሁሉን ይመረምራል፤ እርሱን ግን የሚመረምረው የለም» (2ቆሮ. 2፥15)። ይህም ማለት ኢያሱ አካን ወልደ ኮርዮን (ኢያ. 7፥19-26)፤ ሙሴ ሰለአጵአድን (ዘኍ. 15፥32-36)። ቅዱስ ጴጥሮስ ሐናንያና ሚስቱ ሰጲራን (የሐዋ.ሥራ 5፥1-10)፤ ቅዱስ ጳውሎስ በርያሱስን (የሐዋ.ሥራ 13፥8-10) በተሰጣቸው የብቃት ኀይል እየተመራመሩና በሥውር የተሠራውን ሥራ ዐውቀው አስፈላጊውን ቅጣት እንደሰጡ ይታወቃል። ዛሬ ከእነርሱ የተላለፈው የክህነት ሢመት ሥልጣንም አውግዞ ከመንግሥተ ሰማያት የመለየት ሥልጣን፤ አክብሮ፥ ባርኮ ወደ መንግሥተ ሰማያት የማስገባት ሥልጣን ተሰጥቶታል።

ይህንም ለካህናት (ለሊቃነ ጳጳስት) የተሰጠ ሥልጣን ሰማያዊ ስለሆነ የምድር ነገሥታት በምኞትና በጉልበት አያገኙትም። «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችሁላቸው ይሠረይላቸዋል፤ ይቅር ያላላችሁላቸው ግን አይሠረይላቸውም (ዮሐ. 20፥23። ምሳ. 20፥6-66)፤ እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታሥሩት በሰማይ የታሠረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱም በሰማይ የተፈታ ይሆናል (ማቴ. 18፥18)።»

ሐዋርያትም ይህን ሥልጣን ለተከታዮቻቸው በንፍሐትና በአንብሮተ እድ ሲያስተላልፉ እስከ እኛ ዘመን ደርሶአል። በምሳሌነቱም ለመረዳት እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከምድር አፈር ከፈጠረው በኋላ «በፊቱም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ህያው ነፍስ ያለው ሆነ» (ዘፍ. 2፥7)። ከዚያ በኋላ ሔዋን ስትፈጠርም ሆነ ልጆችዋ ሲወለዱ እግዚአብሔር አምላክ እፍ አለባቸው የሚል የለም። ሥጋ ሲከፈል ነፍስም አንድ ጊዜ የምትከፈል ሁናለችና ነው። ይህ ለነፍስ የተነገረ ቢሆንም ምሳሌነቱ ግን ይህን የሚገልጥ ነውና ነው።

እንደዚሁም ሁሉ አበው ሐዋርያትም ከጌታችን መንፈስ ረድኤትን፥ ኀይለ ክህነትን በንፍሐት ከተቀበሉ በኋላ ተከታዮቻቸው ከጌታ መቀበል አላስፈለ ጋቸውም። ሐዋርትያት ለተከታዮቻቸው፥ ተከታዮቻቸውም ለተከታዮቻቸው፥ እንዲሁ እያለ እስከ ዛሬ ድረስ ሳይቋረጥ ኖሯል። ከዚህም በኋላ እስከ ምጽአት ድረስ ይኖራል (ምሳ. 23፥28)። ይህም ሢመተ ክህነት የሰጪው ሥልጣን ምንም ሳይቀነስ ለተቀባዮቹም ሙሉ የሆነ ጸጋ ያስተላልፋል።

ለምሳሌ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በእርሱ ላይ ያለው መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ምንም ሳይጎድል (ሳይቀነስ) በሰባ ሁለቱ ወንዶች አደረ። ይህም እንደ ሻማ መብራት ነው፤ የሻማ መብራት እልፍ አእላፋት ሰዎች ሻማዎቻቸውን እያበሩ ቢወስዱበት፥ ብዙ ሰዎች እያበሩ ስለወሰዱበት ከነበረው የመብራት ኀይል ፈጽሞ አይቀንስም አይጐድልምና። በካህኑ፥ በጳጳሱ በቅዱስ ፓትርያርኩ ያለው መንፈስ ቅዱስም (ኀይለ ክህነትም) እንዲሁ ነው።

ርትዕት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ሐዋርያዊት ከሚያሰኟት ጉዳዮች አንዱ ይህ ነው። ይህንም አምነው በምእመናን ዘንድ ለተመሰከረላቸው፥ በቅተው ነቅተው ለተገኙ ማለትም ጽንዓ ሃይማኖትን፥ ንጽሕናን፥ ድንግልንና፥ ግብረገብነትና ትምህርትን ገንዘብ ያደረጉ፤ በልቡናቸው ጽማዌ፥ በሰውነታቸው ደዌ የሌለባቸው መሆኑ ከታወቀ በኋላ ከላይ የተጠቀሱትን የክህነት መዓርጋት መሰጠት እንዳለበት ፍትሕ መንፈሳዊ ያዛል።

ማጠቃለያ

ከላይ እንደታተተው፥ በቃሁ ነቃሁ ብሎ ራሱ ለራሱ ክብረ ክህነትን መውሰድ የሚችል የለም። ሢመተ ክህነት የሚሰጠው በጌታ ፈቃድ እንደሆነ ከላይ በዝርዝር አይተናል። ስንኳንስ ከእግዚአብሔር የሚሰጠው ረቂቅ ሥልጣን ይቅርና ከምድራዊ ባለሥልጣን የሚሰጠው ሹመት እንኳ በገዛ ራሱ ገንዘብ ማድረግ የሚቻለው የለም። ጌታም «መኑ እምኔክሙ በተክዞ ዘይክል ወሰኮ አሐደ እመተ በዲበ ቆሙ» ያለው፥ አበው ሲተረጉሙ ከእናንተ ወገን አጠርሁና ልርዘም ብሎ በቁመቱ ላይ ክንድ ሙሉ መጨመር የሚቻለው ማን ነው? እንደዚሁም ሁሉ በቃሁ ነቃሁ ብሎ ሥልጣነ ክህነትን ለራሱ ገንዘብ ማድረግ የሚቻለው ማን ነው? ብለዋል (ማቴ. 6፥27)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በዕብራውያን መልእክቱ ማንም በፈቃዱ ሥልጣነ ክህነትን ገንዘብ ማድረግ እንደማይችል ሲናገር «ወአልቦ ዘይነሥእ ለርእሱ ክብረ ዘእንበለ ዘጸውዖ እግዚአብሔር ዳዕሙ በከመ አሮን» (ዕብ. 5፥4) እንዳለ፥ እንደ አሮን ከእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ለራሱ ክብርን (ሢመተ ክህነትን) የሚወስድ የለም።

ስለዚህ ያልተሰጠን መሻት ወይም በኀይል ለመጠቀም መሞከር ግን እንደነ ቆሬ፥ እንደነ ዳታን፥ እንደ አቤሮን መሆን ነው። እነዚህ የተጠቀሱት በሙሴና በአሮን ላይ በማን አለብኝነት፥ በትዕቢት የተነሡ ናቸው። እግዚአብሔርንም በዚህ ድርጊታቸው ስለአስቆጡት ከብቶቻቸውና ያላቸው ሁሉ ምድሪቱ አፍዋን ከፍታ ዋጠቻቸው፤ እነፍሱና ለእነርሱ የነበሩትም ሁሉ በሕይወታቸው ወደ ሲኦል ወረዱ ይላል ቅዱስ መጽሐፍ (ዘኍ. 16፥3-31)። በዘመነ ሐዋርያት ሀብተ ክህነት በገንዘብ ሸጡልኝ ብሎ እንደጠየቀው እንደ ሸሞን መሠርይ ያስረግማል። (የሐዋ. 8፥18-22)

ንጉሥ ዖዝያንም ሳይፈቀድለት የክህነት ሥራ ለመሥራት በመሞከሩ በለምጽ ነደደ (2ዜና መዋ. 26፥18)። ይህን ያመጣበት እምቢተኛና እልኸኛ ልቡናው ነው። ያልተሰጡትን ነገር፥ የማይፈቀደውንም ምሥጢር በጉልበት፥ በኀይል፥ በማን አለብኝነት መፈለግ ያስቀስፋል። ልንጠነቀቅ ይገባል።

ለሁሉም በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንና በትእዛዘ አበው ተጉዘን የሰያሜ ካህናት እግዚአብሔር ወልድ ጸጋና በረከት ለማግኘት ያብቃን፤ አሜን። መልካም በዓለ ሢመተ ኤጲቆጶሳት ያድርግልን።

ርእሰ ደብር መሓሪ ኀይሉ
የትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት
ዋና ሥራ አስኪያጅ

ሕገ ቤተ ክርስቲያንና ሥርዐተ አበው

«ሐዋዝ ውእቱ ሕገ እግዚአብሔር ዘውስተ ልብየ
በልቡናየ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ሕግ ያማረ ነው።»

(ሮሜ 7፥22)

መግቢያ

በአርአያ እግዚአብሔር ተፈጠረ የሰው ልጅ በሕግት መመራትና መኖር የጀመረው በሕገ ልቡና ነው። በመሆኑም መጻሕፍት ሳይጻፉ የነበሩት ቀደምት አበው በአእምሮ ጠባይዕ ተመራምረው መልካሙንና ክፉውን ለይተው ዐውቀው የእግዚአብሔርን መንገድ ጠብቀው ኑረዋል። ይልቁንም ሕግ ከመጠበቅ አልፈው ምግባር ትሩፋት ሠርተው እግዚአብሔርን አስደስተዋል።

ከእነርሱም መላከል ለማስረጃ፡-

1ኛ) የሕግ አፍራሾቹ የአዳምና የሔዋን ልጅ አቤል ማንም ሳያስተምረው በአእምሮ ጠባይዕ ተመራምሮ በሕገ ልቡና ተመርቶ፥ በትሕትና ሁኖ ንጹሕ መሥውስዕትን ለእግዚአብሔር በማቅረቡ እግዚአብሔርም መሥዋዕቱን በመቀበል መስክሮለታል። እስከ አሁንም ድረስ «መሥዋዕተ አቤል ዘሠመረ» እየተባለ ሲነገርለት ይኖራል (ዘፍ. 4፥4። ዕብ. 11፥4)። በዚህ በጎ ሥራው የቀናው ወንድሙ በግፍ ስለገደለውም የመጀመሪያው ጻድቅና ሰማዕት መሆኑን ጌታ መስክሮለታል። (ማቴ. 23፥25)

2ኛ) የአዳም ሰባተኛ ትውልድ የሆነው ሄኖክም ማንም ሳያስተምረው በአእምሮ ጠባይዕ ተመራምሮ በሕገ ልቡና ተመርቶ ምግባረ ትሩፋት ሠርቶ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስለአደረገ እግዚአብሔር ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ያለውን ምሥጢረ ሰማይ ወምድር ገልጾለት በመጽሐፍ ጽፎልናል፤ በዚህም የመጀመሪያው ጸሓፊ በመሆኑ «ጸሓፌ ትእዛዙ ለእግዚአብሔር» ተብሏል። በመጨረሻም ከሞት ሠውሮታል። (ዘፍ. 5፥24። ዕብ. 11፥5፡6)

3ኛ) ሲወለድ ድንቅ ተአምር የታየለት፥ በቅድመ አያቱ በሄኖክ ትንቢት የተነገረለት፥ በአያቱ በመላልኤል ቤት ያደገው ኖኅም የቅድመ አያቱን የሄኖኦክን ታሪክ በአያቱና በአባቱ ቃል እየሰማ አድጎ በሕገ ልቡና የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዐት በመጠበቁ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አግኝቷል። (ዘፍ. 6፥8) የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቁም ሕግ አፍራሾች በጥፋት ውኃ ሲጠፉ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሠራት መርከብ ከጥፋት ድኗል (ዘፍ. 7፥1 መጨረሻ)። የኖኅ መርከብ የቤተ ክርስቲያን አምሳል ናት፤ ይህንም ቅዱስ ያሬድ ኢትዮጵያዊው ሊቅ፡- አመ ኖኅ ይእቲ መድኀኒት እንተ ኮነት አንቀጸ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቅድስት በማለት ገልጾታል።

በኖኅ መርከብ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቷል። ማለትም የትርጓሜ መጻሕፍት ሊቃውንት እንደሚተርኩልን ኖኅ ወደ መርከብ ሲገባ ዐፅመ አዳምን ይዞ ወንዶች ልጆችን በቀኝ፥ ሴቶች ልጆችን በግራ አድርጎ ገብቷል። ይህም የኖኅ መርከብ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት፥ ዐፅመ አዳም የታቦት፥ ኖኅ የካህናት ምሳሌ ሲሆኑ፤ ወንዶችን በቀኝ ሴቶችን በግራ ማድረጉ ደግሞ የወንዶችንና የሴቶችን መቆሚያና መጸለያ መለየቱ እንደሆነ ይተረካል።

ከእንግዲህ በሕገ ልቡና ተመርተው

የእግዚአብሔርን ሕግ ጠብቀው የተጠቀሙ የእግዚአብሔርን ወዳጆች በዚህ አጭር ጽሑፍ መወሰን ስለማይቻል ለማስረጃ ያህል ሦስቱ ከተጠቀሱ፥ ወደተነሣንበት የጽሑፍ ርእስ እንመለስ። ከላይ በርእሱ እንደተጠቆመው ሕግ የተጀመረው በሕገ ልቡና ነው ብለናልና በመቀጠል፦

- ሕገ ልቡና ምንድን ነው?
- ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና፥
- ኢትዮጵያ በሕገ ኦሪት፥
- ኢትዮጵያ በሕገ ወንጌል፥
- የሕግና የቀኖና መጻሕፍት ማን ማን ናቸው?
- ስለ ሢመተ ኤጲስቆጶሳት ምን ይላሉ?
- የኤጲስቆጶስ ትርጉም ምንድን ነው?
- ከሹመት የሚከለከልበትስ ምንድን ነው?
- የሚሾመው ማን ነው?
- የሚሻርበት ምክንያትስ?
- ጎላፊነቱስ ምንድን ነው?

- ማጠቃለያ፥ በሚሉ ንኡሳን አርእሳት ስለ ሕገ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ቀኖና አበው በመጠኑ እንገልጻለን።

በቅድሚያ ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና የሚለውን እንዳስሳለን።

1) ሕገ ልቡና ምንድን ነው?

ሕገ ልቡና ማለት የሰው ልድጅ በተሰጠው እእምሮ ጠባይዕ ተመራምሮ ክፉውንና መልካሙን ለይቶ የሚያውቅበት የሕሊና ዳኝነት ነው። የሰው ልጅ ከአዳም እስከ ሙሴ በሕግበ ልቡና ተመርቷል።

2) ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና

- እግዚአብሔርን የሚያውቁ፥ የሚያምኑና የሚያመሰግኑ ጥበበኞችና ሃይማኖተኞች መሪዎች
- በእንቆቅልሽ መፈተኗ፥ በዕንቆቅልሽና በቅኔ የሚናገሩ ጥበብን የሚፈልጉ፥
- እጅ መንሻ ወርቅ መውሰኗ፦ መስጠንት እንጂ መቀበልን የማይወዱ ኩሩዎች መሪዎች፥
- በድንግልና ሀገር መምራቷ፥ ኢትዮጵያውያን ድንግልናን ለሹመት መስፈርት የሚያደርጉ፥ ለድንግል ከፍተኛ ክብር ያለቸው መሪዎች እንደነበሯት በግልጽ ያስረዳል።

ከዚህ ላይ አንድ አስተዋይ በዘመናችን ምሁራን መሪዎች ባሉበት በሀገራችን የሚሠራውን አይቶ አዝኖ «ያልተማሩ ምሁሮች ያቆዩዋትን ሀገር የተማሩ ደንቆሮዎች አፈረሷት» በማለት በቁጭት የተናገረውን ስጠቅስ እንደ ድፍረት እንዳይቆጠርብኝ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ እስከ ንግሥተ ሳባ በሕገ ልቡና ተመርታችለች።

3) ኢትዮጵያ በሕገ ኦሪት

ከላይ እንደተገለጸው ጥበበኛዋ ንግሥት ወደ ጥበበኛው ንጉሥ ሰሎሞን በሄደች ጊዜ እግዚአብሔር ጥበብ ፈላጊ መሆንዋን፥ በድንግልናዋ መጽናታን አይቶ ከንጉሥ ሰሎሞን መልካም ዘርን ሰጥቷታል። እርሱም ቀዳማዊ ምኒልክ ነው።

ቀዳማዊ ምኒልክም 22 ዓመት ሲሞላው ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ ከአባቱ ሥርዐተ መንግሥት መጽሐፋዊ ተምሮ፥ በአባቱ ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ የቃል ኪዳን ታቦቱን ከሙሴ ጀምሮ እስከ ሰሎሞን የተጻፉ መጻሕፍተ ብሉይ ኪዳንን፥ መጻሕፍቱን የሚያውቁ ሌዋውያን ካህናትን ይዞልን መጥቷል። በዚህም ሀገራችን ከኢየሩሳሌም ቀጥላ በሕገ ኦሪት እግዚአብሔርን

እግዚአብሔርን ያገለገለች፥ ሕዝቦቿንም በአምላካዊ ሕግ የመራች ታላቅና ታሪካዊት ሀገር ለመሆን በቅታለች። ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ በሕገ አሪት ስትመራ ኑራለች። (ክብረ ነገሥት)

4) ኢዮጵያ በሕገ ወንጌል

ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ በቀዳማዊ ምኒልክ በእግዚአብሔር ፈቃድ በገባው ሕገ አሪት እየተመራች አምልኮተ እግዚአብሔርን እየፈጸመች፥ በትንቢተ ነቢያት ተስፋውን እየተጠባበቀች ከኖረች በኋላ ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ልኮ በቤተ ልሔም ከድንግል ማርያም ሲወለድ በዘመኑ የኢትዮጵያ ንጉሥ ባዜን ገጸ በረከቱን ካቀረቡለት ነገሥት አንዱ መሆኑን «ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ...» የሚለውን የዳዊትን ትንቢት ጠቅሰው መምህራን ይተርካሉ። (መዝ. 71፥9)

በ34ኛው ዓመተ ምሕረትም ኢትዮጵያውያን በየጊዜው ለሥርዐተ አምልኮ ማለት በዓላቱን ለማክበር ይጓዙ ስለነበር በወቅቱ የነበረችው የኢትዮጵያ ንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባዋን አስከትላ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዛለች። ጃንደረባውም ቅዱሳት መፋሕፍትን የማንበብ ልምድ ስለነበረው የኢሳይያስን ትንቢት ሲያነብና ምሥጢሩን ሲያስብ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ልኮለት የተነገረው የነገረ ድኅነት ትንቢት መፈጸሙን አስረድቶት አምኖ ተጠምቆ ተመልሷል። የጃንደረባውም ስሙ ባኮስ ይባላል። (የሐዋ.ሥራ. 8፥26-40)

ከጃንደረባው ታሪክ የምንረዳው ጥንታውያን ኢትዮጵያውያን ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀናዕያን መሆናቸውን፥ መጻሕፍትን የማንበብ ልምድ ያላቸው፥ ያልተረዱትንም ለመረዳት የሚጓጉ ጥበበኞችና አስተዋዮች መሪዎች የነበሯት ታላቅ ሀገር መሆኗን ነው።

ጃንደረባው ሕገ ወንጌልን ዐውቆ፥ በክርስቶስ አምኖ፥ በፊልጶስ እጅ ተጠምቆ፥ መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ የተመለሰው በ34 ዓ.ም. ቢሆንም ሕገ ወንጌል በመላ ሀገሪቱ የተሰበከልን፥ ከመንበረ ማርቆስ የመጀመሪያው ጳጳስ ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማ) ተሹሞ የተላከልን፥ መጻሕፍተ ሐዲሳት ወደ ግእዝ የተተረጐሙልን በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው። የአባ ሰላማ ሹመት ኢትዮጵያ በመንበረ ማርቆስ ሥር እንደ አንድ ሀገረ ስብከት ሁና በጵጵስና ነው እንጂ በፕትርክና አይደለም። ይህ ሐቅ መንበረ ሰላማ በሚል የሚደረገውን ሹኩቻ መሠረተ ቢስ ያደርገዋል። እስትንፋሰ እግዚአብሔር ከተባሉት ከብሉይ ኪዳንና ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እየተውጣጣ ሕግ መንፈሳዊ፥ ሕገ ቤተ ክርስቲያን፥ ሕግ ሥጋዊ ሕገ መንግሥት ተሠርቷል። በዘመናችን ዓለም ለራሱ እንደሚስማማው እያደረገ ሕግ ቢያወጣም ከእነዚህ ያልተገኘ ሕግ የለም።

5) ሕገ ቤተ ክርስቲያን

ሕገ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ሐረግ ከሦስት የግእዝ ግሦች የተገኘ ነው፤ ይኸውም፦ «ሕግ» የሚለው ቃል ትርጉሙ ዘርፈ ብዙ ሲሆን፤ መዝገበ ቃላታዊ ትርጉሙ «ሕግ» ሐገገ፥ ዐገገ፥ ደነገገ፥ ወሰነ፥ ሥርዐት ሠራ፥ አዘዘ፥ ፈረደ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን፤ «ሕግ» ማለት የተወሰነ፥ የተጻፈ፥ የተደነገገ ድንጋጌ፥ ሕግ ሥርዐት፥ ደንብ ውሳኔ፥ ትእዛዝ፥ ፍርድ ተብሎ ይተረጐማል። (መጽ.ሰው.ወግ.ወመ.ቃላት ሐዲስ ገጽ 433)

በሌላ መንገድ በግሪኩ ካኖን የሚለውን ቃል በግእዝ «ቀነ፥ ቀነነ» ዐገገ፥ ደነገገ፥ ደንበ፥ ሕግ፥ ሥርዐት ወሰነ፥ አቆመ፥ ቀኖና ሰጠ ከሚለው ግስ «ቀኖና» የሚለውን ጥሬ ቃል ያወጣና ትርጉሙ እንደ ሕግ ትርጉም ቀኖና፥ ሕግ፥ ሥርዐት፥

ደንብ፥ ፍርድ፥ ቅጣት በማለት ይተረጉመዋል። (መጽ.ሰው.ወግ.ወመ.ቃላት ሐዲስ ገጽ 799-800)

«ሕግ» የሚለው አታድርግ የሚለውን ሲሆን፤ ትእዛዝ የሚለው ደግሞ አድርግ የሚለውን ነው። ይህም አድርግ የሚለውን አለማድረግ ትእዛዝ ማፍረስ ሲሆን፥ አታድርግ የሚለውን ማድረግ ደግሞ ሕግ ማፍረስ ይባላል።

ሕገ ቤተ ክርስቲያን (ቀኖና ቤተ ክርስቲያን) ማለት ቤተ ክርስቲያን የምትመራበት፥ የምትተዳደርበት፥ ሥርዐተ አምልኮዋን የምትፈጽምበት፥ አገልጋዮቿን የምትሾምበት፥ ጥፋተኛ ሁነው ሲገኙ የምትሸርበት ... የመሰለውን ሁሉ የምትፈጽምበትና የምታስፈጽምበት ሕግ፥ ሥርዐት፥ ውሳኔ፥ ደምብ፥ ፍርድ፥ ትእዛዝ፥ አዋጅ ተብሎ ይተረጐማል። ትርጉሙ ይህ ሲሆን፤ ለዚህ ጽሑፍ የተፈለገው ይዘት ስለ ሢመተ ክህነት ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ምን ይላል? የሚለው ስለሆነ በመጠኑ ሰማያዊ ምሳሌዎችን፥ የቀኖና ቤተ ክርስቲያን አንቀጾችንና ይዘታቸውን ብቻ ባጭሩ እንገልጻለን።

6) ቀኖና ቤተ ክርስቲያንና ሢመተ ክህነት

«ቤተ ክርስቲያንስ ትትሜሰል በጽርሐ አርያም ዘላዕሉ ... ቤተ ክርስቲያን በላይኛው ሰማይ በጽርሐ አርያም ትመሰላለች» እንዳለው ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፡- ቅድስት ቤተ ክርስቲ ያን አርአያ ሰማይ ስትሆን አገልጋዮቿ ስዩማነ ቤተ ክርስቲያንን አምሳለ መላእክት ይላቸዋል፤ ምሳሌያቸውም ከታች ወደላይ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሀ) ኤረር በተባለው የመጀመሪያው ሰማይ፡- መላእክት፥ መኳንንት ሊቃናት የተባሉ ሦስት ነገድ ይኖራሉ፤ ምሳሌያቸውም፡-

- መላእክት - የመዘምራን
- መኳንንት - የአናጉንስጢሳውያን
- ሊቃናት - የንፍቀ ዲያቆናት አምሳል ናቸው።

ለ) ራማ በተባለው በሁለተኛው ሰማይ፡- ሥልጣናት፥ መናብርት፥ አርባብ የተባሉ ሦስት ነገድ ይኖራሉ። ምሳሌያቸውም፡-

- ሥልጣናት - የዲያቆናት
- መናብርት - የቀሳውስት
- አርባብ - የቆሞሳት አምሳል ናቸው።

ሐ) ኢዮር በተባለው ሣልሳዊ ሰማይ፡- ኀይላት፥ ሱራፌል፥ ኪሩቤል ሦስት ነገድ ይኖራሉ። ምሳሌያቸውም፡-

- ኀይላት - የኤጲስቆጶሳት
- ሱራፌል - የጳጳሳት
- ኪሩቤል - የሊቃነ ጳጳሳት አምሳል ናቸው። ይህ ሣልሳዊ ሰማይ ቅዱስ ጳውሎስ የማይመረመር ምሥጢር ያየበት፥ ቅዱስ ያሬድ አስደናቂውን ዜማ የሰማበት የምሥጢር ቦታ ነው (2ቆሮ. 12፥2። መጽ. ድጓ)። አገልግሎታችውም የታችኛዎቹ ወደላይ አይወጡም፥ የላይኛዎቹ ግን እስከ ታች ድረስ ወርደው ያገለግላሉ። (ምንጭ፡ የቅዳሴ ታሪክ፤ 1988 ዓ.ም.፤ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት)

ምሳሌያቸውና አገልግሎታቸው ከዚህ በላይ በመጠኑ እንደተገለጸው ሲሆን፤ ለሢመተ ክህነት የሚመረጡበትን መስፈርት፥ እንዴት መመረጥ እንዳለባቸው፡- በምን ቀን፥ በማን ሥልጣን መሾም እንዳለባቸው፥ ኀላፊነታቸው ወይም ከሹመት የሚከለከሉበትን በተመለከተ፥ ወይም ከተሾሙ በኋላ ከሹመት የሚሻሩበትን ምክንያት በተመለከተ በቀኖና መጻሕፍት በሰፊው ተገልጿል።

ይልቁንም በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 4 የሊቃነ ጳጳሳትን፥ አንቀጽ 5 የኤጲስቆጶሳትን፥ አንቀጽ 6 የቀሳውስትን፥ አንቀጽ 7 የዲያቆናትን፥ አንቀጽ 8 የንፍቅ ዲያቆናትን፥ አንቀጽ 9 የሁሉንም ክህነት የሹመት ሥርዐትና ሕግ ዘርዝሮ ያስቀምጣል።

በተወሰነው ሕግና በተሠራው ሥርዐት መሠረት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ብንመራ ይህ ሁሉ በዘመናችን የተከሠተው ችግር ሊፈጠር አይችልም ነበር። ሆኖም የቅድስት ቤተ ክርስቲያን የበላይ ባለሥልጣን ቅዱስ ሲኖዶስ ያደረገውና ቀኖናውን ለማስጠበቅ እያደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ ነው።

ማጠቃለያ

«አንትመ ውእቱ ፄዉ ለምድር ... የምድር ጨው እናንተ ናችሁ ...» እንዳለው፥ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ (ማቴ. 5፥13)። በእግረ ሐዋርያት ተተክተው ሥልጣነ ቅዱሳን ሐዋርያትን ተቀብለው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩ አበው በጨው ተመስለዋል። እንደሚታወቀው ጨው የምግብ ማጣፈጫ ነው እንጂ በራሱ ምግብ አይደለም። ምግብ ሲዘጋጅ ጨው በመጠኑ ተመጥኖ ከተደረገ ምግቡን ያጣፍጠዋል፤ ጨው ከበዛ ግን ያኾመጥጠዋል። የጨው መብዛት ለጤናም ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል። ጨው እንዳይበዛ አልጫም እንዳይሆን መጠንቀቅ ይገባል። እንዲሁ በሐዋርያት እግር የሚሾሙ አበውም በመጠኑ ተውጣጥተው መሾማቸው መልካም ነው። ለዚህም ማስረጃ ጌታ ይህን ዓለም ለማስተማር 12 ሐዋርያትን ሾሟል። እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ወንጌልን እንዲሰብኩ የታዘዙ ሐዋርያትም ከእነርሱ መካከል በተለየው በይሁዳ ፈንታ 2 ሰዎችን መርጠው ዕጣ የወጣለትን አንዱን ሾሙ እንጂ በሕዝብ ብዛት፥ በቆዳ ስፋት ብለው ብዙ ሐዋርያትን አልሾሙም። (ማቴ. 10፥1-5። የሐዋ. ሥራ 21፥26)

እንደሚታወቀው ጥንታዊት፥ ታሪካዊት፥ ሐዋርያዊትና ሉዓላዊት ቤተ ክርስቲያናችን እንኳንስ ሀገረ ሰብከት ለማቋቋም አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን «ደብር» ብሎ ለመሠየም መስፈርት አላት። ስለዚህ በመስፈርትና በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መመራት ተገቢ ይሆናል።

በመጨረሻም ቅዱስ ሲኖዶስ ይህችን ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዋ ሳይሻር፥ ሳይሸረሸር አንድነቷ ተጠብቆ እንዲኖር በትዕግሥትና በማስተዋል በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ያስተላለፈውን ጥበብ የተሞላበት አመራር ሁላችን ተቀብለን ልንተገብር ይገባል። በዚህ ወቅት በብዙ ፈተና አልፈው የተሾሙ አባቶችም ይህችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚያስከብሩና የሚያስቀድሱ መሥዋዕትነት የከፈሉ ምእመናንን ዕንባ የሚያብሱ እንዲሆኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን። አሜን።

መጋቤ ምሥጢር ፍሬ ስብሐት ዱባለ

የሊቃውንት ጉባኤ ም/ሰብሳቢ

እኮተ ሐዋርያትና ፈተናዎቹ

1. ሐዋርያ ማለት ምን ማለት ነው? (የሐዋርያነት ትርጉም)

“ሐዋርያ” የሚለው ቃል “ሖረ” ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ቃል ሲሆን “መንገደኛ፥ መልእክተኛ፥ ቀላጤ” የሚል ትርጉም አለው፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱን ተከትለን ስንተረጉመው “ሐዋርያ” የሚለው ቃል በአማርኛም በቁሙ ሐዋርያ ተበሎ ከመተርጐሙ በተጨማሪ “መንፈሳዊ ሹም፥ መምህር፥ ዙሮ የሚሰብክና የሚያስተምር፥ ባለምሥራች፥ ዐዋጅ ነጋሪ” የሚል ፍቺ አለው (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፥ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፥ 1948 ዓ.ም. ገጽ. 437)::መልእክቱምየጌታ ወንጌል ነው፤ ስለዚህ የሐዋርያነት መሠረቱ ወንጌልን መስበክ ይሆናል ማለት ነው፤ለሰው ልጆች ሁሉ ይደርስ ዘንድ የተላከው የጌታ መልእክት ወንጌል ስለሆነ ወንጌልን ሳይይዙ ወይም ሳይሰብኩ ሐዋርያ መሆን አይቻልም::

በላቲንና በእግሊዝኛ ቋንቋዎች “apostle” የሚለው ቃል ከግሪክኛው “Apostolos” ከሚለው ቃል የተወሰደ ነው፤ ግሪክኛውም ከሁለት የግሪክ ቃላት ማለትም “apo” እና “stellen” የተገኘ ጥምር ቃል ነው፤ “apo” የሚለው “ወዲያ” ወይም “ሩቅ” ማለት ሲሆን “stellen” ደግሞ የተላከ የሚል ትርጉም አለው፤ አንድ ላይ “ወደ ሩቅ ቦታ መልእክተኛ ሆኖ የተላከ” የሚለውን ዐሳብ ይገልጣል:: (ምጭ፡ Dictionary of Word Origins)

2. ሐዋርያነት ስልጣን ነው::

ሐዋርያ መልእክተኛ ቢሆንም በላኪው ስለሚመረጥና ስልጣንን ተቀብሎ የላኪውን ትእዛዝ ስለሚፈጽም ባለሟል ወይም እንደራሴ ነው፤“ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶእንዲያወጡአቸው፥ በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ስልጣን ሰጣቸው” የሚለው የወንጌል ቃልም ይህን ያረጋግጣል (ማቴ.10፥1) :: የማቴዎስ ወንጌል ትይዩ ንባብ የሆነውና በማርቆስ ወንጌል የተጻፈው የሐዋርያትን ጥሪና መመረጥ የሚናገረው የወንጌል ቃል ደግሞ እንዲህ ይላል፤ “ራሱም የወደዳቸውን ወደ እሱ ጠራ፤ ወደ እርሱም ሄዱ፤ ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥ ድውዮችንም ሊፈውሱ፥ አጋንንትንም ሊያወጡ ስልጣን ይሆንላቸው ዘንድ ዐሥራ ሁለት አደረገ” (ማር. 3፥13-15) ::

በዚህ ቃል ውስጥ ስለ ሐዋርያነት ብዙ ነገሮች ተገልጠዋል፤ እነዚህም፥ በራሱ በጌታ መወደድ፥ መመረጥና መጠራት፥ ወደ እርሱ መሄድና ከእርሱ ጋር መኖር፥ወንጌልን ለመስበክ መላክ፥ ድውዮችን ለመፈወስና አጋንንትን ለማውጣት ስልጣንን መቀበል ናቸው፤ ሐዋርያነት አንድ ነገርን ብቻ ወይም ጥቂት ነገሮችንብቻ የያዘ ኀላፊነት እንዳልሆነ ከዚህ ቃል በግልጽ እንመለከታለን::

3. ሐዋርያነት መሠረትነትና ቀዳሚነት ነው::

በዕብራውያን መልእክት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ሐዋርያ” ተብሎ ተጠርቷል፤ ይህም ሐዋርያነት መሠረትነት፥ ጀማሪነት፥ ጥንትነት፥ ፊታውራሪነት፥ አበጋዝነት፥ አስታራቂነት መሆኑን ያስረዳል፤ ኢትዮጵያውያን የአንድምታ ትርጓሜ ሊቃውንት “ርእይዎ ለዝንቱ ሐዋርያክሙ” ያለውን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ሲተረጕሙ “ፊታውራሪያችሁ፥ አበጋዛችሁ፥ አስታራቂያችሁ ኢየሱስ ክርስቶስን አብነት አድርጉት” ብለውታል (የዕብ. 3፥1 አንድምታ ትርጓሜን ተልከት)፤ የነቢያትና የሐዋርያት መሠረትነት ቀደምት አማንያንና ለክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የዐይን ምስክሮች መሆናቸው ነው::

በሌላ ስፍራ ቅዱስ ጳውሎስ “እስመ ተሐነጽክሙ ዲበ መሠረተ ሐዋርያት ወነቢያት” ያለውን የሐዋርያ ቃል የአንድምታ ትርጓሜ መምህራን “ነቢያት ሐዋርያት ባመኑበት እምነት ጸንታችኋልና” ብለው መተርጐማቸው ለዚህ ምስክር ነው፤ “አንተ ኰኵሕ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ አሐንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ” ያለውን የወንጌል ቃልም “እኔ መሠረት ነህ ብዬ መሠረት እንደሆንህ እናገርልሃለሁ” በማለት ይፈቱትና “መሠረትነቱ የሃይማኖት የሹመት ነው” ይላሉ፤ ግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ወንጌልም “ወኰኵሕሰ ዘተብህለ በአፈ ጴጥሮስ ሃይማኖተ ጴጥሮስ፤ እስመ ይቤ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ አሐንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ ከመ ዘይቤ ወዲበ ዛቲ ሃይማኖትከ” ብሎ ይተረጕመዋል፤ በአማርኛ “ዐለት የተባለው በጴጥሮስ አንደበት የተነገረው ሃይማኖት ነው፤በዚህች ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ ብሏልና፤ ይህም በዚህች ሃይማኖትህ ላይ እንደማለት ነው” የሚል ነው፤ የሃይማኖት የሹመት መሠረት የመሆን ሐዋርያዊ እምነትና ትምህርትም ይህ ነው::

ሐዋርያት የሰበኩት መሠረት ክርስቶስ ነው፤ እነርሱ ከሰበኩት ክርስቶስ የተለየ ሐሰተኛ ክርስቶስን የሚሰብክ ቢኖር ከእውነተኛው እምነት የወጣና በፍርድ ቀን የሚቀጣ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ በሚከተለው መልእክቱ ያስጠነቀቀውም በዚህ ምክንያት ነው፤ “የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፥ ሌላውም በላዩ ያንጻል። እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ። ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ፥ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል” (1ቆሮ. 3፥10-12) ::

4. ሐዋርያነት አብነት/አባትነት ነው::

አብነት የሚለው ቃል “አብ” ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጕሙም “አባትነት፥ ጌትነት፥ ባለቤትነት፥ አርአያ፥ ምሳሌ፥ መድኀኒት፥ ነባር፥ ጥልቅና ትልቅ ዕውቀት ያለው፥ ምስክር ፥ተጠያቂ፥ አዋቂ፥ ሊቅ፥ አባት፥ ወይም ለምስክርነትና ለተጠያቂነት የበቃ ሊቅ አዋቂ” ማለት ነው:: ስለዚህ አብነት የሚለው ቃል ለተጠያቂነት ከመብቃት፤ለአንድ ሙያ (ዕውቀት) በቂ ትምህርትን ከመያዝና ምስክር ሆኖ ከመገኘት ጋር የተያያዘ ነው::

ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያይቱ የቆሮንቶስ መልእክቱ “በክርስቶስ ብዙ ሞግዚቶች ቢኖሩአችሁምብዙ አባቶች የሉአችሁም፤ እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጂአችኋለሁና” (1ቆሮ.4፥15) ይላል:: ከዚህም በመነሣት “እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ” ብሎ ልጆቹን ይመክራል (1ቆሮ.11፥1) :: ዛሬም የሚያስፈልገን ሐዋርያዊ አባት እንዲህ ክርስቶስን መስሎ እኔን ምሰሉ የሚልና በወንጌል ለወለዳቸው ልጆች አባት የሚሆን፥ አብነት/አርአያ የሆነ ሕይወት ያለው ሊሆንይገባዋል::

5.ሐዋርያዊ (የሐዋርያት) ተልእኮ ማለትስ ምን ማለት ነው?የሐዋርያት ተልእኮ ምን ነበር?

ሐዋርያዊ ተልእኮ ዘርፈ-ብዙ፥ እግዚአብሔርንና ሰውን ማገልገልን የሚያካትትሰፊ ኀላፊነት ነው፤ሐዋርያት በቤተ ክርስቲያን ያላቸው ኀላፊነት ሁለንተናዊ እንጂ በአንድ ወይም በጥቂት ጉዳዮች ላይ የሚያተኵር ብቻ አይደለም፤ ሆኖም ግን ለዚህ አጭር ጽሑፍ በሚሆን መልኩ ዋና ዋና ነገሮችን እጠቅሳለሁ::

ወንጌልን መስበክ

የአንድ ሐዋርያ ወይም የሐዋርያትን መንበር የወረሰና በእግራቸው ተተክቶ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግል አባት ዋና ተልእኮ ወንጌልን መስበክ ነው፤"ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ራሱ ለዘላለም ድኅነት የሆነውን የማይለወጠውን ቅዱስ ወንጌል ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በእጃቸው ላከው፤... ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" የሚለው የወንጌል ቃል ይህን ታላቅና የከበረ ተልእኮ የሚያስረዳ ነው (ማር. 16፥8፡15) ::

ሐዋርያት የተመረጡት፥ ከዓለም የተለዩት፥ ክርስቶስ ከዋለበት ውለውና ካደረበት አድረው ትምህርትና ተአምራት ሳይከፈልባቸው ሁሉን ያዩትና የተማሩት፥በመጨረሻም ሰማያዊ ኀይልን የተቀበሉትና በጸጋ መንፈስ ቅዱስ የተሞሉት ለዚህ ታላቅና ክቡር ተልእኮ መሳካት ነው፤ በዚህ መልክ የክርስቶስ ምስክሮች ሆነው የወንጌሉን ቃል ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ሰበኩ፤ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም፥ በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም፥ እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"(የሐዋ.1፥8) ብሎ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርት ያዘዘው ትእዛዝ መዳረሻውም መላውን ዓለም በወንጌል መድረስና በዕርፊ መስቀል ማረስ እንደ ሆነ ያሳያል፤ ለዚህም አስቀድሞ "ውስተ ኵሉ ምድር ወፅአ ነገሮሙ፤ ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ" ማለትም "ድምፃቸው በምድር ሁሉ ላይ፥ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ" የሚል ትንቢት አስቀድሞ ተነግሮ ነበር (መዝ.18፥4፤ ሮሜ 10፥18) ::

ይህን ተልእኮ 12 ሐዋርያት ብቻ ሊፈጽሙት እንደማይችሉ፥ ተልእኮውም ለነርሱ ዘመን ብቻ እንዳልሆነ የታወቀ ነው፤ በሐዋርያት መንበር የተተኩ አባቶች በየዘመኑ ይህን ሐዋርያዊ ተልእኮ ተረድተውና ሐዋርያዊ ቅብብሎሽን ጠብቀው እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ በትጋት ሊፈጽሙት ይገባል፤"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" በሚለው የክርስቶስ ቃል ውስጥ "እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" የሚለው የወንጌል ቃል ተልእኮው እስከ ዓለም ፍጻሜ እንደሆነ ያሳያል፤ስለዚህ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት በቀዳሚነት፥ ካህናትና ምእመናን ደግሞ በአበው መሪነትበዚህ ታሪካዊና መንፈሳዊ ሂደት ውስጥ ዛሬ ላይ ይህን ታላቅና ክቡር ኀላፊነትእንዴት እየተወጡ ነው? የሚለውን ጥያቄለብፁዓን አባቶች፥ ለካህናትና ለልጆቻቸውምእመናንእንተወዋለን::

ጥሙቃንን በትምህረተ ወንጌል ማጽናትና መጠበቅ

"በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" (የሐዋ. 20፥28)

የሚለው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ ቃል ጥሙቃንን የመጠበቅ ኀላፊነት ለጳጳሳት የተሰጠ ሐዋርያዊ ተልእኮ መሆኑን ያስረዳል፤ ቅዱስ ጳውሎስ “እኔ ተከልሁ፤ አጵሎስ አጠጣ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር” (1ቆሮ. 3፥6) እንዳለ መትከል ዐዳዲስ አማንያንን አስተምሮ ማጥመቅና ወደ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ማስገባት ነው፤ ማጠጣት ደግሞ አማንያንን በትምህርተ ወንጌል ማጽናትና ማሳደግ ነው፤ የሚተክልናየሚያጠጣ ሁለቱም አገልጋዮች ናቸው፤ ባለቤቱ እግዚአብሔር ሕይወትን ይሰጣል፤ ያሳድጋልም፡፡ ጥሙቃንን (አማንያንን) የመጠበቅና የማሳደግ ሐዋርያዊ ተልእኮ ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ በዘመነ ሊቃውንትና በዚህም ዘመን ቤተ ክርስቲያን ያለምንም መቋረጥ እየፈጸመችው የኖረና ያለ ሐዋርያዊ ተግባር ነው፡፡

የሐሰት (የስሕተት) ትምህርቶችን መቃወምና እውነተኛውን ትምህርት መጠበቅ

ሐሰተኛ ትምህርት/ምንፍቅና የቤተ ክርስቲያን የውስጥ ደዌ ነው፤ ከአባላት መካከል በአንዱ ወይም በብዙ አባላት ላይ የሚታይና ሌላውን ጤነኛ አባል/የአካል ክፍል/በቅርበት የሚጎዳ ይሆናል፤ ከዘመነ ሐዋርያት ቀጥሎ በነበረው ዘመነ ሰማእታት ቤተ ክርስቲያን ከዓላውያን ነገሥታት በሚመጣ ከፍተኛ ስደትና መከራ ውስጥ አልፋለች፤ እንደ አውሮፓውያን አቈጣጠር ከ312 ዓ.ም. በኋላ ሰላም ሲገኝ ደግሞ ቀድሞም በመጠኑ የነበረ ቢሆንም የመናፍቃን መነሣትናየስሕተት ትምህርቶች መስፋፋት ቤተ ክርስቲያንን ከውስጥ ፈተናት፤ ወደ ውጭ መዘርጋትና ያላመነውን ዓለም በወንጌል የማሳመን ተልእኮዋን በማደናቀፍ የውስጥ ችግሮችን በመፍታት ላይ እንድትጠመድ አደረጋት፤ በመስፋፋት ፈንታ ተሰበሰበች ወይም መስፋፋትዋ ተገታ፤ማውገዝና መናፍቃንን ከቤተ ክርስቲያን መለየት የግድ ስለሆነ በክርስቲያኖች መካከል መለያየቱ እየሰፋ ሄደ፤ቤተ ክርስቲያን በዚህ ችግር ለ300 ዓመታት ስትፈተን ከቆየች በኋላ ችግሯን የበለጠ የሚያባብስ የእስልምና መነሣት ተከሠተ፤ ይህ ሁሉ ታሪካዊ ሁኔታ የሚነግረን የሐሰት ትምህርትን መከላከልና እውነተኛውን ትምህርት ማስተማር በሐዋርያዊ ተልእኮ የግድ መሆኑን ለማሳየትና ይህን ኀላፊነት በትክክል አለመወጣት ሁለንተናዊ ጥፋት የሚያመጣ መሆኑን ለማመላከት ነው፤ ስለዚህ ብፁዓን አባቶች፥ ካህናትና ምእመናን ከቅዱሳን ሐዋርያት የተቀበልነውን እምነትና ትምህርት መጠበቅና ሳይበረዝ ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ይገባቸዋል፡፡

ሐዋርያዊ ቅብብሎሽንና የቤተ ክርስቲያንን ቅዱስ ትውፊት በመጠበቅ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ማጽናት

ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ የሚባለው ቃል የ12ቱ ሐዋርያት ስልጣን በተለይ በኤጲስ ቆጶሳት (ጳጳሳት) በኩል እስከ ዛሬ የቀጠለበት፥ ወደፊትም የሚቀጥልበት ክህነታዊ ሰንሰለት ነው፤ ዋናው ዐሳብ የዛሬዋ ኦርቶክሳዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሐዋርያት ከሰበሰቧትና ከመሯት ጥንታዊት ቤተክርስቲያን ጋር በእምነትና በትምህርት አንድ መሆንዋን የሚያረጋግጥ ቅብብሎሽ ነው፤ ከጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል ቀሌምንጦስ ዘሮምና አግናጥዮስ ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ ምንእንደሆነ አስተምረዋል፤ ግኖስቲካውያን ስዉር እንቅስቃሴ በመፍጠርና ይህን ስዉር እንቅስቃሴ ትክክለኛው የሐዋርያት ትምህርትና እምነት ወራሽ እንደሆነ በማስተማር

ክርስቲያኖችን ማሳት ሲጀምሩ ቀሌምንጦስና አግናጥዮስ ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያትን ተልእኮ በስዉር ሳይሆን በዐደባባይ እየሰበኸች ጠብቃ ያለች መሆንዋንና ስዉር እንቅስቃሴ ያደረጉ መናፍቃን ከእውነተኛው ሐዋርያዊ ሰንሰለት ራሳቸውን እንደለዩ በማስተማር የሐዋርያዊ ቅብብሎሽ ትምህርት ምን እንደሆነ የሚያሳይ መሠረት ጥለዋል፤ ከትምህርትና እምነት ይዘት በተጨማሪም ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ እጅ በመጫን የሚገለጥ ክርስቲያናዊ የሢመተ ክህነት መስመርም ነው::

የቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚገለጠው በእምነትና በትምህርት ኦርቶክሳዊነት (ርቱዕነት)፥ በሐዋርያዊ ቅብብሎሽ፥በቀኖና ወጥነትና በመዋቅር አንድነት መጽናት ሲቻል ነው፤የትምህርት ትክክለኛነት የእምነትን ትክክለኛነት ያመጣል፤ በትምህርት የተከፋፈለች ወይም ሐሰተኛ ትምህርትን የማትቃወምና የማታወግዝ ቤተ ክርስቲያን ውስጣዊ ጥንካሬዋና አንድነትዋ ይዳከማል፤ እንዲህ ባለ ሁኔታ ያለችቤተ ክርስቲያንበቀኖና እና በመዋቅር አንድነት ሊኖራት አይችልም፤ከሐዋርያዊ ቅብብሎሹ ያፈነገጠና ቀኖናን የጣሰ አሠራር ሊስፋፋባት ይችላል፤ሐሰተኛ ትምህርትን መከላከልና እውነተኛውን ትምህርትመጠበቅ የሐዋርያት ትልቅ ተልእኮ እንደሆነም አስቀድመን ተመልክተናል፤የቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ትውፊትንና ሐዋርያዊ ቅብብሎሽን (Apostolic succession)መጠበቅ የቀኖና አንድነት መሠረት ይሆናል፤ የትምህርት፥ የእምነትና የቀኖና አንድነት ካለ የቤተ ክርስቲያን ሕጎችወጥና ተፈጻሚነታቸው ከፍተኛ፥የቤተ ክርስቲያን መዋቅርም አንድነቱ የጸና ይሆናል፤ ሐዋርያነት ይህ ነው! የዛሬ ዘመን አባቶች ኀላፊነትም ይህን ጠብቆ ማስጠበቅ ነው::

በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙትን መፈወስ

ሕማምና ደዌ ልዩ ልዩ ዐይነት ነው፤ አካላዊ፥ ሥነ ልቡናዊ፥ መንፈሳዊና ማኅበራዊ መልክ ያላቸው ልዩ ልዩ ደዌያት አሉ፤ደዌ ነፍስ በትምህርት፥ ደዌ ሥጋ ደግሞ በተአምራት ይርቃል፤ የነፍስ ደዌ ለሥጋ እንደሚተርፈው ሁሉ የነፍስ በትምህርተ ሃይማኖት መፈወስም የሥጋዊ ጤንነትን ያስገኛል፤ ደዌያት እርስ በእሳቸው የተሳሰሩ ናቸውና፤ አባቶች ሐኪሞች ናቸው፤ የሰው ልጆችም በኀጢአት በሽታ ከተያዙ ዘመናት ተቈጥረዋል፤ በሽታው እያስከተለ ያለው ሁለንተናዊ ሥቃይም ለአንድ መንፈሳዊ ሐኪም የተገለጠ ነው::

እንግዲህ ሐኪሞች ምን ያህል ለሕዝቡ ሥቃይ ያዝናሉ? ለማከም ምን ያህል ይተጋሉ? ምን ያህል የሙያ ብቃትና ዝግጅት አላቸው? የሚሉት ጥያቄዎች አሁንም መልስ ይፈልጋሉ፤ ደዌ ነፍሱ በስብከተ ወንጌልና በትምህርተ ሃይማኖት ይርቃል ብለናል፤ መንፈሳዊ ጤንነቱ ለሥጋዊ ጤንነት መሠረት እንደሚሆነውም ዐይተናል፤ ከዚህ ቀጥሎም በጸሎትና በጸበል ሕሙማንን መርዳት፥ትምህርት ቤቶችን ማስፋፋት፥ የሕፃናት ማሳደጊያዎችንና የአረጋውያን መደገፊያ ተቋማትን መመሥረት፥ የጤና ተቋማትን መገንባትና ባለሙያዎችን በሳይንስና በመንፈሳዊ ሥነ ምግባር ማሰልጠንና ማብቃት፥ ወጣቶችን በእውነተኛ ትምህርተ ሃይማኖት መሳደግ፥ የማኅበረሰብ ፈውስ መሠረት ናቸው፤ዘርፈ ብዙ ሕማምና ሥቃይ እየደረሰበት ያለውን የሰውን ልጅ ለመርዳት ዘርፈ ብዙ ዐቅምና ችሎታ ያለው አገልጋይ ያስፈልጋል::

6. ሐዋርያት/ተከታዮቻቸው ተልእኮአቸውን በትክክል ለመወጣት ምን ያስፈልጋቸዋል?

ሐዋርያዊ ተልእኮን በአግባቡ ለመወጣት ሰማያዊ ኀይል (ጸጋ መንፈስ ቅዱስ)፥ እምነት፥ የሚያገልግሉትን ክርስቶስንና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን መውደድ፥ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት (የቅዱሳት መጻሕፍትትምህርት)፥ በክርስቶስ ፍቅር ተማርኮ ከዓለም መለየት፥ ጸሎትና አንድነት በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፤ በዚህ ዘመን ደግሞ ሐዋርያዊ ተልእኮ ከእግዚአብሔር ቃል እውቀት በተጨማሪ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀትን፥ የቋንቋ ችሎታን ይፈልጋል፤በእርግጥ የቋንቋ ችሎታ ሁልጊዜም አስፈላጊ ነው፤ በበዓለ ኀምሳ ለሐዋርያት 72 ቋንቋዎች የተገለጡላቸውም በዚህ ምክንያት ነበር፤ አባቶች አባት የሚሆኑት በእምነትና በመንፈሳዊ ሕይወት ቢሆንም ለሚያገለግሉት ማኅበረሰብ የሚሰጡትን ሐዋርያዊ ተልእኮ በተገቢ መልክ ለማከናወንይችሉ ዘንድ የሳይንስና ቴክኖሎጂእንዲሁም የባህልና የቋንቋ እውቀት በጣም ያስፈልጋቸዋል።

7. ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልእኮዋን ለመፈጸም እንቅፋት (ፈተና) የሆኑባት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

የቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ ተልእኮ ከጅምሩ እስከ ዛሬ፥ ከዚህ በኋላም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚያደናቅፉ ሁለት ነገሮች አሉ፤ እነዚህም ከአይሁድና ከአሕዛብ የመጣ/የሚመጣ ተቃውሞ/መከራ እና ከውስጥ አባላት የተነሡ/የሚነሡ የስሕተት ትምህርቶች፥ ምንፍቅናዎችና ክሕደቶች ናቸው፤ መከራና ተቃውሞ ፈተና ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን መስፋፋትን፥ የስብከተ ወንጌል መጠናከርንና የምእመናን መብዛትን የሚያመጣ እድልም ይሆናል፤ መከራ ለቤተ ክርስቲያን ጌጥና የሰማዕታት መፈልፈያ መልካም አጋጣሚም ነው፤ሆኖም ግን የመከራው ጽናት የቤተ ክርስቲያንን መዋቅር ሊያፈርስ፥ ምእመናንን ሊበትን፥ መጻሕፍትን ሊያጠፋ፥ አብያተ ክርስቲያናትን ሊያፈርስ ይችላል፤በሀገራችን በታሪክም ሆነ በአሁኑ ወቅት የሆነውና እየሆነ ያለውም ይህ ነው፤ ይህ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልእኮዋን የመወጣት ዕቅምዋ ይዳከማል፤ አንዳንድ ሀገሮች ላይ በታሪክ እንደ ታየው ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ህልውና ፈጽሞ ሊጠፋም ይችላል፤ ቱኒዝያና ኑቢያ (ሱዳን) ውስጥ የሆነው ለዚህ ምሳሌ ነው፤ ስለዚህ ለቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልእኮ መሳካት ሰላም ያስፈልጋል፤ ሰላም ሲገኝ መናፍቃን ከውስጥ ስለሚነሡ ደግሞ እውነተኛውን ትምህርትና እምነት አስቀድሞ በትጋት በማስተማር መከላከል ይገባል።

8.ማጠቃለያ ሐሳብ

ሐዋርያዊ ተልእኮ ምን ያህል ታላቅና የከበረ ኀላፊነት እንደ ሆነ፥ የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያትና በሐዋርያት እግር የተተኩ ጳጳሳትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በታሪክ ሂደት በልዩ ልዩ መከራና ፈተና ውስጥ አልፈው የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ከእኛ ከልጆቻቸው እንዳደረሱት ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተማርነው እውነት ነው፤ ጥያቄው በዚህ ዘመን ይህ ሐዋርያዊ ተልኮ የሚገባውን ትኩረት አግኝቶ እየተፈጸመ ነው ወይስ ቸል ተብሏል? የሚለው ነው፤ ስሙን ብቻ ተቀብለን ግብሩን መፈጸም ካቃተን በቤተ ክርስቲያን ላይ የምናደርሰው ጉዳት ሁለንተናዊ ነው፤ ላላመነው ዓለም ትምህርተ ወንጌልን

ማድረስ አንችልም፤ ያመኑትን ምእመናን ማጽናት አንችልም፤ በደዌ ሥጋና በደዌ ነፍስ ተይዞ በጽኑ ሥቃይ እየተጨነቀ ላለው ዓለም መድረስ አንችልም፤ ፍትሕ ለጎደለበትና ለተበደለ ድሃ መቆም ያቅተናል፤ ከዚህም አልፎ ከገፊና ከበዳይ ጋር ቆመን እግዚብሔርን ልናሳዝን እንችላለን፤ጨውነትና ብርሃንነት ወደ አልጫነትና ጨለማነት ይቀየራል፤ ይህም በሰውና በእግዚአብሔር ፊት የሚያስከትለው ፍርድ ከፍ ያለ ይሆናል።

ሐዋርያ የሚለውን ስም መሸከም ብቻ በጎ/ትክክለኛ ሐዋርያ አያደርገንም፤ እንዲያውም አንድ ሰው ከመንፈሳዊነት የራቀና ክርስቲያናዊ አርኣያነት የሌለው ከሆነ ክርስቲያንም ሆነ፥ ጳጳስም ሆነ ካህን ወይም ሐዋርያ የሚለው ቃል ብቻውን ስም ሆኖ ቢሰጠው ያስኬንነዋል እንጂ አያጸድቀውም፤ሐዋርያ የሚለው ስምም የቃሉ ትርጉም ሲታይ ለክፉም ለበጎም ይሆናል፤ ለምሳሌ ጠቢቡ ሰሎሞን በተናገረው ቃል (ምሳሌ 6፥10፡11) “ሕቀ ትነውም ወሕቀ ትነብር፤ ሕቀ ትዴቅስ ወሕቀ ታስተጋብእ እዴከ ዲበ እንግድዓከ ። ወእምዝ ይመጽአከ ግብተከመ እኩይ ሐዋርያ ንዴት” በሚለው ንባብ ውስጥ የተሰመረበትና ተንጋድዶ የተጻፈው ንባብ እንደሚያመለክተው ሐዋርያ ለሚለው ቃል እኩይ የሚለው ቃል ተቀጥሎለት ይታያል፤ ትርጉሙም “ድህነት እንደ ክፉ መልእክተኛ ድንገት ይመጣብሃል” ማለት ነው፤ስለዚህ ሐዋርያ የሚለው ቃል ስም ብቻ ሆኖ እንዳይቀርና አብነትን/አባትነትን የሚገልጥ እንዲሆን የላኪውን የክርስቶስን ፈቃድና ስልጣን በመፈጸም ሊገለጥ ያስፈልገዋል። በሌላ ስፍራ ጠቢቡ ሰሎሞን “ላእክ አብድ ይወድቅ ውስተ እኪት ወሐዋርያሰ ጠቢብ ያድኅን ርእሶ” (ምሳሌ 13፥17)እንዳለው ሰነፍ መልእክተኛ በክፋት ውስጥ ይወድቃል፤ ጠቢብ ሐዋርያ (መልእክተኛ) ግን መጀመሪያ ራሱን ያድናል፤ ቀጥሎ ሌሎችን የሚያድን ሐዋርያዊ ተልእኮውን በአግባቡ ይወጣል፤ የሐዋርያዊ ተልእኮ አደራ ተቀባዮች የሆኑ ብፁዓን አባቶች፥ ካህናትና ምእመናን ጠቢባን ሐዋርያት ሆነው መጀመሪያ ራሳቸውን፥ ቀጥሎ ደግሞ ሌላውን ዓለም ማዳን እንዲችሉ የቤተ ክርስቲያን አምላክ ጥበቡንና ጸጋውን ይስጥልን።

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንን እግዚአብሔር ይጠብቅልን!

መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብር

የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ሰባኬ ወንጌል

መዐርገ ኤጲስ ቆጶስ በጥንታውያን የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዓለም አቀፍ ዳሰሳ

1. መግቢያ

እግዚአብሔር አምላካችን እርሱ በፈቀደና እሱ ብቻ በሚያውቀው ምሥጢር ምስጋናው የሚደርስበትን አምልኮው የሚፈጸምበትን መንገድ እና ጥበብ በብሉይ ኪዳንም በሐዲስ ኪዳንም ሠርቷል። ይኽም ልዩ ምሥጢር እና ጥበብ ሥልጣነ ክህነት ነው፡ ፡ በብሉይ ኪዳን ከዐሥራ ሁለት ነገድ አንዱን የሌዊን ነገድ ለብቻው ለይቶ ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ከዚያም የአሮንን ቤት ለሊቀ ካህንነት ለይቶ (ቀድሶ) ለዚህ ተልእኮ መርጧል። ይኽንም ሲያደርግ እሱ በፈቀደና ባወቀ አደረገ እንጅ በሰማይም ካሉ በምድርም ከሚኖሩ ፍጡራን የማንንም ምክር እና አስተያየት አልጠየቀም። በሐዲስ ኪዳን እንዲሁ የድኅነት ምሥራች የሆነች ቅድስት ወንጌልን ሲሠራ፣ የቃሉን ትምህርት፣ የእጁን ተአምራት አይተው ከሚከተሉት አምስት ገበያ ከሚሆን ሕዝብ መቶ ሃያ ቤተሰብን፣ ከመቶ ሃያውም ዐሥራ ሁለቱን ለሐዋርያነት ሲመርጥ እንዲሁ እሱ በፈቀደ፣ ዐውቆ በወደድ መጠን በስም ጠርቶ ተከተሉኝ አለ እንጅ የሰውን ምኞት፣ የኋደኛ ምልጃ፣ የምድርን መለኪያ አልተጠቀመም። ስለዚህም ክህነትን ይልቁንም ትልቁን የኤጲስ ቆጶስነት መዐርገ ክህነት የእግዚአብሔር ጥሪ ነው ብለን እናምናለን።

የቅድስት ቤተ ክርስትያን ልዩ መታወቂያዋ ከሆኑት መጠሪያዎቿ ውስጥ አንድነቷ ወሳኝ ቦታ አለው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከአመሠራረቷ ጀምሮ አንዲት ናት፤ በወርቀ ደመ የመሠረታት ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በሐዋርያት ጉባኤ ሲመሠርታት እነሱ ብዙ ቢሆንም ስለቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ሲናገር ቤቶቸን ሳይል በአንድነት (ወይም በነጠላ) አንቀጽ ቤቴን በማለት ጠርቷታል። (ማቴ 16፤18) ስለዚህ ጌታችን የአንድ መንጋ ባለቤት ነው፤ (ዩሐ 10፤16 ዮሐ 21፤15) እርሱ የቤተ ክርስቲያን ራሷ ሊሆን እሷ ደግሞ እስከ መስቀለ ሞቱ ድረስ የወደዳት አንድ አካሉ ነች (ሮሜ 12፤16 1ኛ ቆሮ 12፤27፤ ቆላ 1፤18፣ ኤፌ 1፤23)። እርሱ ሙሽራዋ ሲሆን ሙሽራው እንድትሆን የፈቀዳላትም አንዲት ቤተ ክርስቲያን ናት (ኤፌ 5፤27)። በእናት ቤተ ክርስቲያን ላይ አንዱን መንጋ ጠብቀው እንዲያገለግሉ በስም ጠርቶ ሰማያዊ ሥልጣንን፣ መንፈሳዊ ሀብት፣ በቦታና በጊዜ የማይገደብ ተልእኮን ከመለኮታዊ አደራ ጋር ለሐዋርያት እና ለእነሱ ተከታዮች ኤጲስ ቆጶሳት ሲሰጣቸው ይኽንን አንድነት እና ቅድስና፣ ስፋህ እና ሐዋርያዊ የሆነ ባህርይዋንም እንዲጠብቁ ነው።

ዓለም አቀፋዊት በሆነች፣ በሰው ልጆች ባህል፣ ቋንቋ፣ ቀለምና መልክዓ ምድራዊ አሰፋፈር፣ ወይም ማኅበራዊ ልማዶች እና የኑሮ ደረጃ የማትወሰነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ የማይለወጥ መሠረተ እምነቷ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጡ ሰማያዊ ምሥጢራቷ፣ በውስጧ የሚፈጸሙት መንፈሳዊም ሆኑ ማኅበራዊ ሥርዓቶች በሙሉ አንድነቷን፣ ቅድስናዋን፣ ዓለምአቀፋዊነቷንና ሐዋርያዊነቷን የሚገልጹ ናቸው። ለሰው ልጅ ድኅነት እና ዘለዓለማዊ ልዕልና የምትፈጽመው ተልእኮ በሙሉ ከዚህ ፍጹም አንድነት እና ዘላለማዊ

ሕብረት ውጭ መገለጫ የለውም። ከሁሉ በላይ ደግሞ የቤተ ክርስትያን መሠረታዊ የሆነው በሰዎች መካከል እና በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል ያለው የአንድነት ትሥሥር የሚገለጠው ከሐዋርያት በተቀበልነው እንከን በሌለው እና ርቱዕ በሆነ አንድ እምነት በማመናችን፤ እና የድኅነት ምሥጢራት ሁሉ እንዲፈጽሙ ለሐዋርያት በሰጣቸው በምሥጢረ ክህነት ነው። ይኽ ምንጩ ሰማያዊ የሆነ በዚህ ምድር ላይ በሚታይ አገልግሎት ፍጹም የሆነውን የድኅነት ጸጋ የሚያሰጠን ሥልጣነ ክህነት ከሐዋርያት የሥልጣን ተዋረድ የተገኘ በብፁዓን አበው ኤጲስ ቆጶሳት አማካኝነት እስከ ዓለም ፍጽሜ ድረስ በመላው ዓለም የሚሠራ ሥልጣን ነው። በዚህ ሥልጣንም መሠረት ሐዋርያዊ ተልእኮን የሚፈጽሙት አበው ኤጲስ ቆጶሳት ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጣቸው "እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ" ብሎ የገባላቸው እውነተኛ ቃልኪዳን ስላለ ተልእኮው በሙሉ የሐዋርያት መሆኑን እናምናለን። ይኽ ሐዋርያዊ ተልዕኮና አደራ ፍጹም ሰማያዊ ነው፤ በዚህ ምድር አምሳያ የለውም፣ ከዚህ ምድር ፈራሽና ኃላፊ ፍልስፍና እና ደካማ ጥበብ ጋር ዝምድና የለውም፤ ተጠሪነቱም ለአደራ ሰጭው እና ዋጋ ከፋዩ አምላክ ብቻ ነው።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የመሠረታት መድኀኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ አካሉ ስለሆነች ያለምንም ምድራዊ ወሰን እና ገደብ አንድ የአዳም ዘር ለሆነው የሰው ልጆች ሁሉ ሐዋርያዊ ተልእኮን ስትሰጥ ይኽንን ተልእኮ የተቀበሉት ሐዋርያት የተልእኮዋን ምሥጢርና አደራ፣ መንፈሳዊ ጸጋ እና ሥልጣን ብቻ ሳይሆን እውነተኛ መገለጫዎቿንም ሳይቀር አብረው ተቀብለዋል። ስለዚህ ይኽ ሁነኛ ማንነቷ መቀየር አይችልም።

2. መዐርገ ኤጲስ ቆጶስ በሐዲስ ኪዳን

ስለ ኤጲስ ቆጶሳት የሐዋርያት ሥልጣን ወራሽነት ያለን ግንዛቤ በአዲስ ኪዳን የተገለጠው በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኢየሩሳሌም በተደረገው የሐዋርያት ጉባዔ ነው። አስቀድሞ የክብር ባለቤት የሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን መርጦ የትንሣዔ ምስክሮች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው (ዮሐ 20፡21 የሐዋ 1፡8)፡ በዚህ አይነት እነርሱ የቤተክርስትያን መሠረቶች ሆኑ (ኤፌ 2፡20)። ለዓለም ሕዝብ ሁሉ ወንጌል እንዲያበስሩ ላካቸው (ማቴ 28፡19)፤ "የማሰር" እና "የመፍታት" ሥልጣን ሰጣቸው (ማቴ 18፡18)። መንጋውን እንዲጠብቁ አደራ ሰጣቸው፣ ከዚያም የተልኮውን ኃይል መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው። የመጨረሻው ሐዋርያ ከዚህ ዓለም ቢለይም የሐዋርያት ተልእኮ አላቆመም፤ የሐዲስ ኪዳን አዋጅ እና ምስክርነት በተከታዮቻቸው ኤጲስ ቆጶሳት ቀጠለ። በሐዋርያት ዘመን የነበረው ሐዋርያዊ አገልግሎት እና ሥልጣን በተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታዎች እና አገልግሎቶች ይገለጥ ነበር (ሮም 12፡4-8፣ ኤፌ 4፡11 ፊል 1፡1፣ ዕብ 13፡7፣ቲቶ 1፡5-8)። ይኽም ሥርዓት ሰው ሠራሽ ሳይሆን አስቀድሞ ጌታችን ለሐዋርያት የሠራላቸው ሥርዓት ነው። የሐዋርያት ተከታይ የሆነው የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ አግናጢዮስ እነዚህን ሦስቱ መዐርጋት የጳጳሳት፣ ካህናትና ዲያቆናት ሥልጣን ተዋረድ እንደ ሐዋርያት መዋቅር በቤተክርስትያን ውስጥ በሚሰጠው ክህነታዊ አገልግሎት ተጠብቀው መቆየታቸውን አስረድቷል። ጳጳሳት በአብያተ ክርስትያናት ላይ ሐዋርያዊ ሥልጣን ያላቸው የሐዋርያት ተተኪዎች ናቸው። በዚህም በአብያተ ክርስትያኖቻቸው ዘንድ በሐዋርያት እምነት አንድነትን ለማስጠበቅ እና ለክርስትና ሕይወት ግዴታዎች ታማኝ በመሆንና

ሐዋርያት እንዳስተማሩት በመኖር የሐዋርያትን ትውፊት የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።

ብፁዓን ጳጳሳት የአገልግሎት ሥልጣናቸውን የሚቀበሉት በምእመናን ጉባኤ በሚፈፀመው የምሥጢረ ክህነት፣ ሥርዐት ነው። በሢመቱ መሠረት ኤጲስ ቆጶሱ የአንድ ሀገረ ሰብከት ወይም ቤተ ክርስቲያን በምትመድበው የአገልግሎት ዘርፍ ሐዋርያዊ ተልእኮውን ይፈጽማል፤ ምደባው በርሱ ፈቃድ እና ስምሪት ሳይሆን ተልእኮውን የምትሰጠው የሾመችው ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት። የጳጳሱ አገልግሎት ፍጹም ትኩረቱ የሚፈልግ፣ ዓላማው የማይናወጽ ሰማያዊ ሀብትንና ዘለዓለማዊ ድኅነት የማስተማር፣ የመቀደስ እና የማስተዳደር አገልግሎት፣ የሃይማኖትን ንጽሕና ከክህደትና ከኑፋቄ እንዲሁም ከቁሳዊ አስተሳሰብ እንዳይበረዝ ራሱንም መንጋውንም መጠበቅ ነው። ስለዚህ መዐርገ ኤጲስ ቆጶስ በምእመናን መካከል የትልቅ አገልጋይነት እና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምልክት ነው።

በትርጉም ደረጃ ስናየው ኤጲስ ቆጶስና ወይም ጵጵስና በሐዲስ ኪዳን ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተሠጠ ሥልጣን መሆኑን እና የመጨረሻው ሥልጣነ ክህነት ነው። ኤጲስ ቆጶስ ἐπίσκοπος ጠባቂ፣ እረኛ ማለት ሲሆን ትርጉሙ ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተመርጠው በከፍተኛ ሥልጣነ ክህነት አገልግሎት እንዲሠጡ የተሾሙ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎችንና መሪዎችን፣ በሁሉም ጉዳይ ላይ ኃላፊነት ያላቸውን አበው ይመለከታል። ይህ መዓርግ በሥልጣነ ክህነት የሚወረስ የሐዋርያዊ ትውፊት Apostolic Succession መሠረት ነው። በሐዲስ ኪዳን ἐπίσκοπος የቤተ ክርስቲያን ዐቢይ ካህን ማለት ነው። በቋንቋ ትርጉሙ ግን ኤጲስ ቆጶስ ማለት ከሁሉ በላይ ሆኖ የሚጠብቅ ማለት ነው። ኤጲስ ቆጶስና በአንድነት በሚመሠረቱት ጉባኤ ሐዋርያት እና በሚኖራቸው ፍጹም መንፈሳዊ ተልእኮ የሐዋርያት ሥልጣንና የቤተ ክርስቲያን ሉዓላዊነት መገለጫ ሆኗል። በሥርዓተ አምልኮትም ሁሉንም የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የሚፈጽሙ ሲሆኑ በቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ አገልግሎት (ማለትም የመንፈሳዊ፣ የሀብት፣ የንብረት፣ የሰው ኃይል፣ የመሳሰሉት ሁሉ) በበላይነት የሚመሩ፣ የሚያስተዳድሩና የሚጠብቁ ናቸው። የኤጲስ ቆጶስና ሥልጣን ከአንዱ ትውልድ ወደ ቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፍበት ቀኖናዊ ሥርዓትም ከሐዋርያዊ የሥልጣነ ክህነት መውራረስ ጋር ተያይዞ የሚፈጸም ነው። ይሁን እንጅ ይኽ ሥልጣን ሲኖዶሳዊ ስለሆነ የተናጠል ተልእኮ ያለው እና በራስ ፈቃድ የሚታዘዝበት አይደለም። በጳጳሳት መካከል ያለው ሐዋርያዊ ሕብረት የሚገለጠው በቤተክርስትያን ውስጥ ባለው ሲኖዶሳዊ ባሕርይ ነው። ይኽም የሐዋርያት ጉባኤ ነጸብራቅ ሲሆን በሁሉም አርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እስከ አሁን የተጠበቀ ትውፊት ነው።

3. የጥንታዉያን አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የጋራ ትውፊት

መዐርገ ኤጲስ ቆጶስ መሠረት በሁሉም ጥንታዉያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ አንድ ዓይነት ነው። በሁሉም የምሥራቅ እና የኦሪንታል አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ሐዋርያዊ መሠረት እንዳለው፣ መሥፈርቱና የሢመት ሥርዓቱ፣ ተልእኮው እና የሥልጣን ደረጃው፣ የሚፈጽማቸው ዓበይት ተግባራትም ሆነ ዋጋው ወይም አስቡ አንድ ዓይነት ነው። በዘመን ሂደት እና በየአብያተ ክርስቲያናቱ በየጊዜው እየዳበሩ በመጡ የአፈጻፀም ደረጃዎች መስፋት እና መጥበብ ምክንያት መሠረቱ ሳይለቅ የተወሰኑ መንፈሳዊ ባህሎችና ልማዶች ዳብረው

ይገኛሉ። ኦርቶዶክሳውያን በሆኑት በሁሉም ጥንታዉያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ቀደምት የቅዱስት መጻሕፍት ድንጋጌዎች እና የአበው ቀኖናት በተለይ የጉባኤያት ቀኖናት ሳይለወጡ እንዳሉ ተጠብቀው ይገኛሉ። የሐዲስ ኪዳን ተጨማሪ የቀኖና መጻሕፍት ውስጥ በተለይም ዲድስቅልያ፣ አራቱ ሲኖዶሳት (አብጠሊስ፣ ትእዛዝ ግጽው እና ሥርዐተ ጽዮን) መልእክታተ ቀለምንጦስ (ረስጠአ፣ ረስጠብ፣ ረስጠጅ) እንዲሁም ኪዳን ዘእግዚእ ሁነኛ ምንጭ ናቸው። ከታወቁት ጉባኤያት ወይም ዐበይት ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ዘኒቅያ፣ ወቁስጥንጥንያ ወኤፌሶን የተገኙት፤ ድምራቸው 35 ቀኖናት ሲሆን አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ይጨምራል። በእነዚህ ሦስት ጉባኤያትም ከታወቁት የመሠረተ እምነት ትምህርቶች በተጨማሪ የጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት መዐርግ፣ የመናብርት ቁጥርና መቀመጫ ተወስኗል። በዚህ ውሳኔ መሠረትም ለምሳሌ ማንኛውም መንበር ከጌታችን ሐዋርያት መዋዕለ ስብከት ጋር ብቻ እንዲያያዝ ተወስኗል። ይኽም በመሆኑ በዓለም ያሉ መናብርት በሙሉ ሥያሜአቸው ከዐሥራ ሁለቱ የጌታችን ሐዋርያት አልወጣም። መናብርቱ መንበረ ጴጥሮስ፣ መንበረ ማርቆስ፣ መንበረ ያዕቆብ፣ መንበረ ታዴዎስ፣ መንበረ ቶማስ እየተባሉ ይጠራሉ ተጠሩ እንጅ ከሐዋርያት በኋላ በመጡ ደኃርት ሊቃውንት እና ጳጳሳት የሚጠሩ መናብርት የሉም።

ከሦስቱ ዐበይት ዓለም አቀፍ ጉባኤያት በተጨማሪ እስትግቡዕ ቀኖናት ዘንዑሳን (የአካባቢ) ሲኖዶሳት የተባሉ የዕንቆራ፣ ቅርጣግና፣ የግንግራ፣ የአንጾኪያ፣ የሎዶቅያ፣ የስርድቅያ እና በኋላ ዘመን በትንሹ ጉባኤ የተደረገበት ኒቅያ ጉባኤያት ውሳኔዎቹ የኤጲስ ቆጶሳትን ሢመት፣ ተልእኮና አደረጃጀት፣ የአህጉረ ስብከትን አሰያየም፣ የተጠሪነት እና የመዐርግ ቅደም ተከተሎችን፣ የምሥጢራት አፈጻጸም እና የተልአኮዎች ሥምሪት ተወስነዋል። በዘመነ ሰማዕታትና ሊቃውንት ዓለማውያን ገዥዎች የዚህን መንፈሳዊ ሥልጣን ምንነት ለመረዳት እና በቁጥጥራቸው ሥር ለማስገባት ጥረት በሚያደርጉበት ዘመን ከሐዋርያት በኋላ የተነሡ ሐዋርያውያን አበው እንደ ቅዱስ አግናጥዮ ስ ምጥው ለአንበሳ፣ እንደ ቅዱስ ጎርጎሪዮስ ባሄብ ፈወዝ (ሕንድ)፣ ቅድስ አቡነ ገብርኤል ኢብን ቱሪይቅ፣ ቅዱስ አቡነ ሚካኤል ዘድምያጥ፣ ቅዱስ መቃርዮስ መነኰስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ ጸዋሚ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ አቡሊዮስ፣ ቅዱስ ባስልዮስ፣ ቅዱስ ዲዮናስዮስ፣ ቅዱስ አቡነ ጎርጎርዮስ እና ቅዱስ አቡነ ጢሞቴዎስ የሰጧቸው ማብራሪዎች እና ትምህርቶች በሁሉም ጥንታውያን ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲናት ዘንድ እስከ አሁን ሳይዛነፉ ተግባራዊ ይደረጋል። በሁሉም አብያተ ክርስቲናያት ዘንድ ኤጲስ ቆጶሳት ከደናግል መነኰሳት ተመርጠው ይሾማሉ። መሥፈርቶቹ እግጅ ጥብቅ እና በከፍተኛ ጥንቃቄ ተግባራዊ ይደረጋሉ። ለመዐርገ ኤጲስ ቆጶስ የሚሰጠው ትከረት በሁሉም ዘንድ አንድ ዓይነት ነው።

የኤጲስ ቆጶስ ሥልጣን ሁሉንም ምሥጢራት የሚፈጸም መሆኑ፣ የመሪነቱ፣ የመጋቢነቱ፣ የአርዓያነቱ፣ ዋና ዋና ተግባራት በሐዋርያዊ ተልእኮ ፈጻሚነቱ አንድ ዓይነት ነው። በሃይማኖቱ ጽኑ የሆነ እና ሃይማኖቶን ጠብቆ ለማስጠበቅ ብቁ መሆኑ የተረጋገጠ፣ አካላዊ ጤንነት፣ አእምሮአዊ መረጋጋት፣ የአንደበት ቁጥብነት፣ ብስለት እና አስተዋይነት፣ ሰላማዊና አስታራቂነት፣ መንፈሳዊ ሰብእና፣ ያለው መሆኑ ጥንታዊ መሥፈርት ነውና አይለወጥም። በምግባሩ ለምእመናን እና በሥሩ ለሚላላኩ ቀሳውስት እና ዲቆናት አርኣያነት ያለው መሆኑ

እንደሚገባው፤ በምንኩስናው ፍጹም መናኝ፣ የሆነ የሁሉ አባት ሊሆን የሚችል ሰው መምረጥ እንደሚገባ በሁሉም ዘንድ በወጥነት ተግባራዊ የሚደረግ ትውፊት፣ ሕግ እና ቀኖና ነው።

ሁሉም አርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ቅድመ ሚመት፣ ጊዜ ሚመት፣ እና ድኅረ ሚመት ያሉ ቀኖናትን በጥንቃቄ ያከብራሉ፡ ፡ ብቁ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር እንኳ የሚሸሩባቸው በትንሹ ፭፭ የሚሆኑት መሥፈርቶች አንድ ዓይነት ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች አልፎ አልፎ ከሚታዩ የአደረጃጀት መስፋት እና የሥያሜ ቅደም ተከተል ጋር ከብዙ በጥቂቱ ለማሳየት ያህል አጭር መግለጫን አቀርባለሁ፡

4. የኦሪንታል አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ትውፊት

በእስክንድርያ ኮፕቲክ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መዐርገ ኤጲስ ቆጶስ የሐዋርያት ሥልጣን ወራሽነት በመሆኑ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ የሐዋርያት ትውፊት ቀጣይነት ምልክት ነው። በአሌክሳንደርያ ኮፕቲክ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ አበው መነኰሳት ወደ መዐርገ ኤጲስ ቆጶነት ለመምጣት መሠረታዊ ከሆነው የምንኩስና ደረጃ በተጨማሪ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ዕውቀቶችን በሚገባ መማር አለባቸው፤ በአብዛኛው ትምህርቱ የቤተ ክርስቲያን ቢሆን ወቅታዊና ሕዝባዊ ዕውቀትንም ተምሮ መገኘት ግድ ነው። እምነታቸው የቀና፣ በምግባራቸው የተመሰከረላቸው መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የትምህርት ብቃታቸው በሚገባ ይመዘናል። በትምህርታቸው ብቁ ሁነው መገኘታቸው ከተረጋገጠ በኋላ መንፈሳዊ አገልግሎትን በየደረጃው ማከናወናቸው በድጋሜ ይታያል ይህም ትልቅ ሚዛን ይሰጠዋል። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ የሚሾም ዓቢይ አገልጋይ ውስጧን በሚገባ ሊያውቅ ይገባል። በግብጻውያን ዘንድ ከጥንት ጀምሮ አንድ ተወዳጅ አባባል አለ፤ የሚሾም ሰው ራሱን ለክርስቶስ አሳልፎ የሰጠ፣ ምእመናንን ለመመገብ የበቃ፣ ከዚህ ዓለም ምድራዊ ትሥሥር የጸዳ ሊሆን ይገባዋል። በእስክንደርያ አበው መነኰሳት የሀገረ ሰብከት ጳጳስ፣ የትላላቅ ከተሞች ሜትሮፖሊታን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ረዳት ጳጳስ፣ ሁለገብ ጳጳስ፣ ሱፈጋን ጳጳስ፣ የታላላቅ ተቋማት ጳጳስ ሁነው ሊሾሙ ይችላሉ። መዐርገ ኤጲስ ቆጶስ በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በልዩ ጥንቃቄ ለእያንዳንዱ ሹመት ተገቢው መሥፈርት ወጥቶለት የሚከናወን ሹመት ነው፡ ፡ አንድ ሰው ከመሾሙ በፊት ለሚሾምበት ቦታ ብቃቱ ይታያል። ይሕም ማለት ተመሳሳይ መሥፈርት ለሁሉም እንዳለ ሁሉ ዕጩው አባት በተለየ ሁኔታ እንዲሾም ለተመረጠበት ቦታ ደግሞ ብቃቱ ይታያል። አንድ አባት በተሾመበት ኃላፊት እስከ ዕለተ እረፍቱ ድረስ ሊቆይ ይችላል አንዳንድ ጊዜም ይገደዳል። ለምሳሌ የሀገረ ሰብከት ጳጳስ ወይም ሊቀ ጳጳስ እስከ ዕለተ እረፍቱ ድረስ መቆየት ግዴታ ነው፡ ፡ ይኽ እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም በድጅስና መዐርግ ውስጥ ያሉ ደረጃዎች በራሳቸው በሥፍር በሚመዘን መሥፈርት ብቻ ከመዐርግ ወደ መዐርግ መሸጋገር ይቻላል።

አዲስ ሀገረ ሰብከት የሚመሠረተው በራስዋ በቤተ ክርስቲያኒቱ መሥፈርት ነው፡ ፡ ይኽም በአብያተ ክርስቲያናት፣ ቀሳውስት፣ ተቋማት፣ የአማኞች ብዛትና አሠፋፈት የወንጌል ሥርጭት ይወሰናል። አዲስ ሀገረ ሰብከት ሲመሠረት ወዲያው ጳጳስ ይሾማል፤። በነባር

አህጉረ ሰብከት ያሉ ጳጳሳት ወይም ሊቃነ ጳጳሳት በእረፍት ሲለዩ ወዲያው ሲኖዶስ ተሰብስቦ መንበሩ ሳይውል ሳያድር አዲስ ጳጳስ ለቦታው በሚፈለገው መሥፈርት መሠረት ይሾማል። ለምሳሌ በቅርቡ የኢሩሳሌም የኮፕቲክ ሊቀ ጳጳስ ሲያርፉ ወዲያው ሲኖዶስ አዲስ ጳጳስ ሾሟል። የሚመት መስፈርቶቹ በሙሉ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሐዋርያዊ ተልእኮ ለማከናወን የሚያበቁ ናቸው፡ በሂደቱ ወሳኙ አካል ቅዱስ ሲኖዶስ ቢሆንም ሊቃውንት፣ ገዳማውያን እና ተአማኒነት ያላቸው ምሁራን ይሳተፋሉ። በሕይውት ያሉት ሊቀ ጳጳስም የሚተካቸውን ሰው ከሥጋዊ ወይም ወገናዊ መሥፈርት በጸዳና ተአማኒ በሆነ መንገድ ሊያዘጋጁ ይችላሉ። ሁሉም ጳጳት ከመሾማቸው በፊት ሰፊ ጊዜ የወሰደ ሥልጠና፣ የተግባር ልምምድና መንፈሳዊ ዝግጅት ያደርጋሉ፤ ከተሾሙም በኃላ በየጊዜው የወቅታዊ መረጃ ሥልጠና፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይቶች፣ የአዳዲስ አሠራሮች ልምምድ በየጊዜው ለዚሁ በተዘጋጀው ገዳም እየገቡ ይሰለጥናሉ፤ በጽሙና ይወያያሉ፣ ራሳቸውን ያበቃሉ።

በሶርያ ሐዋርያዊት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ በቅዱስ ያዕቆብ ዘንጽቢን፣ በተለይ በሶርያ ግዛት የሚታወቁት የቆጶዶቅያ አባቶች ቅዱስ ባስልዮስ፣ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙና ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ በሰፊው ያስተማሩት ትምህርት እስከ አሁን እንደተጠበቀ ነው። የሶርያ ቤተ ክርስቲያንን ጥንታውያን የአበው ትውፊት ጠንቅቆ ማወቀ ለመዐርገ ጴጵስ ቆጶስነት ወሳኝ ነው። በአሁኑ ዘመን መደበኛው የሥራ ቋንቋ አረብኛ ቢሆንም የሶርያ ቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑ ለምሳሌ በሕንድ የሚኖሩ ሕንዳውያን ከሦስት በላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ያላቸው፣ በመካከለኛው ምሥራቅም የኩርድ፣ የፍልስጥኤም፣ የዘዲ ጎሣዎች ቢኖሩም የጥንቱን የሶርያን ቋንቋ (ሱርስት) ማወቅ ግድ ነው። ምክንያቱም ቅዳሴዎቹና የማኅሌት ድርሰቶቹ፣ የጸሎት መዛግብቱ መቶ በመቶ በሶርያ ጥንታዊ ቋንቋ የተጻፉ ናቸው። በርግጥ በአሁኑ ጊዜ በርካታ መጻሕፍት ወደ አረብኛ እና የሕንድ ማላለም ቋንቋ ቢተረጎሙም ሶርያውያን የጥንቱ ቋንቋቸው ክርስቶስ ያስተማረበት አረማይክ-ሱርስት ነው ብለው ሰለሚያምኑ በሶርያ ቋንቋ መቀደስ፣ መጥቀስ፣ መጸለይ ዋና የሊቅነት መሥፈርት ነው። ከዚሁ ጋር ተያያዘ ወደ መዐርገ ኤጲስ ቆጶስ ለመምጣት በርከት ያሉ ትምህርቶችን መቅሰም ግዴታ ነው። በርካታ የሶርያ ጳጳሳት በአሁኑ ጊዜ ሐኪሞች መሐንዲሶች፣ የሒሳብና መዝገብ አያያዝ፣ የቋንቋ እና የሥነ ባህርይ ባለሙዎችም ናቸው። በሶርያ ቀኖና ዋናዎቹ ከላይ የተዘረዘረት እንደተጠበቁ ሁነው ኤጲስ ቆጳሳት በርካታ ኃላፊነት አለባቸው፣ መንፈሳዊ ሐዋርያ ብቻ ሳይሆኑ ማኅበራዊ አገልጋዮች አስታራቂ ሽማግሌዎች፣ የሕዝብን ደኅንነት የሚጠብቁ፣ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት እና ታሪካዊነት ትልቅ ቦታ የሚሰጡ መሆን አለባቸው። በሶርያ ቤተ ክርስቲያን እንደ እስክንድርያ ሁሉ ጳጳሳት፣ ሊቀ ጳጳሳት፣ ሜትረፖሊታን ይገኛሉ። በሕንድ ሀገር ያሉት የሶርያ መንበር ጳጳሳት አለቃ በሊቀ ጳጳስ ደረጃ ይኖራሉ። ተጠሪነታቸው ለአንጾኪያ በዐለ መንበር ፓትርያርክ ነው። ይኽ የማላንካራ ሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን አይጨምርም፡ ፡ በሶርያ በአንድ ወቅተ በአሌፖ ገዳም ለወደፊቱ ጳጳሳት የሚሆኑ አባቶችን በድብቅ በከፍተኛ መንፈሳዊ ጥብኣትና ተጋድሎ ያሰለጥኑ ነበር። ይኽም በአረቦች ከሚደርስባቸው ስደት የተነሣ

ነበር፡፡ የሶርያ መንበር የምሥራቁን የሮም ግዛት ሁሉ የሚመለከት መንበር ስለነበር ከሶርያ አልፎ እስከ ፋርስ እና እስያ ድረስ ሐዋርያትን እያሰለጠኑ ይልኩ ነበር፡፡ ስለዚህ መዐርገ ኤጲስ ቆጶስነት ከተዘዋዋሪ ሰባኪና ሩቅ ሀገር ሂዶ ከማስተማር የተያያዘ ወንጌል ባልደረሰበት ቃለ እግዚአብሔርን ከማድረስ ጋር የተያያዘ ነው፡ ፡ ሶርያውያን ጳጳሳት ስማቸውን ሲጠሩ “ማር” የሚል ቃልን ይጠቀማሉ ትርጉሙ ቅዱስ፣ ብፁዕ፣ ክቡር ማለት ነው፡፡ ማር ጊዮርጊስ፣ ማር ቂርቆስ፣ ማር ይስሐቅ እንዲል፡፡

በአርመን ሐዋርያዊት አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መዐርገ ኤጲስ ቆጶስ የክርስቶስ እንደራሴ፣ የምእመናን ሁነኛ ጠባቂ እረኝነት ነው፡፡ ለዚህ መዐርግ የሚበቃ ሰው እጅግ ብዙ የተሰጠው እንደመሆኑ መጠን ብዙ ይጠበቅበታል፤ የሃይማኖት ምሥጢራትን ይህ ቀረህ ሳይባል ሊያውቅ ይገባል፡፡ የሃይማኖት ጠባቂ፣ የምእመናና እረኛ፣ የሕዝብ መከታ፣ አገልጋይ፣ አባት፣ መጋቢ፣ ዳኛ፣ መሪ ነው፡ ፡ ታዋቂው የአርመን አስተማሪ ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ ፖሎዲያን ሲናገሩ “አርመኖች ጳጳሳት በጣም ያከብራሉ ሁሉንም የሚፈልጉትን ነገር እንዲያደርጉላቸው ይጠብቃሉ” ብለዋል፡፡ በአርመኖች ዘንድ ከጥንታውያኑ ቀኖናዎች በተጨማሪ አርመናውያን አበው ጠብቀው ያስፋፉት ከታወቁት በተጨማሪ ጥብቅ ቀኖናዎች ይገኛሉ፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ከሣቴ ብርሃንና ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘናሬግ፣ ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የአርመን ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሰሜናዊውና ከቂልቅያ ባሻገር ያለው በሮም ግዛት ሥር ስላልተገዛ፤ በሮም ግዛት የመናብርት ተጠሪነት አይመለከተውም ነበር፡ ፡ በዚህም ምክንያት በስም አጠራርም ሆነ በአህጉረ የአህጉረ ሰብከቱ አከፋፈሉ ከጥንት ጀምሮ የሮምን ግዛት አደረጃጀት አልተከተለም፡፡ አርመኖች ለረጅም ጊዜ በነፃነት የኖሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስትናን ብሔራዊ ሃይማኖታቸው ያደረጉ ስለነበሩ ሀገራዊ ማንነታቸውና ሃይማኖታዊ ክብራቸውን በአንድነት ይዘው ኖረዋል፡፡ በርካታ ወረራና መከራን ሲመጣም መዐርግ ጵጵስናው ከፍተኛ ችግር ሲገጥመው እንኳ ሀገራቸውና ሕዝባቸው ሳይከፋፈሉ የተጠኑ ዘዴዎችን በመጠቀም በስደት እና በሀገር ውስጥ የግንኙነት ሰንሰለት በመፍጠር የቤተ ክርስቲያናቸውንም የሀገራቸውንም አንድነት ጠብቀው ኖረዋል፡፡ የአርመኖች የመዐርገ ኤጲስ ቆጶስ ሢመት የጥንቱን ያልለቀቀ ቢሆንም የራሳቸው ለየት ያለ ያለባበስ እና የክብር ሥርዓት አላቸው፡፡

በሕንድ ማላንካራ ቤተ ክርስቲያን የሥልጣነ ኤጲስ ቆጶስ አሠያየም ሙሉ ለሙሉ እንድሶርያቤተክርስቲያንነው፡፡ሊቀጳጳስ፣ጳጳስ፣ ሜትሮፖሊታን ሲሾሙ የሚከቱሉት መሥፈርት ከሶርያ የተወሰደ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የአህጉረ ሰብከት አሰያየማቸው እና አከፋፈሉ የራሳቸውን ሚዛን ይከተላሉ፡፡ ለጵጵስና ሹመት የአህጉረ ሰብከት መደራጀት ወሳኝነት አለው፡፡ አህጉረ ሰብከት ሲያደራጅ በቁጥርም ሆነ በስብጥር በሕገ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተቀመጠው መሥፈርት ሙሉ ለሙሉ መሟላት አለበት፡፡ የሀገረ ሰብከቱ የምእመናንን፣ የአገልጋይ ቀሳውስት፣ የወጣቶች ቁጥር የተመጣጠነ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ በቁጥሩ መሠረት ምርጫ ይከናወናል፡፡ በማላንካራ ትውፊት መሠረት ለምርጫ የሚቀርበው አባት ለሚሾምበት ሀገረ ሰብከት ብቃቱ ብቻ ሳይሆን ተቀባይነቱም በመጠኑ ይታያለ፡፡ ይኽም በሕገ ቤተ ክርስቲያን የተደነገገ ነው፡፡ ዕጩ ኤጲስ ቆጶስ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ያልተማሩት ሊኖር አይገባም፤ ሁሉንም ምሥጢራት የመፈጸም፣ ሁሉንም አገልግሎት የማዳረስ ዕውቀትና መንፈሳዊ ስጦታ ይጠበቃል፡፡

5. መዐርገ ኤጲስ ቆጶስ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት

በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የቤተ ክርስቲያን ቅርጽና መዋቅር የሚወስነው መዐርገ ኤጲስ ቆጶሳት ነው፤ ሀገረ ሰብከትን ስፋት፣ የመንበረ ጵጵስናን ደረጃ፣ የስብከተ ወንጌልን መስፋፋት መገለጫም ነው፤ አዲስ መንበረ ጵጵስና መመሥረት ማለት በዚያ ቦታ እየተስፋፋ ስላለው የወንጌል አገልግሎት እና የድኅነት ተልእኮ ምስክር ነው፤ ይኽም በከፍተኛ ጥንቃቄና ጥብቅ በሆነ ቀኖና ይከናወናል። የቀኖና ምንጮቹና ሥርዓቱ በኦሬንታል ከሚደረገው ሥርዓት አይለይም፤ ቅድመ ሢመት ተገቢው ሃይማኖታዊ፣ የሥነ ምግባር፣ የቀኖና፣ የብሕትውና፣ የዕውቀት ብቃቶች ይታያሉ። በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን በምርጫ ሂደት ውስጥ ይደረግ የነበረው የሁሉንም የቤተ ክርስቲያን አባላት ያሳተፈ ተግባር በሂደት እንደ ኦሬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ ለሙሉ ሲኖዶሳዊ ሆኗል፤ ምርጫውም ሢመቱም በቅዱስ ሲኖዶስ ወይም ጉባኤ ጳጳሳት ይወሰናል። በሲመቱ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እና በዐውደ ምሕረት ይከናወናል። በእያንዳንዱ ጸሎት መጨረሻ እኛ እንደምናደርገው ቀሳውስት እና ሕዝብ ሁሉ “ይደልዎ/ይገባዋል፤ ይደልዎ/ይገባዋል፣ ይደልዎ/ይገባዋል (Ἄξιος, Ἄξιος!/Ἄξιος, Ἄξιος!/Ἄξιος, Ἄξιος!/Ἄξιος,)” ይላሉ ይኽም የማጽደቅ እና በይሁንታ የመቀበል ማረጋገጫ ነው።

በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ሥልጣነ ክህነትን የመስጠት ምሥጢር የሐዋርያት ውርስ ማረጋገጫ፣ የቤተ ክርስቲያን አንድነት ማስጠበቂያ ነው፤ የቤተ ክርስቲያን የድኅነት ተልእኮ ቀጣይነት፣ የመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ማእከልም ነው። ስለዚህ የጳጳሳት ዋናው የአስተዳደራዊ ሥራ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ከአጥቢያ እስከ ሀገረ ሰብከት እንዲሁም በሁሉም አህጉረ ሰብከት መካከል ተናቦና ተሣሥሮ እየተፈጸመ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። ይኽ ምሥጢር ትልቁ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢር ስለሆነም “የአንብሮተ ዕድ ምሥጢር” ይሉታል።

6.ጳጳስ፣ ሊቀ ጳጳስ፣ ሜትሮፖሊታን፣ ኤግዛርኬት፣

በመዐርገ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ጵጵስና ውስጥ ጳጳስ፣ ሊቀ ጳጳስ፣ ሜትሮፖሊታን፣ ኤግዛርኬት እና ይህን የመሰሉ ሥያሜዎች በየአብያተ ክርስቲያናቱ ጥቅም ላይ ይውላሉ። ሌሎችም ረዳት ሊቀ ጳጳስ፣ ሱፈጋን ሊቀ ጳጳስ፣ ኮሬ ኤጲስ ቆጶስ የሚሉ እንደየትውፊት ይገኛሉ፡ ዋናው ነገር የቃላቱ አመጣጥ እና አጠቃቀም የየራሱ ሰፊ ታሪክ እና ትርጉም ቢኖረውም በአሁኑ ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውሉ ለየራሳቸው የሚወክሉት መሠረታዊ ተግባር አለ። አንዳንድ ጊዜ የመዐርግ ቅደም ተከተልን፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ በሢመት ለረጅም ጊዜ ማገልግልን፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ የሚሾሙበትን ቦታና ክብር ወክሎ ተገኝተዋል።

ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ የመዐርጉ መጀመሪያ እና ዕጩ ሆኖ የቀረበው መነኩሰ አባት በተሾመ ጊዜ የሚሰጠው ሥያሜ ነው፡ ከጥንት ጀምሮ ይኽ ሥያሜ የሚያመለክተው የመጨረሻውን የሥልጣነ ክህነት መዐርግ ነው። ሊቀ ጳጳስ ወይም ሊቀ ኤጲስ ቆጶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ ዋለው ከሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ በተለይም ከጉባኤ ኒቅያ (325 ዓ/ም) በኋላ እንደሆነ በሁሉም ጥንታውያን ኦርቶዶክሳውያን ዘንድ ይታመናል። የግሪኩ

አርኺኤጲስቆጶስ “αρχιεπίσκοπος” የጳጳስ አለቃ ማለትን ያመለክታል። በዚህ መሠረት ሊቀ ጳጳስ ካለ አንድ ኤጲስ ቆጶስ በመዐርግ ከፍ ማለቱን ብቻ የሚያሳይ ሲሆን፤ ሊቀ ጳጳሳት ካለ ግን የሚወክለው ፓትርያርክን (ርዕሰ-አበውን) ነው። ቃሉ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የበላይነትን ከማሳየት በተጨማሪ አንዳንድ ጥንታውያን መንበሮችን በዚህ ሥያሜ ሲጠሩ ይታያል። መንበረ ጵጵስና እንደሚለው ሁሉ መንበረ ሊቀጵጵስና የሚልም ይገኛል።

ሜትሮፖሊታን የመጀመሪያው ሕዝባዊ ትርጉሙ የከተማ ነዋሪ ማለት ሲሆን፣ በሂደት በቤተ ክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት በተለይም የመዐርገ ኤጲስ ቆጶስን መሠረት አድርጎ ጥቅም ላይ ሲውል ከሕዝባዊ ትርጉሙ ለመለየት ሜትሮፖሊታን ጳጳስ ወይም ሜትሮፖሊታን ሊቀ ጳጳስ በማለት እያገለገለ ይገኛል። በግሪክና ሮማውያን ወግ አንድን ከተማ ትልቅ እና የሰለጠነ ነው ለማለት ከሚሰጡት መሠረታዊ መለኪያ ውስጥ ብዙ ቋንቋ የሚነገርበት፣ በርከት ያለ የሕዝብ ስብጥር ያለው፣ ሰፊ እና ያልተቋረጠ እንቅስቃሴ የሚደረግበት፣ የደራ ገበያ ያለው ከሆነ ሜትሮፖሊታን Μητροπολίτης ነው ይላሉ። በቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓይነት ቦታ የሚሾሙ ኤጶስ ቆጶሳትን በዚህ ሥያሜ የተጠሩት ከዚህ በመነሣት ነበር። በሂደት ግን ወደቀኖናዊ ሥርዓት በመግባቱ በአንዳንድ ቦታዎች ሜትሮፖሊታን ሊቀ ጳጳስ ራሱን ችሎ መደበኛ ትርጉም ተሰጥቶት አንዳንድ ጊዜ ከሊቀ ጳጳስት የበለጠ፣ እንደ ሩሲያና ቡልጋርያ በሌሎች የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ደግሞ ከሊቀ ጳጳስ በታች ሆኖ ይገኛል። በእስክንድርያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ እና በሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሜትሮፖሊታን በሥሩ የአህጉረ ስብከት ጳጳሳት ወይም ረዳት ጳጳስ ሊኖራቸው ይችላል። በሀገራች ሊቀ ጳጳስንን የምንጠቀም ሲሆን ለሊቀ ጳጳስነት የሚያበቃው መለኪያ እንደሌሎቹ አይደለም፤ ሜትሮፖሊታን ጳጳስ/ሊቀጳጳስ የሚለውን እስከ አሁን አንጠቀምም። በሶርያ አንጾክያና በሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተመሳሳይ አጠቃቀም ያለው ሲሆን፤ በማላናካራ የማላንካራ ሜትሮፖሊታን የቅዱስ ፓትርያርክ/ካቶሊኮሱ ሥልጣን ነው፡ ይኽም በተጨማሪ እና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ወይም ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸደቀ ሥያሜ ነው።

7. መንበረ ጵጵስና፣ መንበረ ሊቀ ጵጵስና

የሀገረ ስብከት ጳጳሳት ወይም ሊቀ ጳጳስ የሚኖረው በመንበረ ጵጵስና ነው። በሀገራችን ከጥንት ጀምሮ አበው ሊቃነ ጳጳሳት የሚኖሩበትን ቤት “አቡን ግቢ/ቤት/” ማለት የተመለደ ነበር። የሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤቱ የሊቀ ጳጳሱ ወይም የጳጳሱ ሐዋርያዊ ተልእኮ የሚፈጽበት ቦታ ነው፡ ይኽም መንበረ ጵጵስና ይባላል። ቀደም ሲል ለመጥቀስእንደተሞከረው መንበረ ጵጵስና ወይም ሰፊ ከሆነ መንበረ ሊቀ ጵጵስና የሚመሠረትበት የራሱ መስፈርት አለው። በብዙ ቦታዎች ይኽ አመሠራረት በጣም በከፍተኛ ጥንቃቄ እና የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ መሠረት አድርጎ ይከወናል፡ በሥሩ ያሉት አጥቢያዎ፣ ገዳማት፣ መንፈሳዊ ተቋማት፣ አገልጋይ ካህናት፣ ምእመናን ሁሉ በአግባቡ ታይቶ ይሰየማል። ለምሳሌ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ለመባል የሚበቁ መሥፈርቶች በቃለ ዐዋዲ እንደተደነገጉ ሁሉ ሀገረ ስብከትን መንበረ ጵጵስና ወይም መንበረ ሊቀጵጵስና የሚያሰኙትም በሕገ ቤተ ክርስቲያን ይደነገጋሉ። ይኽም ተመጣጣኝ እና ወጥ ወይም ተቀራራቢ መሆኑ በአበው መካከል የሐዋርያዊ ተልእኮ መስፋትና መጥበብን መለኪያ ሆኖ ይቆጠራል። ሀገረ ስብከቱ ያለበት ወይም መንበረ ጵጵስና ያለበት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ካቴድራል ይባላል። ካቴድራል ማለት መንበረ

ጵጵስና እንደማለት ነው። መንበረ ጵጵስና ከዋናው መንበረ ፓትርያርክ ይለያል፤ መንበረ ፓትርያርክ በሐዋርያት ብቻ ሲሰየም መንበረ ጵጵስና በሕይወት እያገለገሉ ባሉት አባቶች ስም እስከ እረፍታቸው ድረስ ይጠራል። ከዚያ በሚተኩት ብፁዕ አባት .. እገሌ ዘ... ሀገረ ሰብከት ተብሎ ይጠራበታል።

8. ከሢመተ ጵጵስና (መዐርገ ኤጲስ ቆጶስ) የሚከለክሉ የጋራ መሥፈርቶች

ወደ ሢመት ሲመጣ እና በሥርዓተ ሢመት ጊዜ ያለውን አንድነት እና ብዙነት እንዳየነው ሁሉ በሁሉም ጥንታውያን የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ከመዐርገ ኤጲስ ቆጶስና የሚከለክሉ ጉዳዮችንም በአብዛኛው ይጋራሉ። የሃይማኖት ሕጻጽ፣ የሥነ ምግባር ጉድለት፣ የአገልግሎት ብቃት አለመኖር፣ ለሹመት ያልደረሰ ዕድሜ፣ በእምነት አዲስ መሆን፣ የተረጋጋ ሥነ ልቡና አለመኖር፣ ከገዥዎች ጋር ተሻርኮ ለመሾም መሞከር፣ ወይም ተሹሞ መገኘት፣ በመናፍቅ ወይም በከሀዲ ጳጳስ መሾም፣ ያለፈቃድ ወይም ትክክለኛ መመዘኛ መሾም፣ ጠባብ ጎሠኝነት ወይም አድሎአዊነት፣ የመሰሉት በሁሉም ዘንድ ከሢመት ይከለክላሉ። አንዳንዶቹ መሥፈርቶች ከጥንት ጀምረው የመጡ ሲሆን ሌሎች ችግር ሲፈጠር በጋራ የተወሰኑ ይገኙበታል። ለምሳሌ መፍቀሬ ጎሣ በግሪክ ቋንቋ Phyletism (an ecclesiological heresy territorially organized on an ethnic, racial, or cultural basis) ተብሎ ተተርጉሟል። ይህም ቤተ ክርስቲያንን ከዓለምአቀፋዊነቷ አውርዶ በጎሣ ሲያደራጁ የሚፈጠር ስሕተት ነው። ይሕንንም በአውሮፓ አቆጣጠር 1872 በቁስጥንጥንያ በተደረገ ጉባኤ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አውግዘዋል። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም መዐርገ ኤጲስ ቆጶስ የሁሉ አባትነት በመሆኑ ዕጩዎች ለአንድ ጎሣ ወይም አካባቢ ነን ብለው እንዳያስቡ የሚያደርግ ነው።

9. ማጠቃለያ

በዚህ አጭር ጽሑፍ እጅግ በጣም ጥልቅ እና መሠረታዊ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን አምድ እና የሰባቱ ምሥጢራት አካል ከሆነው ከምሥጢረ ክህነት ዋነውን እና የመጨረሻውን እርከን በጥንታውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ትውፊት ውስጥ መጠነኛ መረጃ ለመስጠት ነው፡ ፡ ከሥልጣነ ክህነት አንዱና ዋናው የሆነውን መዐርገ ኤጲስ ቆጶስና በነገረ ቤተ ክርስቲያን፣ በነገረ ድኅነት፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እና ቀኖና ውስጥ ያለውን ዝርዝር ትምህርት ከአበው ቀኖና እና ትርጓሜ መጻሕፍት በጥልቅት መረዳት እንደሚገባ እየጠቆምኩ በሁሉም ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ትልቁ መዐርግ የሆነው የሥልጣነ ኤጲስ ቆጶስ በአግባቡ መፈጸም፣ መጠበቅ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ መሻገር ለሐዋርያዊ ትውፊት፣ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት፣ ለትምህርተ ወንጌል መስፋፋት፣ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቷ በተሟላ መልኩ መፈጸም መሠረት በመሆኑ፣ አስቀድመው ይዘጋጃሉ፣ በርካታ ተተኪ አበው መነኰሳትን በትምህርት፣ በዕውቀት፣ በጥበብ እና በክሕሎት፣ በአገልግሎት እና በኃላፊነት ብቃት ያሰለጥናሉ፤ ጥሪው የደረሳቸውን በተገቢው ቦታ ይሾማሉ፤ ይኽንን በማድረግም የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሉዓላዊነት እና ሕልውና ያስጠብቃሉ። የአባቶቻችን አምልክ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን አንድነት እና ሉዓላዊነት በአበው ኤጲስ ቆጶሳት ብቁ ተጋድሎና ጥብዓት ይጠብቅልን ሐዋርያዊ ትውፊትን አያቆርጥብን።

መምህር ዳንኤል ሰይፈሚካኤል ፈለቀ
የውጭ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ

የኤጲስቆጶስ (ጳጳስ) አባታዊ ተግባርና ኃላፊነት

«ወይእዜኒ ዕቀቡ ርዕሰክሙ ወኵሎ መራዕየ ዘሎቱ ሢመክሙ መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳተ ክመ ትርዐዩ ቤተ ክርስቲያኑ ለእግዚአብሔር እንተ አጥረያ በደሙ፡- በገዛ ደሙ የዋጀትን የእግዚብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቃት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጐ ለሾመባት፥ ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።» (የሐዋ. 20፥28)

ኤጲስቆጶስ የሚለው ስም ቃሉ ከግሪክ የተወሰደ ሲሆን፤ ለሚመተ ክህነት የሚሰጥስ ስመ ተቀብዖ ነው፡፡ መሠረታዊ የቃሉ ትርጓሜም እረኛ፥ ጠባቂ፥ የሃይማት መሪ፥ ተቆጣጣሪ የሚለውን ጽንስ ሐሳብ የያዘ ነው፡፡ ሚመተ ኤጲስቆጶስ በቤተ ክርስቲያናችን ትልቁና ከፍተኛው የሥልጣን ደረጃ ነው፡፡ ኤጲስቆጶስ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በበላይነት የሚመራና የሚያስተዳደር ከሁሉ በላይ የሆነ አባታዊ ሥልጣን ያለው አካል ነው፡፡

በኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ቀኖናዊ ሥርዓት መሠረት የሚመተ ክህነት ጉዳይ፥ ጽላት የማክበር፥ ቤተ ክርስቲያን የመባረክ፥ ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ መዳረስ፥ መንጋውን የመጠቅና ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን የማከናወኑ፥ አገልግሎት ሁሉ የኤጲስቆጶስ የሥራ ድርሻ ነው፡፡

ኤጲስቆጶስ (ጳጳስ) የሚለው ቃል በሐዲስ ኪዳን ለኤጲስቆጶስነት ለሚመረጡ ብፁዓን አበው የሚሰጥ ስያሜ ቢሆንም በክህነት የሚፈጸመው ሥርዐተ አምልኮት ግን ዓለም ከተፈጠረ፥ ዘመን ከተቆጠረ የሰው ልጅ ለፈጣሪው መገዛትና እሱን ማምለክ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ያለና የነበረ ነው፡፡

ከዘመነ አበው እስከ ሐዲስ ኪዳን ዋዜማ በእግዚአብሔር ፊትና በሕዝቡ መካከል ለክህነታዊው አገልግሎት የተመረጡ አበው ቅዱሳን የግብረ ኖሎቱን ሥራ የሚያፋጥኑ በነግሕና በሰርክ የሚዘወተረውን ጸሎትና መሥዋዕት ለአምላካቸው የሚያቀርቡ ቅዱሳን አባቶች እንደነበሩ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ዜና ገድላቸው ይመሰክራል፡፡

እነዚህ ቅዱሳን አበው በሕገ ልቡና በሕገ ኦሪት የነበረውን የእግዚአብሔር ሕዝብ ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ፥ ከሞት ወደ ሕይወት፥ ከአምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮተ አግዚአብሔር፥ ከጨለማ ወደ ብርሃን አሸጋግረዋል፡፡ በሕዝቡ ላይ መቅሰፍት በተላከ ጊዜ ስለ መንጋው እኛን ከሕይወት መጻሕፍት ደምስሰን እያሉ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ቁጣና መቅሰፍት አድነዋል፡፡

የሐዲስ ኪዳን ዘመን የሥርዓተ ክህነት አመሠራረትና ተልእኮው፡-

ሥርዓተ ክህነቱን የመሠረተና ፈቅዶ የሰጠ ራሱ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ሊቀ ካህናት ወኖላዌ አባግዕ መባል የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ ልዑለ ባሕሪይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ « አነ ውእቱ ኖላዊ ኄር አመ ኖላዊሰ ሄር ይሜጡ ነፍስ ቤዛ አባግኒሁ -- እኔ ቸርና ደግ እረኛ ነኝ፥ ደግ እረኛ ስለበጎቹ ነፍሱን አሳልፎ ይሰጣል (ዮሐ. 10፥11)። እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በየጊዜው ለሚጠሩት የመንጋው እረኞች ምሳሌያቸው በማለት እሱ እንደሆነ በዚሁ ቃለ ወንጌል አረጋግጦላቸዋል፡፡ ስለ በጎቹ የሚገደው እውተኛው እረኛ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ

መንጋው እስከ ሞት ድረስ የታመነ ሊሆን እንደሚገባው ይህ ቃለ ወንጌል ያስገነዝበናል። (ራእ 2፥10)

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን ሕይወት ለበጎቹ ቤዛ አድርጐ እንደሚሰጥ አስቀድሞ የተናገረውን ሕያው ቃሉን በቀራንዮ አደባባይ በራሱ ፈቃድ ስለ ሁላችን የሞት ዋጋ ሲከፍል ፍጹም የሆነ ፍቅሩን ሲገልጽ ተመልክተናዋልና።

«ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።» (ዮሐ. 15፥13)

እግዚአብሔር የመወደድ ምሥጢር የሚገለጸው ለተመረጡበት ዓላማ በመታመን ነው። የእግዚአብሔር ፍቅርም በዚህ ይገለጻልና፤ በቅዱስ መጽሐፍም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል «ዘይፈቅድ ይትልወኒ ይጽልኣ ለነፍሱ ወያጥብዕ ወይንሣእ መስቀል ሞቱ ወይትልወኒ -- እኔን መለከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ» (ማቴ. 16፥24)፤ ቅዱሳን ሐዋርያት ሚመተ ክህነቱን ከተቀበሉ በኋላ የተልዕኳቸው ዋና ዓለማ መንጋውን በመጠበቅና በመመገብ ላይ ያተኮረ እንደሆነ ለቅዱስ ጴጥሮስ በተሰጠው አደራ ታውቋል። (ዮሐ. 21፥15)

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ የተጠራችሁ ሁሉ ከዚህ ነውና፥ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌን ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሏልና በማለት የተጠሩበት ዓላማው ነገረ መስቀሉን ለመሸከም እንደሆነ አረጋግጧል። የሐዲስ ኪዳን የክህነት አገልግሎት በካህናት አለቃ በኢየሱስ ክርስቶስ ተመስርቶ ከቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ እንደ እሱ ሐሳብና ፈቃድ ለተጠሩት ሲታደል ከእኔ ዘመን ደርሲልወደፊትምይቀጥላል።

የክህነቱ ምንጭ ከቤተ ሌዌና ከቤተ አሮን በዘር መወለድን የሚጠይቀው የኦሪቱ የክህነት ሥርዓት አልፎ የዘር ውክልና ወደማይጠይቀው ሥርዓት አሻጋግሮናል።

ቅዱሳን ሐዋርያት የተጠሩት ከማይታወቁ ከድሀና ከተራ ቤተሰብ ሲሆን ይህ የአዲስ ሥርዓት ቤተ አይሁድንና ፈሪሳውያንን ሁሉ ያስቆጣ ነበር። የቅዱሳን ሐዋርያት መጠራት ከደማዊና ከሥጋዊ ሐሳብ የተነሣ ሳይሆን በእሱ መለኮታዊ ፈቃድ ሁሉን ትተው እንደ ተከተሉት ዜና ገድላቸው ይመሰክራል።

የሐዲስ ኪዳን የክህነት ጥሪ

«ንዑ ወእሬስየክሙ ትውልድኒ ድኃሬየ ወእሬዕየክሙ ትኩኑ መሰግራናነ ስብእ -- ከኋላዬ ተከሉኝ፤ ሰዎችን አጥማጅ እንድትሆኑ አድጋችኋለሁ» (ማቴ. 4፥19) በሚለው አምላካዊ ቃል የተጀመረ ነው።

ከዋለበት እየዋሉ ካደረበት እየደሩ የቃሉ ትምህርት፥ የእጁ ተአምራት ሳይከፈልባቸው ወደፊት ከእሱ እጅ የሚቀበለትን አደራ ለመሸከም የሚያስችላቸው ምሥጢርና ሐዋርያዊ ተልኮውን ለ3 ዓመታት እንዳስተማራቸው በዚህ እናውቃለን።

12ቱ ደቀ መዛሙርት በ3 ዓመታት ጉዞአቸው ከእሱ ያዩትና የሰሙት ሁሉ ለተጠሩለት ሚመተ ክህነት የነበረው ቅድመ ዝግጅት ያመለክታል። ለግብረ ክህነት የሚጠራ ሐዋርያ ከሥጋዊና ደማዊ ጠባይ ተለይቶ ከመንፈስ ቅዱስ በሚሆን የጸጋ ስጦታ አጋንንትን ያወጣል፥ ሕሙማን ይፈውሳል፥ ተአምራትን ያደርጋል (ማቴ. 10፥6-8፤ ሉቃ. 10፥9)። ብፁዕ ወቅዱስ የመባል ጸጋን ያገኛል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቂሣርያ ሀገር ደቀ መዛሙርቱን ሰዎች የሰውን ልጅ

ማን እንደሆነ ይሉታል ብሎ ሲጠይቃቸው፡- መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ነው፥ ኤልያስ ነው፥ ኤርምያስ ነው፥ ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል፤ ባሉት ጊዜ እናንተስ እኔን ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ ሲላቸው፡- ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ «አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ሲለው ክርስቶስም መልሶ፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህንን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ፤ እኔም እልሃለሁ አንተ ዐለት ነህ፤ በዚችም ዓለት ላይ ቅድስት ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም፤ የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎችን እሰጥሃለሁ፥ በምድር የታሠረው በሰማያተ የተሠረ ይሆናል» በሚለው አምላካዊ ቃል ተረጋግጧል፡፡ (ማቴ 16፥13-20። ማቴ. 18፥18)

በሐዲስ ኪዳን ዘመን ብፁዕ ወቅዱስ ንዑድ፥ ወክቡር መባልን ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ምስጢር ተገልጾለት ስለ ባሕርይ አምላክነቱ በመሰከረ ጊዜ የምሥጢር ባለቤት፥ የጥበብ መገኛ የሆነው አምላክ ቅዱሳን ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ሐዲስ ኪዳን ሥርዐተ ክህነት አስቀድሞ የነገራቸውንና ያሳያቸውን ከትንሣኤው በኋላ በአንብሮተ እድ የሚፈጸመውን ሀብተ ክህነት እንዴት እንደሰጣቸው በቅዱስ ወንጌል ተዘግቧል፡ : «አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ» አላቸው። ይህንም ብሉ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስ ተቀበሉ፤ «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችሁ ላቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው።» (ዮሐ. 20፥20-23፤ የሐዋ. 2፥1)

በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዊ መስፈርቱን አሟልተው እንደ ሕጉና እንደ ሥርዐቱ ለተጠሩት ልጆቿ ሀብተ ክህነቱን ስታድል ከጥነት እስከዛሬ ክብሩን አስጠብቃ እንሆ ዛሬም ለትውልድ እያስረከበች ትገኛለች፡፡

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዶግማዋን፥ ቀኖናዋንና ክብረ ክህነቱን በማቃለልና በመንቀፍ የሚፈታተኑት አጽራረ ክህነት እውነታ ባይካድም የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃው ሳይለያት እስከ ዓለም ፍጻሜ እንደምትቀጥል አንጠራጠርም፡፡ ወንጌላዊ ቅዱስ ማቴዎስ እንዲህ ሲል ዘግቧል፡- «ወናሁ አነ እሄሉ ምስሌክሙ በኵሉ መዋዕል እስከ ኀልቀተ ዓለም» (ማቴ 28፥20)፤

የዘመኑ ትውልድ ከቤተ ክርስቲያን አባቶች የሚጠብቀው ተግባርና ኃላፊነት ምንድን ነው? ለሚለው ወቅታዊ የቤተ ክርስቲያናችን ወቅታዊ ቁልፍ ጉዳይ፡- በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ቀኖናዊ ሥርዓት የክህነት መዓርጋት ከታች ወደላይ በደረጃ ሲገለጽ ዲቁና፥ ቅስና፥ ጵጵስና፥ ሊቀ ጵጵስና፥ ፓትርያርክ ናቸው፡፡ ዲያቆኑም ሆነ ቄሱና ቆሞሱ የሚሾሙት በኤጲስቆጶሱ አንብሮተ እድ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያናችን ሁለንተናዊ የውጭና የውስጥ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብቷ ሁሉ የሚመራው በጳጳሱ የበላይነት ነው፡፡

ጳጳሱ (ሊቀ ጳጳሱ) በተሾመበት ሀገረ ስብከት ሁሉም የቤተ ክርስቲያንዋ አገልጋይ ተጠሪነቱ ለክፍሉ ጳጳስ እንደሆነ በሕገ ቤተ ክርስቲያን ታዟል። የሚያዝበት የማይናዘዝበት የቤተ ክርስቲያን ሀብት የለም፡፡ በሁሉም ላይ የማይገደብ የሥልጣን ልዕልና ለጳጳሱ ብቻ የተሰጠ ጸጋ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ሀብት ላይ የተሾመው ጳጳስ ከእኔ ምን ይጠበቃል ማለትን ሊያስቀድም እንደሚገባው ይታመናል። ቅዱሳን ሐዋርያት በግብር እንዲመስሉት ጠርቶ ለሾማቸው አምላክ የቅርብ ተጠሪዎች እንደሆኑ ሁሉ ዛሬም ኤጲስቆጶሱ የእግዚአብሔር እንደራሴ

እንደሆነ እናምናለን:: ምክንያቱም የያዘው ሥልጣነ ክህነት ከጌታ ደቀ መዛሙርት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ስለሆነ ነው:: የኤጲስቆጶስ የምርጫ ጥሪ በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት ሊፈጸም ይገባዋል።

ከጥንት ጀምሮ አበው ቅዱሳን በደነገጉት ቀኖና ቤተ ክርስቲያንና የሕግ ምንጭ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ ባወጣው በሕገ ቤተ ክርስቲያን የኤጲስቆጶስ የምርጫ ማስፈጸሚያ ሊከበር ይገባል።

በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን ቀኖናዊ ሥርዐት ለኤጲስቆጶስነት የተሾመ አባት ኃላፊ ከሆነው ምድራዊ ፍላጎት ተለይቶ ራሱን በመካድ ሙሉ ሕይወቱ ለተጠራበት ዓላማ በመስጠት አርዐተ መስቀሉን ተሸክሞ ለመንጋው ምሳሌ ሊሆን የሚሆን:: «ወናሁኬ ንሕነ ኀደግነ ኵሎ ወተለውናከ ምንተ እንከ።» (ማቴ 19፥27)

የመሪነት ሚናንን በሚመለከት

የኤጲስቆጶስነቱ ጥሪ ፍጥረታዊ የሐሳብ ውሳኔ ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ በቅድሚያ አምኖ መቀበል ያስፈልጋል:: በአገልግሎቱ ጽንዓት የሚገኘው ዋጋም ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ አይደለም:: የተልእኮው ዓላማም በዚህ ዓለም ያይደለ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊት ሕይወት ለማትረፍ የሚደረግ ተጋድሎ ነው::

አበው ቅዱሳን በሄዱበት ቀጥተኛ መንገድ መቀጠል የግድ ነው፤ ጉዞውም እስከ ሞት የሚደርስ ዋጋን ያስከፍላል (ማቴ. 10፥16)፤ ታዲያ በብዙ ፈተና መካከል አልፎ የእግዚአብሔር ሰማያዊ መንግሥቱን ለመውረስ የሚደረግ ውድድር ስለሆነ ሁሉን በጸጋ መቀበልና ፈተናው መታገስ የአንድ ኤጲስቆጶስ የተለመደ የዘወትር ተግባር መሆኑ መዘንጋት የለበትም ::

ቀጥሎም ወላዲተ ኵሉ የሆነችውን አሐቲ ቤተ ክርስቲያንና ልጆቿን ለመጠበቅ ኃላፊነት ከተቀበለ ኤጲስቆጶስ የሚጠበቁ ዋና ዋና ተግባራት መኖራቸው ሊሠመርበት ይገባል::

1. በኦርቶዶክሳዊ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በብፁዕ ወቅዱስ ፖትርያርኩና በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጸሎትና ቀኖናዊ ሥርዓት በአንብሮተ እድ ሢመተ ጵጵስና ተፈጽሞ ሙሉ ሃላፊነቱ ከተጠያቂነቱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ፥ ከመንበረ ጵጵስናው ሳይለይ ሁሉንም የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ጉዳይ በሕጉና በሥርዓቱ እንዲከናወን አባታዊ መመሪያ መስጠት፤

2. የቅድስት ቤተክርስቲያናችን ዶግማዋና ቀኖናዋ፥ ሥርዓቷና ትውፊቷ ተጠብቆና ተከብሮ እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል፤

3. የቤተ ክርስቲያናችን ዋና ተግባር የሆነው የእግዚአብሔር ወንጌለ መንግሥት ለሁሉም ይደርስ ዘንድ የስብከት አገልግሎት እንዲስፋፋ ርቱዓነ ሃይማኖት የሆኑ ትጉሃን ሰባክያንን ማብዛት ይጠበቃል፤

4. ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የመሠረት ድንጋይና የማይነቃነቅ ዓምድ የሆነውን የአብነት ትምህርት ቤት የጉባኤ መምህራንን የዕውቀት ምንጭነታቸው እንዳይነጽፍ፥ እንዲሁም ገዳማትንና ገዳማውያንን በምናኔ ሕይወታቸው ጸንተወ እንዲቀጥሉ ማጠናከርንና መደገፍ የዘወትር ትኩረት ሊሆን ይገባል::

5. የድኅነታችን ማእከል የሆነችውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና መንጋውን ከቢጽ ሐሳውያንና ከመናፍቃን ወረራ መጠበቅ ያስፈልጋል።

6. አዲሱ ትውልድ ዘመንና ጊዜ በወለደው ኃላፊና ጠፊ ፈተና ተሸርሽሮ ከክርስትናው ሐዲዲ (መስመር) ወጥቶ ስመ ክርስትና ሀብተ ወልድን አግኝቶ ከከበረበት ከእናቱ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንድነት ተለይቶ እንዳይጠፋ

አባታዊ ዋጋ መክፈል ይጠበቃል።

7. የእግዚአብሔርን ሰማያዊ መንግሥት ይወርሱ ዘንድ ለተጠሩት የመንፈስ ቅዱስ ልጆች በሃይማኖታቸውና በክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ጸንተው ይኖሩ ዘንድ ከመሐል እስከዳር፥ ከከተማ እስከ ገጠር፥ ከቅርብ እስከ ጠረፍ በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን አገልግሎት መቆጣጠርና የጐደለውን ሚሚላት ዋናው ተግባር ነው።

8. በአንብሮተ እድ ሢመተ ክህነት የማደል ጸጋ ለጳጳሱ ብቻ የተሰጠ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ፥ ለማይገባቸውና ሺሞናዊ መንፈስ ላደረባቸው ሰዎች እንዳይሰጣቸው ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠይቃል።

9. በአጠቃላይ ከጌታችን እየሱስ ክርስቶስ እጅ ምሥጢረ ክህነትን ከተቀበሉት ከቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ ለትውለድ ትውልድ በቅብብሎሽ ከዚህ የደረሰውን አደራ ለማስቀጠል እንደቀደምት አበው የሕሊና ጥብዓት ያስፈልጋል። ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸምና ማስከበር፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መጠበቅና ማሠማራት፥ መመገብና መምራት ከምንም በላይ የቤተ ክርስቲያኗን ውስጣዊና ውጫዊ መዋዕለ ሀብቷን ማስተዳደርና፥ መቆጣጠር፥ በሕገ ቤተ ክርስቲያን እንደተደነገገው ሊተገበር ይገባዋል።

10. በመጨረሻም በእግዚአብሔር ዘንድ ሰማያዊ ክብርና ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚገኝበትን ክህነታዊ አደራ መጠበቅ ከብፁዕ ወቅዱስ ፖትሪያርኩና ከብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ጀምሮ በየደረጃው የሚገኙ የክህነቱ ተጠሪዎች ሃላፊነትና ድርሻ ነው።

በግብረ ክህነቱ የሚያገለግሉ ሁሉ ከእግዚአብሔር እጅ የተቀበሉት መክሊት አለ። መክሊቱን ማብዛትም ሆነ ቆፍሮ መቅበር የአገልጋዩ ውሳኔ ይሆናል። የመክሊቱ ባለቤት አንድ ቀን መቆጣጠሩ የማይቀር ስለሆነ፥ ከወቀሳና ከፍርድ ለመዳን የተቀበሉትን መክሊት አብዝቶና አትርፎ ባለመክሊቱ ለመቆጣጠር ሲመጣ ታማኝነቱን በማስመስከር ለበለጠ ክብር መዘጋጀት ያስፈልጋል። (ማቴ. 25፥14-30)

“ከሁሉ በሚያንስ የታመነ በብዙ ደግሞ የታመነ ነው፤ ከሁሉ በሚያንስ የሚያምጽ በብዙ ደግሞ አይታመንም” (ሉቃ 16፥10) ተብሎ ተጽፏልና።

ከቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አዕማድ የሆኑ 318 ሊቃውንትና ሌሎችም አበው ቅዱሳን ደማቸውን አፍስሰው፥ አጥንታቸውን ከስክሰው የሰማዕትነትን ዋጋ ተቀብለው ያቆዩዋትን አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ርትዕት ሃይማኖታችን መጠበቅና በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምኖ መኖርን ማመን ማስቀጠሉ የሁሉም አገልጋይ ድርሻ ነው። ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ወደ በጎች በረት በዋናው በር ያልገቡ፤ ሳይጠሩ ፍቅረ ሢመት ክህነት አገብሯቸው ቀኖናን የጣሉ ቢኖሩ ወደ እውነተኛው መንገድ መመለስ ይችሉ ዘንድ የሁላችንም ጥረት ሊሆን ይገባል።

በቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ ንጹሕ ዘር የሆነ ሀብተ ክህነት በመንገድ ዳርና በጥላ ላይ እንደወደቀው ዘር እንዳይሆን ሁሉም ማጎበረ ካህናትና ምእመናን ሊጠብቁ ይገባል። ከምንም በላይ የቤተ ክርስቲያን አምላክ ቤቱን እንደሚጠብቅ እናምናለን።

የአባቶቻችን አምላክ ቅዱስ እግዚአብሔር ወደቀናው መንገድ ይመልሰን፤ ማስተዋሉንና ጥበቡ ያድለን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ

ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር

ሊቃ ጳጉያን ሠርፀ አበበ

የሕዝብ ግንኙነት መምሪያ ም/ኃላፊ